# መጽሐፈ ነህምያ

**የመጽሐፈ ዕዝራን መግቢያ ይመ**

**አስተዋፅኦ**

1. የነህምያ የመጀመሪያው አስተዳደር (ም1-12)
   ሀ. ነህምያ በኢየሩሳሌም ስላጋጠመው ሁኔታ የሰጠው ምላሽ
      (1) በኢየሩሳሌም ስለ ሆነው አሳዛኝ ነገር የመጣው ወሬ (1፥1-4)
      (2) የነህምያ ጸሎት (1፥5-11)
   ለ. ነህምያ ወደ ኢየሩሳሌም ያደረገው ጉዞ (ም2)
      (1) የንጉሡ መልስ (2፥1-8)
      (2) ጉዞው (2፥9-10)
      (3) ነህምያ ቅጥሩን መጐብኘቱ (2፥11-16)
      (4) ቅጥሩን እንደ ገና ለመሥራት ሕዝቡን ማበረታታቱ (2፥17-18)
      (5) የሰንባላጥ፣ የጦቢያና የጌሳም ተቃውሞ (2፥19-20)
   ሐ. ቅጥሩን የጠገኑት ሰዎች ዝርዝር (ም3)
      (1) የሰሜኑ ክፍል (3፥1-7)
      (2) የምዕራቡ ክፍል (3፥8-13)
      (3) የደቡቡ ክፍል(3፥14)
      (4) የምሥራቁ ክፍል (3፥15-32)
   መ. ቅጥሩ እንደ ገና እንዳይጠገን የተደረገ ተቃውሞ (ም4)
      (1) የሰንባላጥና የጦቢያ ፌዝ (4፥1-5)
      (2) ለማስፈራራት የተደረገ ዛቻ (4፥6-15)
      (3) የቅጥሩ እንደ ገና መጠገን (4፥16-23)
   ሠ. ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች (ም5)
      (1) ድኾች ያሰሙት ሮሮ (5፥1-5)
      (2) የዕዳ መሠረዝ (5፥6-13)
      (3) የነህምያ አርአያነት (5፥14-19)
   ረ. ተቃውሞ ቢኖርም ቅጥሩ መሠራቱ (ም6)
      (1) ነህምያን ለማጥመድ የተደረገ ሙከራ (6፥1-9)
      (2) ሐሰተኞች ነቢያትን በገንዘብ መቅጠር (6፥10-14)
      (3) የቅጥሩ ሥራ መጠናቀቅ (6፥15-19)
   ሰ. ከምርኮ የተመለሱት ሰዎች ስም ዝርዝር (7፥1-73ሀ)
      (1) ለኢየሩሳሌም የተደረገ ጥበቃ (7፥1-3)
      (2) ከምርኮ የተመለሱትን ሰዎች ስም ዝርዝር ነህምያ ማግኘቱ (7፥4-5)
      (3) ከምርኮ የተመለሱት ሰዎች ስም ዝርዝር በሚገባ መጣራቱ (7፥6-72)
      (4) ከምርኮ የተመለሱት ሰዎች በየከተሞቻቸው መቀመጣቸው (7፥73)
   ሸ. የዕዝራ ስብከትና የተሐድሶው ሥራ እንቅስቃሴ መጀመር (7፥73ለ-10፥39)
      (1) የሕጉ መጽሐፍ ለሕዝቡ እየተብራራ መነበቡ (7፥73ለ-8፥12)
      (2) የዳስ በዓል (8፥13-18)
      (3) የጾም፣ የንስሐና የኑዛዜ ቀን (9፥1-5ሀ)
      (4) እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር የነበረው ግንኙነት መወሳቱ (9፥5-31)
      (5) ኀጢአትን መናዘዝ (9፥32-37)
      (6) የሚያስተሳስር ስምምነት (9፥38)
      (7) ውሉን ያተሙት ሰዎች (10፥1-29)
      (8) የስምምነቱ ዝግጅት (10፥30-39)
   ቀ. አዲሶቹ የይሁዳና የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች (ም11)
      (1) አዲሶቹ የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች (11፥1-24)
         ሀ) የመግቢያ ሐሳብ (11፥1-4ሀ)
         ለ) ከይሁዳ ወገን የመጡ (11፥4ለ-6)
         ሐ) ከብንያም ወገን የመጡ (11፥7-9)
         መ) ከካህናት ወገን የመጡ (11፥10-14)
         ሠ) ከሌዋውያን ወገን የመጡ (11፥15-18)
         ረ) ከቤተ መቅደስ አገልጋዮች የመጡ (11፥19-24)

(2) አዲሶቹ የይሁዳ ነዋሪዎች (11፥25-36)
ሀ) የይሁዳ ሰዎች የተቀመጡባቸው ቦታዎች (11፥25-30)
ለ) የብንያም ሰዎች የተቀመጡባቸው ቦታዎች (11፥31-35)
ሐ) ከይሁዳ ወደ ብንያም አገር የሄዱ ሌዋውያን (11፥36)
በ. የካህናቱ ስም ዝርዝርና የቅጥሩ ምረቃ (ም12)
(1) ከምርኮ የተመለሱት የመጀመሪያዎቹ ካህናትና ሌዋውያን (12፥1-9)
(2) ከኢዮአቄም መንግሥት ጀምሮ የነበሩ ሊቃነ ካህናትና ሌዋውያን (12፥10-26)
(3) የኢየሩሳሌም ቅጥር ምረቃ (12፥27-43)
(4) በቤተ መቅደሱ የሚከናወነው የቍርባን አቀራረብና የአምልኮ ሥርዐት አፈጻጸም (12፥44-47)

2 የነህምያ ሁለተኛው አስተዳደር (ም13)
ሀ. ነህምያ በሌለበት ጊዜ የተሠሩ ስሕተቶች (13፥1-5)
(1) ከባዕዳን ጋር የተደረገ ጋብቻ (13፥1-3)
(2) ጦቢያ ከቤተ መቅደሱ ክፍሎች አንዱን መያዙ (13፥4-5)
ለ. ነህምያ ወደ ኢየሩሳሌም መመለሱ (13፥6-9)
(1) ኢየሩሳሌም መድረሱ (13፥6-7)
(2) ጦቢያን ማባረሩ (13፥8-9)
ሐ. እንደ ገና የማደራጀቱና የማደሱ ሥራ (13፥10-31)
(1) ለቤተ መቅደሱ አገልጋዮች ስለሚሰጠው ድርሻ (13፥10-14)
(2) ሰንበትን አለማክበር /አለመቀደስ (13፥15-22)
(3) ከባዕዳን ጋር የተደረገ ጋብቻ (13፥23-29)
(4) ዕንጨትና በኵራት ስለ መስጠት (13፥30-14)

## የነህምያ ጸሎት

1 የሐካልያ ልጅ የነህምያ ቃል፤
በሃያኛው ዓመት ካሴሉ በተባለው ወር በሱሳ
ግንብ ሳለሁ፣ 2ከወንድሞቼ አንዱ የሆነው
አናኒ፣ ከሌሎች ጥቂት ሰዎች ጋር ከይሁዳ
መጣ፤ እኔም ከምርኮ ስለ ተረፉት የአይሁድ
ቅሬታዎችና ስለ ኢየሩሳሌም ጠየቅኋቸው።
3እነርሱም በሕይወት ተርፈው "ከምርኮ ወደ
አገራቸው የተመለሱት ሰዎች በታላቅ መከራና
ውርደት ላይ ይገኛሉ፤ የኢየሩሳሌም ቅጥር ፈራ
ርሶአል፤ በሮቿም በእሳት ተቃጥለዋል" አሉኝ።
4ይህን ነገር በሰማሁ ጊዜ ተቀምጬ አለ
ቀስሁ፤ በሰማይም አምላክ ፊት አያሌ ቀናት
ዐዘንሁ፤ ጾምሁ፤ ጸለይሁም። 5ከዚያም እንዲህ
አልሁ፤

"ለሚወዱህና ትእዛዝህን ለሚያከብሩ የፍቅ
ርህን ቃል ኪዳን የምትጠብቅ ታላቅና የተፈራ
ህ አምላክ፣ የሰማይ አምላክ *እግዚአብሔር*
ሆይ፤ 6ባሪያህ ስለ አገልጋዮችህ ስለ እስራ
ኤል ሕዝብ ቀንና ሌሊት በፊትህ የሚ
ጸልየውን ጸሎት ለመስማት ጆሮህ ይንቃ፤
ዐይንህም ይከፈት። እኔንና የአባቴን ቤት
ጨምሮ እኛ እስራኤላውያን አንተን በመ
በደል የሠራነውን ኀጢአት እናዝዛለሁ። 7በአ
ንተ ላይ እጅግ ክፉ ሥራ ሠርተናል፤ ለባሪያ
ህም ለሙሴ የሰጠኸውን ትእዛዝ፣ ሥርዐ
ትና ሕግ አልጠበቅንም።
8"ለባሪያህ ለሙሴ እንዲህ ስትል የሰጠ
ኸውን ቃል አስብ፤ 'ታማኞች ካልሆናችሁ፣
በአሕዛብ መካከል እበትናችኋለሁ፤ 9ወደ እኔ
ብትመለሱና ትእዛዞቼን ብትፈጽሙ፣ የተ
ሰደዱት ወገኖቻችሁ እስከ ምድር ዳርቻ
ድረስ እንኳ ቢበተኑ፣ ከዚያ እሰበስባቸዋ
ለሁ፤ ለስሜም ማደሪያ ወደ መረጥሁት
ስፍራ አመጣቸዋለሁ።'
10"እነዚህም በታላቅ ኀይልህና በብርቱ
እጅህ የተቤዠሃቸው ባሪያዎችህና ሕዝብህ
ናቸው። 11*እግዚአብሔር ሆይ*፤ የባሪያህን ጸሎት፣
ስምህን በመፍራት ደስ የሚሰኙትን የባሪያ
ዎችህንም ጸሎት ጆሮህ ታድምጥ። በዚህ
ሰው ፊት ሞገስን አድርገህለት ዛሬ ለባሪያህ
መከናወንን ስጠው።"

በዚያን ጊዜ እኔ የንጉሡ ጠጅ አሳላፊ
ነበርሁ።

1፥1 ዕዝ4፥9፤ አስ2፥8፤ዘካ2፥1
1፥2 2ነገ21፥14፤ ነህ7፥2:6፤ኤር52፥28
1፥3 ዘሌ26፥31፤ 2ነገ25፥10ነህ፤2፥3፡ 13:17፤ኢሳ22፥9፤ ኤር39፥8፤52፥14፤ ሰቆ2፥9
1፥4 2ዜና20፥3፤ ዕዝ9፥4፤ መዝ137፥1፤ዳን9፥3
1፥5 ዘዳ7፥9:21፤ 1ነገ8፥23፤ነህ4፥14፤ ዳን9፥3
1፥6 1ነገ8፥29:3፤ 47፤2ዜና7፥15
1፥7 መዝ106፥6
1፥8 ዘፍ8፥1፤ ዘሌ26፥33፤2ነገ20፥3፤ ነህ4፥14፤5፥19፤ 6፥14፤13፥22:29:31
1፥9 ዘዳ 30፥4፤1ነገ 8፥48፤መዝ 106፥47፤107፥3፤ኢሳ 11፥12፤ 56፥8፤ ኤር 29፥14፤ 42፥12፤ ሕዝ 11፥17፥20፥34-38፤ 36፥24-38፤ ሚክ 2፥12
1፥10 ዘፀ 32፥11፤ ኢሳ 51፥9-11 1፥11 ዘፍ 40፥1፤ ዘፀ ፥21፤ 2ዜና6፥40

1፥1 *የ … ቃል፤* ከጥንት ጀምሮ የዕዝራና የነህምያ መጻሕፍት እንደ አንድ መጽሐፍ ቢቈጠሩም (በመጽሐፍ ዕዝራ መግቢያ ላይ "ዕዝራና ነህምያ" የሚለውን ይመ)፣ በዚያ ዘመን አንድን ጽሑፍ "የእገሌ ቃል" ብሎ መጀመር የተለመደ ነበር። (ኤር1፥1፤ አሞ1፥1 ይመ)። *ነህምያ*፤ የስሙ ትርጒም፣ "እግዚአብሔር ያጽናናል" ማለት ነው። *ሐካልያ*፤ ትርጒሙ "እግዚአብሔርን ጠብቅ" ማለት ሊሆን ይችላል፤ ይህ ስም ድጋሚ የተጠቀሰው በ10፥1 ላይ ብቻ ነው። *በሃያኛው ዓመት ካሴሉ፤* በኅዳር/ታኅሣሥ ወር፣ 445 ዓ.ቅ.ክ. ላይ ይውላል፤ "ዕዝራ - ነህምያ የሚለውን ሰንጠረዥ በገጽ 675 ይመ። *በሱሳ*፤ የዕዝ 4፥9 ማብ ይመ።

1፥2 *አናኒ፤* ምናልባት "ሐናንያ" ለሚለው ስም አጭር መጠሪያ ሲሆን፣ ትርጒሙም "እግዚአብሔር ቸር ነው" ማለት ነው። *ከወንድሞቼ አንዱ*፤ 7፥2 ይመ። በግብፅ አገር ኤሌፋንታይ ተብሎ በሚጠራው ስፍራ የተገኘ ፓፒረስ እንደሚያስረዳው፣ በኢየሩሳሌም የአይሁድን ሕዝብ ጒዳይ በኀላፊነት የሚመራ ሐናንያ የሚባል ሰው ነበር። የነህምያ ወንድም እንደ ነበርና፣ በነህምያ አመራር ወቅት ሕዝቡን ሳያስተዳድር እንዳልቀረ ብዙዎች ይናገራሉ (የ7፥2 አማራጭ ትርጒም ይመ)። *ቅሬታዎችና*፤ የዕዝ 9፥8 ማብ ይመ።

1፥3 *አገራቸው፤* የዕዝ 2፥1 ማብ ይመ። *የኢየሩሳሌም ቅጥር ፈራርሶአል*፤ በጥንት ዘመን አንድ ከተማ ቅጥር የላትም ማለት የከተማዋ ነዋሪዎች ከጠላቶቻቸው የሚከላከሉበት ነገር የላቸውም ማለት ነው። የአቴናም ከተማ በ480-479 ዓ.ቅ.ክ. በፋርስ ሰዎች ከፈራረሰች በኋላ ይህን መሰል ገጽታ እንደ ነበራት ቱሲዲዲስ የተባለ ጸሓፊ ገልጾአል። የኢየሩሳሌም ቅጥር በምሥራቅ በኩል ሲፈርስ በዚያ የነበሩ እርከኖችም ፈራርሰው እንደ ነበር በ1961-67 ዓ.ም. በከተማይቱ የተደረገው የሥነ ቅርስ ቍፋሮ ያመለክታል። ናቡከደነፆር ኢየሩሳሌምን ወሮ በያዘበት ጊዜ፣ ቅጥሯን አፈረሰ (2ነገ 25፥10)። ነገር ግን የነህምያ ጭንቀት በዕዝ 4፥7-23 ላይ የተገለጸው ሁኔታ እንጂ፣ ናቡከደነፆር በ586 ዓ.ቅ.ክ. ያደረሰው ጥፋት እንዳልሆነ ብዙዎች ያምናሉ። የአይሁድ ሕዝብ በቀዳማዊ አርጤክስስ የከተማውን ቅጥር መልሰው ለመገንባት ቀደም ሲል ሙከራ አድርገው ነበር፤ ነገር ግን ሬሁምና ሲምሳይ ባመፁ ጊዜ የአይሁድ ሕዝብ ሥራውን እንዲያቋርጡ ንጉሡ ትእዛዝ አስተላልፎ ነበር፤ የዕዝ 4፥21-23 ማብ ይመ።

1፥4 *ተቀምጬ፤* ከዕዝ 9፥3፤ ከኢዮ 2፥13 ጋር ያነጻጽሩ። *አለቀስሁ፤* 8፥9፤ዕዝ3፥13 እና ማብ፤ 10፥1፤አስ 8፥3 ይመ። *በሰማይም አምላክ* የዕዝ 1፥2 ማብ ይመ። *ዐዘንሁ፤* ዕዝ 10፥6፤ ዳን 10፥2 ይመ። *ጾምሁ፤ ጸለይሁም፤* የዕዝ 8፥23 ማብ ይመ። በምርኮው ዘመን ጾም በሕዝቡ ዘንድ የተለመደ ነበር፤ በምርኮው ዘመን ስለ ኢየሩሳሌም መውደቅና ስለ ጎዶልያስ መገደል በማሰብ ጾም በሕዝቡ ዘንድ ይዘወተር ነበር (2ነገ 25፥22–25 ይመ፤ የዘካ 8፥19 ማብ እንዲሁም አስ 4፥16፤ዳን 9፥3፤ 10፥3፤ ዘካ 7፥3-7 ይመ)።

1፥5 *የፍቅርህን፤* "ጽኑ ፍቅር" ማለት ነው፤ ይኸውም በደስታም ሆነ በመከራ ጊዜ ቃል ኪዳኑ የሚከበር መሆኑን ያመለክታል።

1፥6 *ቀንና ሌሊት በፊትህ የሚጸልየውን*፤ ከመዝ 42፥3፤ 88፥1፤ኤር 9፥1፤14፥17፤ሰቆ 2፥18፤ሉቃ 2፥37፤1ተሰ 3፥10፤1ጢሞ 5፥5፤2ጢሞ 1፥3 ጋር ያነጻጽሩ። *እኔንና የአባቴን ቤት … ኀጢአት*፤ ነህምያ የሕዝቡን ኀጢአት በሚናዘዝበት ጊዜ የራሱንና የቤተሰቡንም ኀጢአት ይናዘዝ ነበር፤ የእግዚአብሔርን ማንነት በትክክል ማስተዋል ስንችል፣ የራሳችን ኀጢአት ምን ያህል አስከፊ እንደ ሆነ ይገለጥልናል (ኢሳ 6፥1-5፤ ሉቃ 5፥8)።

1፥7 *ትእዛዝ፣ ሥርዐትና ሕግ*፤ የዘፍ 26፥5 ማብ ይመ። *ለሙሴ*፤ የሙሴ ሕግ፣ በዕዝራና በነህምያ መጻሕፍት ምን ያህል ጐልቶ እንደሚታይ ለመገንዘብ ዕዝ 3፥2፤ 6፥18፤ 7፥6፤ ነህ 1፥8፤ 8፥1፡ 14፤ 9፥14፤ 10፥29፤ 13፥1 ይመ።

1፥8 *አስብ፤* የ13፥31 ማብ ይመ፤ የመጽሐፉ ቁልፍ ቃል ነው (4፥14፤ 5፥19፤ 6፥14፤ 13፥14፡ 22፡ 29፡ 31)። *ታማኞች ካልሆናችሁ … እበትናችኋለሁ፤* የእግዚአብሔር ሕዝብ ለአምላኩ ካልታመነ መበተኑ ምን ጊዜም የማይቀር ነው፤ በአዲስ ኪዳን ዘመንም በፓለስቲና ከሚኖረው ይልቅ በየአገሩ የተበተነው የአይሁድ ሕዝብ ቍጥር ከፍተኛ ነበር።

1፥9 *እሰበስባቸዋለሁ፤* ዘዳ 30፥1-5 ይመ፤ የተስፋ ቃል ሲሆን፣ በነቢያት መጻሕፍት ውስጥ ተደጋግሞ ተጠቅሶአል (ለምሳሌ ኢሳ 11፥12፤ ኤር 23፥3፤ 31፥8-10፤ ሕዝ 20፥34፡ 41፤ 36፥24፤ ሚክ 2፥12)። *ለስሜም ማደሪያ ወደ መረጥሁት ስፍራ፤* ዘዳ12፥5 እና ማብ፤ መዝ 132፥13 ይመ።

1፥10 *የተቤዠሃቸው … ሕዝብህ*፤ ኀጢአት ሠርተው ቢወድቁም እንኳ በጸጋው ያዳናቸው ስለ ሆነ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው (ዘዳ 4፥34፤ 9፥29 ይመ)።

1፥11 *ዛሬ ለባሪያህ መከናወንን ስጠው*፤ ከዘፍ 24፥12 ጋር ያነጻጽሩ። *ጠጅ አሳላፊ፤* በቀሙ ሲተረጐም "መጠጥ አቅራቢ" ማለት ነው። ይህን ቃል ለመግለጽ የገባው የዕብራይስጡ ቃል በዚሁ ትርጒሙ ("ጠጅ አሳላፊ") በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በሌላ ስፍራ ዐሥራ አንድ ጊዜ ተጠቅሶአል (ዘፍ 40፥1-2:5:9:13:20-21:23፤41፥9፤ 1ነገ 10፥5፤ 2ዜና 9፥4)። ዚኖፎን የተባለው ግሪካዊ ታሪክ ጸሓፊ እንደ ዘገበው፣ ከጠጅ አሳላፊው ተግባሮች አንዱ ለንጉሡ ሲቀርብ የሚገባውን ጠጅ መምረጥና መርዝ እንዳልተጨመረበት ቀምሶ ማረጋገጥ ነው (2፥1 ይመ)። ይህም የሚያሳየው ነህምያ በንጉሡ ዘንድ እጅግ የታመነ ሰው መሆኑን ነው። አቻመኒድ በተባለው የፋርስ ንጉሥ ግቢ ውስጥ የተፈጸመው ድርጊት የታማኝ ጠባቂን አስፈላጊነት ያስገነዝባል፤ የቀዳማዊ አርጤክስስ አባትም በመኝታ ክፍሉ ውስጥ እንዳለ በገዛ ባለሟሉ ተገድሎአል።

## አርጤክስስ ነህምያን ወደ ኢየሩሳሌም እንዲሄድ ፈቀደለት

2 በንጉሡ በአርጤክስስ ዘመነ መንግሥት
በሃያኛው ዓመት ኒሳን ተብሎ በሚጠራው
ወር የወይን ጠጅ በመጣለት ጊዜ፣ የወይን ጠጁን
አንሥቼ ለንጉሡ ሰጠሁት። ቀድሞ በፊቱ
ዐዝኜ አላውቅም ነበር፤ 2 ስለዚህ ንጉሡ፣
“ሳትታመም ፊትህ ለምን እንዲህ ዐዘነ? መቼም
ይህ የልብ ሐዘን እንጂ ሌላ አይደለም” አለኝ።
እኔም በጣም ፈርቼ ነበር፤ 3 ለንጉሡም
“ንጉሥ ለዘላለም ይኑር፤ አባቶቼ የተቀበሩባት
ከተማ ስትፈርስ፣ በሮቿም በእሳት ሲቃጠሉ
ለምን ፊቴ አይዘን?” አልሁት።
4 ንጉሡም፣ “ታዲያ ምን ትፈልጋለህ?” አለኝ።
ከዚያም ወደ ሰማይ አምላክ ጸለይሁ፤
5 ለንጉሡም፣ “ንጉሡን ደስ የሚያሰኘው ቢሆ
ንና ባሪያህ በፊትህ ሞገስ ቢያገኝ፣ እንደ
ገና እንድሠራት አባቶቼ ወደ ተቀበሩባት
ወደ ይሁዳ ከተማ እንድሄድ ይፈቀድልኝ”
አልሁት።
6 ከዚያም ንጉሡ አጠገቡ ከተቀመጠችው
ንግሥት ጋር በመሆን፣ “ጕዞህ ምን ያህል
ቀን ይፈጃል? መቼስ ትመለሳለህ?” ሲል ጠየ
ቀኝ። ንጉሡም እኔን ለመስደድ ደስ አለው፤
እኔም ጊዜውን ወሰንሁ።
7 ደግሞም እንዲህ አልሁት፤ “ንጉሡን ደስ
የሚያሰኘው ቢሆን፣ ይሁዳ እስክደርስ ድረስ
በደኅና እንዲያሳልፉኝ ከኤፍራጥስ ማዶ
ላሉት አገረ ገዦች ደብዳቤ ይሰጠኝ፤ 8 እንዲ
ሁም ለንጉሡ ደን ጠባቂ ለአሳፍ፣ በቤተ
መቅደሱ አጠገብ ላለው ግምብ በሮች፣
ለከተማዪቱ ቅጥርና እኔም ለምገባበት ቤት
ሠረገላ የሚሆን እንጨት እንዲሰጠኝ ደብዳቤ
ይጻፍልኝ፤” መልካሚቱ የአምላኬ እጅ በእኔ
ላይ ነበረችና ንጉሡም ፈቀደልኝ። 9 ስለዚህ
በኤፍራጥስ ማዶ ወደሚገኙት አገረ ገዦች
ሄጄ የንጉሡን ደብዳቤዎች ሰጠኋቸው፤ ንጉ
ሡም የጦር አለቆችና ፈረሰኞች አብረውኝ
እንዲሄዱ አድርጎ ነበር።
10 ሖሮናዊው ሰንባላጥና አሞናዊው ሹም
ጦብያ ይህን በሰሙ ጊዜ ስለ እስራኤላውያን

2፥1 ዕዝ4፥7፤6፥14
2፥3 1ነገ1፥31፤
ነህ1፥3፤ መዝ137፥6፤
ዳን2፥4፤ 3፥9፤
5፥10፤6፥6፡21
2፥6 ነህ5፥14፤13፥6
2፥7 ዕዝ8፥36፤
ዕዝ 4፥24፤5፥5፤
ነህ7፥2
2፥9 ዕዝ8፥22
2፥10 ቍ19፤ነህ4፥1፡
3፡7፤6፥1-2፡5፡12፡
14፤13፥4-7፡28፤
አስ10፥3

---

2፥1 *በሃያኛው ዓመት ኒሳን* መጋቢት/ሚያዝያ 444 ዓ.ቅ.ክ ማለት ነው (“የጊዜ ቅደም ተከተል በሚመለከት፤ ዕዝራ - ነህምያ” የሚለውን በገጽ 675 ይመ)። ነህምያ መጀመሪያ ወሬውን ከሰማበት (1፥1) ከካሌሉ ወር አንሥቶ ንጉሡ ፊት እስከ ቀረበበት እስከ ኒሳን ወር ድረስ፣ ለአራት ወራት ዘግይቶአል፤ ለዚህም የተለያዩ ምክንያቶች ቀርበዋል፦
(1) ንጉሡ በባቢሎን ወደሚገኘው የክረምት ቤተ መንግሥቱ ሄዶ ይሆናል፤ (2) ምናልባት ንጉሡ በጥሩ ሁኔታ ላይ አልነበረም ይሆናል፤ (3) ነህምያ በንጉሡ ዘንድ የተወደደ ቢሆንም እንኳ ተጣድፎ ከመጠየቅ ተቈጥቦ ነገሩን ለማጤን ጊዜ ወስዶ ይሆናል። *በፊቱ ዐዝኜ፤* የንጉሡ አገልጋዮች ምንም ዐይነት ችግር ቢኖርባቸውም፣ ችግራቸውን በልባቸው ይዘው ምን ጊዜም በንጉሡ ፊት ሲቀርቡ የደስታ ፊት ማሳየት ይጠበቅባቸው ነበር።

2፥3 *ንጉሡ ለዘላለም ይኑር፤* አንድ ሰው ንጉሥ ፊት ሲቀርብ የሚናገረው የተለመደ አባባል ነበር። *ከተማ፤* ነህምያ ኢየሩሳሌምን በስሟ አይጠራትም (ቍ 5 ይመ)፤ የዘመዶቹን መቃብር መደፈር ለንጉሡ አስቀድሞ በመግለጽ ዐዘኔታ ለማግኘት ያሰበ ይመስላል።

2፥4 *ወደ ሰማይ አምላክ ጸለይሁ፤* ነህምያ ለንጉሡ መልስ ከመስጠቱ በፊት፣ ወደ አምላኩ አጭር ጸሎት አቀረበ፤ በሚገጥመው ሁኔታ ውስጥ ሁሉ እግዚአብሔርን ለመጠየቅ በጸሎት መቅረብ፣ ከነህምያ አስደናቂ ባሕርያት አንዱ ነው (1፥4፤ 4፥4፡ 9፤ 5፥19፤ 6፥9፡ 14፤ 13፡ 14፤ 22፡ 29፡ 31)።

2፥6 *ንግሥት፤* ይህን ቃል ለመግለጽ የገባው የዕብራይስጡ ቃል ተጠቅሶ የሚገኘው እዚህ ላይና በመዝ 45፥9 (“የቤተ መንግሥት ሙሽራ”) ላይ ብቻ ነው። ቃሉ ከአካዳውያን ቋንቋ የተወሰደ ሲሆን ቃል በቃል ሲተረጐም፣ “የቤተ መንግሥት ሴት” ማለት ነው። በአረማይስጡ የዚህ ቃል አቻ በዳን 5፥2-3፡23 ላይ ብቻ ይገኛል፤ የተተረጐመውም “ሚስቶች” ተብሎ ነው። የአርጤክስስ ሚስት ስም ደማስጵያ መሆኑንና ንጉሡ ከእርሷ ሌላ ቢያንስ ሦስት ቁባቶች እንደ ነበሩት በአቻሜኒድ አደባባይ ይኖር የነበረው ክቴስያስ የተባለው ግሪካዊ ዘግቦአል። ደማስጵያም እንደ አስቴር በንጉሡ ዘንድ የነበራትን ሥልጣን ሳትጠቀምበት አልቀረችም (አስ 5)። የአቻሜኒድ አደባባይ ከንጉሣዊ ቤተ ሰብ የተገኙ ሴቶች ከፍተኛ ተጽዕኖ ያደርጉበት ስለ ነበር መልካም ስም አልነበረውም። በተለይ የንጉሥ ጠረክሲስ ባለቤትና የቀዳማዊ አርጠክሴስ እናት የነበረችው ጨካኟ አሜስትሪስ አምባገነን ነበረች። *ጕዞህ ምን ያህል ቀን ይፈጃል?* ነህምያ ፈቃድ የጠየቀው ለአጭር ጊዜ ሳይሆን አይቀርም፤ ሆኖም በኋላ አራዝሞታል። የይሁዳ አስተዳዳሪ ሳለ ዐሥራ ሁለት ዓመት እንደ ቈየ ከ5፥14 መገንዘብ እንችላለን። በንጉሥ አርጤክስስ ዘመነ መንግሥት በ32ኛው ዓመት፣ ነህምያ ያከናወነውን ለንጉሡ ለማስታወቅ ፋርስ ሄደ፤ ከዚያም ወደ ይሁዳ ተመልሶ ለሁለተኛ ጊዜ ሥራውን ቀጠለ (13፥6-7)።

2፥7 *ደብዳቤ፤* በተመሳሳይ ዘመን የተጻፈ አንድ ሰነድ፣ አራሜስ የተባለ በፋርስ ቤተ መንግሥት ይኖር የነበረ የግብፅ እንደ ራሴ፣ በሥሩ የነበረ አንድ መኰንን ወደ ግብፅ በሚመለስበት ጊዜ በጕዞው ምግብና መጠጥ እንዲያቀርቡለት የፋርስን ባለሥልጣኖች እንዳዘዘ ያሳያል። *ከኤፍራጥስ ማዶ፤* የዕዝ 4፥10 ማብ ይመ።

2፥8 *ደን፤* ዕብራይስጡ “ፓርዴስ” ይለዋል፤ ከጥንቱ የፋርስ ቋንቋ የተወሰደ ሲሆን፣ ትርጕሙም “የተከለለ” ማለት ነው፤ ውብ የመዝናኛ ስፍራን ያመለክታል፤ ይህ ቃል በሌላ ስፍራ በመክ 2፥5 “የመዝናኛ ስፍራዎች” እና በማሕ 4፥13 (“ሮማን”) ላይ ብቻ ይገኛል። በዚህ ስፍራ የገባው የግሪኩ ቃል (ሰብዓ ሊቃናት ትርጕም) “ፓራዴሶስ” የሚለው ነው። በብሉይና በአዲስ ኪዳን መካከል ባለው ዘመን ቃሉ የሞቱ ቅዱሳን የሚያርፉበትን ማለትም “ገነት”ን ማመልከት ጀመረ። በአዲስ ኪዳን ሦስት ጊዜ ብቻ ተጠቅሶ ይገኛል (ሉቃ 23፥43፤ 2ቆሮ 12፥4፤ ራእ 2፥7)። አንዳንዶች ይህ “የንጉሡ ደን” የሚገኘው በሊባኖስ ነው ይላሉ፤ ይህም ቦታ በዝግባና በጥድ ዛፎች የታወቀ ነበር (የመሳ 9፥15፤ ዕዝ 3፥7 ማብ ይመ)። ይበልጥ ቅቡል የሆነው ግን፣ ከኢየሩሳሌም በስተ ደቡብ ዐሥር ኪ.ሜ ርቀት ላይ ኤታም በተባለ ስፍራ የሚገኘውን የንጉሥ ሰሎሞንን ልዩ የአትክልት ስፍራ ያመለክታል የሚለው አስተያየት ነው። ለከተማዋ ቅጥር በሮች መሥሪያ ውድ የሆነውን የዝግባ እንጨት ከሊባኖስ ማስመጣቱ የሚከብድ በመሆኑ፣ አገር በቀል የሆኑትን የተለያዩ ዛፎች መጠቀሙ ይሻላል (ሆሴ 4፥13) *ግንብ፤* ይህ ግንብ ምናልባት ከቤተ መቅደሱ በስተ ሰሜን ታላቁ ሄሮድስ ካሠራው ከአንጦንያ ግንብ በፊት የነበረው ከፍተኛ ምሽግ ሳይሆን አይቀርም (ሐሥ 21፥34፡ 37፤ 22፥24 ይመ)።

2፥9 *የጦር አለቆችና ፈረሰኞች፤* ነህምያ የይሁዳ ገዥ ስለ ነበር በሚያስገርም አኳኋን በታጠቀ ሰራዊት ታጅቦ ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሶአል (የዕዝ 8፥22 ማብ ይመ)።

2፥10 *ሰንባላጥና፤* የባቢሎናውያን ስም ሲሆን ትርጕሙም፣ “ሲን ሕይወት ሰጠ” ማለት ነው፤ “ሲን” (ጨረቃ - አምላክ ነው)። *ሖሮናዊው፤* ይህ የሚያመለክተው ሰንባላጥ፣ (1) ከገሊላ ባሕር በስተ ምሥራቅ ከሚገኘው ከሐውራን መምጣቱን (ሕዝ 47፥16፡18)፤ (2) ከሞዓብ አገር ከሖሮናይም (ኤር 48፥34) መምጣቱን፤ 3) ወይም ይበልጥ የሚመስለው ከላይኛው ወይም ከታችኛው ቤት ሖሮን መምጣቱን ነው፤ እነዚህ ሁለት ከተሞች በሰሜን ምዕራብ በኩል ከኢየሩሳሌም 20 ኪ.ሜ ያህል ርቀው፣ ወደ ኢየሩሳሌም በሚወስደው አውራ ጐዳና ዳር ይገኙ ነበር (ኢያ 10፥10፤ 16፥3፡5)። ሰንባላጥ የነህምያ ተቀናቃኝ ነበር (ቍ 19፤4፥1፡7፤6፥1-2፡5፡12፡14፤13፥28)። እርሱም የሰማርያ አገረ ገዥ ነበር (ከ4፥1-2 ጋር ያነጻጽሩ)። በአምስተኛው ዓ.ቅ.ክ መጨረሻ ገደማ ለይሁዳው ገዥ ለበጎሃይ (ቢግቫይ) የተጻፈው አንድ የኤሌፋንታይ ፓፒረስ ጽሑፍ “ዲላያና ሻማያ፣ የሰማርያው ገዥ የሰንባላጥ ወንዶች ልጆች” የሚል ተገኝቶበታል። በአራተኛው ዓ.ቅ.ክ.

ደኅንነት የሚቈረቈር ሰው በመምጣቱ እጅግ ተበሳጩ::

**ነህምያ የኢየሩሳሌምን ቅጥሮች ተዘዋውሮ ተመለከተ**

[11]እኔም ወደ ኢየሩሳሌም ሄድሁ፤ በዚያም
ሦስት ቀን ከቈየሁ በኋላ፣ [12]ከጥቂት ሰዎች
ጋር በሌሊት ወጣሁ:: ለኢየሩሳሌም አደር
ገው ዘንድ እግዚአብሔር በልቤ ያኖረውን ነገር
ለማንም አልነገርሁም፤ ከተቀመጥሁበት እን
ስሳ በቀር ከእኔ ጋር ሌሎች እንስሳት አልነ
በሩም::
[13]በሌሊትም ወጥቼ በሸለቆው በር በኩል
አድርጌ ወደ ዘንዶው[u] የውሃ ጕድጓድና
ወደ ቆሻሻ መድፊያው በር ሄድሁ፤ የፈረሱ
ትንም የኢየሩሳሌምን ቅጥሮችና በእሳት
የወደሙትን በሮች ተመለከትሁ:: [14]ከዚያም
ወደ ውሃ ምንጭ በርና ወደ ንጉሡ ኵሬ
ሄድሁ፤ ይሁን እንጂ የተቀመጥሁብትን እንስሳ
ማሳለፍ የሚያስችል በቂ ቦታ አልነበረም::

2፥11 ዘፍ40፥13
2፥13 2ዜና26፥9፤ ነህ1፥3፤3፥13፤12፥31
2፥14 2ነገ18፥17፤ ነህ3፥15፤12፥37

[u]13 ወይም *ቀበሮ ወይም በለሱ*

የተጻፈ አንድ የፓፒረስ ጽሑፍ በ1962 ዓ.ም. ከኢያሪኮ በስተ ሰሜን ዋሻ ውስጥ ተገኝቶአል፤ በጽሑፉ ውስጥ ከሰፈሩት የስም ዝርዝሮች መካከል የሰንባላጥም ስም አለ፤ ምናልባት ይህ ሰው በነህምያ ዘመን ከነበሩ ሰዎች የአንዱ ልጅ ሊሆን ይችላል:: *አሞናዊው፤* ዕዝ 9፥1 እንዲሁም፤ የዘፍ 19፥33 ማብ ይመ:: ምናልባት ጦብያ በፋርስ ሹማምት ሥር ሆኖ ከዮርዳኖስ ማዶ የነበረውን አካባቢ ሳያስተዳድር አልቀረም:: ከዚያ በኋላ በነበሩት ዘመናት በጦብያ ስም የሚጠራ አንድ ቤተ ሰብ በአሞን ግዛት ይኖር እንደ ነበር ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ ያሉ ምንጮች ያመለክታሉ:: *ጦብያ፤* የስሙ ትርጕም፣ "እግዚአብሔር መልካም ነው" ማለት ሲሆን፣ ምናልባት *እግዚአብሔርን* ሲያመልክ የቈየ ሰው ሳይሆን አይቀርም፤ ይህን ለማለት የሚያስደፍረው የስሙ ትርጕም ብቻ ሳይሆን የልጁም ስም ጭምር ነው:: የልጁ ስም ይሆሐናን ሲሆን (6፥17-18)፣ ትርጕሙ "*እግዚአብሔር* ቸር ነው" ማለት ነው:: ይሆሐናን ቅጥሩን ከሚሠሩት ሰዎች የአንዱ ቡድን መሪ የነበረውን የበራክያን ልጅ የሜሱላምን ሴት ልጅ አግብቶአት ነበር (3፥4:30፤ 6፥18):: ጦብያ ከካህኑ ከኤልያሴብ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ነበረው (13፥4-7):: *እጅግ ተበሳጩ፤* የሰንባላጥና የጦቢያ ተቃውሞ መሠረቱ ፖለቲካዊ እንጂ ሃይማኖታዊ አይደለም:: የነህምያ ወደ ኢየሩሳሌም መምጣት የሰማርያውን ገዥ ሥልጣን ችግር ላይ ሳይጥለው አልቀረም::

2፥11 *ሦስት ቀን፤* የዕዝ 8፥32 ማብ ይመ::


2፥12፤ ነህምያ የከተማዋን ቅጥር እየዞረ በተመለከተ ጊዜ ከፍተኛ ጥንቃቄና ምርመራ አድርጎአል:: *ከተቀመጥሁበት፤* በበቅሎ ወይም አህያ ሊሆን ይችላል::

2፥13፤ ነህምያ በስተ ደቡብ ያለውን ክፍል (*ከዚህ በታች ያለውን ካርታ ይመ*) ብቻ እንጂ የከተማዋን ቅጥር ሙሉ በሙሉ ዞሮ አላየም፤ ኢየሩሳሌም በሰሜን በኩል ለጠላት የተጋለጠች በመሆኗ፣ አብዛኛውን ጊዜ ጥቃት የሚደርስባት በዚያው በኩል ነበር፤ በዚያ ክፍል ያለው የከተማዋ ቅጥር *ሙሉ በሙሉ* የወደመውም ከዚህ የተነሣ ሳይሆን አይቀርም:: *በሸለቆው በር፤* 3፥13 ይመ:: በ2ዜና 26፥9 *መሠረት፣* ዖዝያን በምዕራቡ በኩል ባለው የከተማዋ ቅጥር ላይ ማማዎች ሠርቶ ነበር፤ ይህም ማማ በሄኖምና በቄድሮን ሸለቆች መካከል ያለውን ከጢሮጳን ሸለቆ ባሻገር የሚያሳይ ነበር:: በ1927-28 ዓ.ም. በተደረገው የሥነ ቅርስ ጥናት ቍፋሮ፣ በፋርስ ዘመን የነበረ አንድ ያረጀ በር ተገኝቶአል፤ ይህም የሸለቆው በር እንደ ሆነ ታውቆአል:: *ወደ ዘንዶው የውሃ ጕድጓድ፤* ብዙ ምሁራን ይህ ቦታ በአሁኑ ጊዜ ኤንሮጌል ተብሎ የሚጠራው ነው ይላሉ (ኢሱ 15፥7-8፤ 18፥16፤ 2ሳሙ 17፥17፤ 1ነገ 1፥9)፤ ይህ የውሃ ጕድጓድ የሄኖምና የቄድሮን ሸለቆዎች በሚገናኙበት ቦታ፣ ከኢየሩሳሌም ደቡብ ምሥራቃዊ ጫፍ 227 ሜትር ያህል ርቆ የሚገኝ ነው:: ሌሎች ደግሞ የሰሊሆም መጠመቂያ ነበር ይላሉ:: *ቆሻሻ መድፊያው በር፤* ምናልባት በሄኖም ሸለቆ ወዳለው ቆሻሻ መጣያ ስፍራ የሚወስደው በር ሊሆን ይችላል (ከ3፥13-14፤ 12፥31፤ ከ2ነገ 23፥10 ጋር ያነጻጽሩ):: ከሸለቆ በር በስተ ደቡብ 445 ሜትር ያህል ይርቅ ነበር (3፥13)::

2፥14 *ውሃ ምንጭ በር፤* በኤንሮጌል ትይዩ (3፥15፤ 12፥37 ይመ) ባለው የደቡብ ምሥራቅ ቅጥር ውስጥ የሚገኝ ሳይሆን አይቀርም:: *ንጉሡ ኵሬ፤* ሕዝቅያስ ከከተማዋ ቅጥር ውጭ በቄድሮንና በሄኖም ሸለቆዎች መገናኛ ላይ የሚገኘው የቤተ መንግሥቱ እርሻ ውሃ እንዲያገኝ ያደረገው (ከ2ነገ 25፥4)፣ ከሰሊሆም ቦይ ሞልቶ የሚፈሰውን ውሃ (ከ2ዜና 32፥30 ጋር ያነጻጽሩ) ጠልፎ በመውሰድ ሳይሆን አይቀርም:: ስለዚህ የንጉሡ ኵሬ የተባለው ምናልባት የሰሊሆም መጠመቂያ (3፥15) ወይም በአጠገቡ ያለው ቢርኬት ኤል ሐምራ የተባለው ሊሆን ይችላል:: *በቂ ቦታ አልነበረም፤* ይህ ችግር የተፈጠረው ከከተማዋ በስተ ምሥራቅ የነበረው የተራራ ላይ እርከን ስለ ተናደ ሊሆን ይችላል (ከ2ሳሙ 5፥9፤ 1ነገ 9፥15:24 ጋር ያነጻጽሩ)::

**ኢየሩሳሌም ከምርኮ መመለስ በኋላ**
**(ዓ.ቅ.ክ 458 በኋላ)**

በምሥራቁ በኩል ከፍ ያለ ቅጥር ያላት አነስተኛ ከተማ እንደገና ተሠራች:: በቤተ መቅደስ የሚደረገው አምልኮ ቀድሞ በነበረው ስፍራ እንደ ገና በተሠራው መቅደስ ቀጠለ:: በምዕራብ በኩል ያለው ቅጥር ሥራም ተጀምሮ ይሆናል::



15ስለዚህ ቅጥሩን እየተመለከትሁ ሌሊቱን
ሸለቆውን ዐልፌ ወደ ላይ ወጣሁ፤ በመጨ
ረሻም ተመልሼ በሸለቆው በር በኩል ገባሁ።
16ለአይሁድ ወይም ለካህናቱ ወይም ለመኳ
ንንቱ ወይም ለሹማምቱ ወይም ሥራውን
ለሚሠሩት ሰዎች ገና ምንም የተናገርሁት
ነገር ስላልነበረ፣ ወዴት እንደ ሄድሁ ወይም
ምን እንዳደረግሁ ሹማምቱ አላወቁም።
17ከዚያም፣ "ያለንበትን ችግር ይኸው ታያ
ላችሁ፤ ኢየሩሳሌም ፈርሳለች፤ በሮቿም በእ
ሳት ጋይተዋል፤ አሁንም ኑና የኢየሩሳሌምን
ቅጥር እንደ ገና እንሥራ፤ ከእንግዲህስ
መሣለቂያ አንሆንም አልኋቸው። 18እንዲሁም
መልካሚቱ የአምላኬ እጅ በእኔ ላይ እንደ
ነበረችና ንጉሡም ምን እንዳለኝ ነገርኋቸው።
እነርሱም፣ "እንደ ገና መሥራቱን እን
ጀምር!" ካሉ በኋላ ይህን መልካም ሥራ
ጀመሩ።
19ነገር ግን ሖሮናዊው ሰንባላጥ፣ አሞና
ዊው ሹም ጦብያና ዐረባዊው ጌሳም ይህን
ሲሰሙ አፌዙብን፤ አንቋሸሹንም፤ እንዲሁም፣
"የምታደርጉት ይህ ምንድን ነው? በንጉሡ
ላይ ልታምፁ ትፈልጋላችሁን?" አሉ።
20እኔም፣ "የሰማይ አምላክ ያከናውንልናል፤
እኛ ባርያዎቹ እንደ ገና ሥራውን እንጀምራለን፤

2፥17 ነህ1፥3፤ መዝ102፥16፤ ኢሳ30፥13፤58፥12፤ ሕዝ5፥14
2፥18 ዕዝ5፥5
2፥19 ቍ10፤ ነህ6፥1:2:6፤ መዝ44፥13-16
2፥20 ዕዝ4፥1:3፤ ሐሥ8፥21
3፥1 ቍ32፤ ዕዝ10፥24፤ ነህ12፥39፤ መዝ48፥12፤ ኢሳ58፥12፤ ኤር31፥38፤ ዘካ14፥10፤ዮሐ5፥2
3፥2 ነህ7፥36
3፥3 2ዜና33፥14
3፥4 ዕዝ8፥33
3፥5 ቍ27፤2ሳሙ14፥2

እናንተ ግን በኢየሩሳሌም ድርሻ ወይም
ይገባናል የምትሉት ወይም የታሪክ መታሰ
ቢያ የላችሁም" ስል መለስሁላቸው።

## የቅጥሩ ሠራተኞች

3ሊቀ ካህናቱ ኤልያሴብና ወንድሞቹ
ካህናት ለሥራ ተነሡ፤ የበጎች በር የተ
ባለውንም እንደ ገና ሠሩ። ቀደሱት፤ መዝ
ጊያዎቹንም በየቦታቸው ላይ አቆሙ። መቶ
ማማ እስከሚባለው ግንብና ሐናንኤል ማማ
ተብሎ እስከ ሚጠራው ድረስ ሠርተው ቀደ
ሱት፤ 2ቀጥሎ ያለውንም የኢያሪኮ ሰዎች
ሠሩ፤ እነርሱ ከሠሩት ቀጥሎ ደግሞ የአምሪ
ልጅ ዘኩር ሠራ።
3የዓሣ በሩን የሃስናአ ልጆች ሠሩ፤ እነርሱም
ምሰሶዎቹን አቁመው መዝጊያዎቹን፣ መቀ
ርቀሪያዎቹንና መወርወሪያዎቹን በየቦታቸው
አኖሩ።
4የአቆስ ልጅ የኦርዮ ልጅ ሜሪሞት ከዚያ
ቀጥሎ ያለውን ክፍል መልሶ ሠራ። ከእርሱ
ቀጥሎ ያለውን የሜሴዜቤል ልጅ የበራክያ
ልጅ ሜሱላም መልሶ ሠራ። ከእርሱ ቀጥሎ
ያለውን የበዓና ልጅ ሳዶቅ መልሶ ሠራ፤
5የሚቀጥለውን ክፍል የቴቁሐ ሰዎች መል
ሰው ሠሩ፤ መኳንንቶቻቸው ግን በተቈጣጣሪ

2፥15 *ሸለቆውን*፤ የቄድሮን ሸለቆ ነው።

2፥16 *መኳንንቱ*፤ የዕብራይስጡ ቃል ትርጕም "ነጻ" ማለት ነው (4፥14:19፤5፥7፤6፥17፤7፥5፤13፥17 እና የ3፥5 ማብ ይመ)።

2፥17 *ፈርሳለች*፤ በ586 ዓ.ቅ.ክ. ናቡከደነፆር ቅጥሯንና በሮቿን ካፈረሰ በኋላ ከተማዪቱ የነበረችበትን ሁኔታ የሚያመለክት ነው፤ የፈረሰውን ቅጥርና በር መልሶ ለመገንባት ጥረት ቢደረግም ሳይሳካ ቀርቶአል። መሪዎችና ሕዝቡ ለዚህ አሳዛኝ ሁኔታ ደንታ አልነበራቸውም። የነበረውን ሁኔታ ለመገምገምና የፈራረሰውን መልሶ ለመገንባት የውጭ ድጋፍ አስፈልጓቸው ነበር።

2፥18 *የአምላኬ ... ንጉሡም*፤ ነህምያ ሕያው እግዚአብሔር አብሮት የሚሠራ እንደ ሆነና የንጉሡን ፈቃድና ሥልጣን አግኝቶ እንደ መጣ በግሉ መመስከሩን ያመለክታል።

2፥19 *ሰንባላጥ ... ጦብያ*፤ የቍ10 ማብ ይመ። *ጌሳም*፤ በሰሜን ምዕራብ ዐረብያ ዴዳን ከተባለ ቦታ እንዲሁም በግብፅ አገር ከእስማኤልያ አጠገብ ቴል ኤል ማስኩታህ በተባለ ቦታ የተገኙ ጽሑፎች ጌሳም የሚል ስም ተጠቅሶባቸው ይገኛል፤ ይህ ሰው ከሰሜን ምሥራቅ ግብፅ ጀምሮ እስከ ሰሜናዊው ዐረብያና እስከ ደቡባዊው ፓለስቲና የሚያጠቃልለውን ሰፊ የሰሜን ዐረብያ ግዛት ያስተዳደረ ሳይሆን አይቀርም። ጌሳም ነህምያን የተቃወመው ራሷን የቻለች ነጻ አገር ለማቋቋም ጥረት እያደረገና ምናልባትም ትርፍ የማገኝበትን የቅመማ ቅመም ንግድ ያቃውስብኛል በማለት ሠግቶ ይሆናል። *ዐረባዊው*፤ 2ዜና 9፥14፤ ኢሳ 21፥13፤ ኤር 25፥24 ይመ። ዐረቦች ከአሦራውያን ዘመን አንሥቶ እስከ ፋርሶች ዘመን ድረስ ከዮርዳኖስ ወንዝ ማዶ ባለው አገር ላይ ገናና ሆነው ነበር። የአሦር ንጉሥ ዳግማዊ ሳርጎን በ715 ዓ.ቅ.ክ ጥቂት ዐረቦችን በሰማርያ እንዲሰፍሩ አድርጎ አል። ዐረቦች በፋርሶች ግዛት ሥር በነበሩበት ጊዜ መብታቸው ተጠብቆላቸው ይኖሩ እንደ ነበር ጥንታውያን ጽሑፎች ያስረዳሉ።

3፥1-32፤ ይህ ምዕራፍ የኢየሩሳሌምን ከተማ መልክዐ ምድራዊ አቀማመጥ በሚገባ ለማወቅ ከሚረዱት የብሉይ ኪዳን ክፍሎች አንዱ ነው። ታሪኩ በከተማዋ ሰሜን ምሥራቅ ማእዘን ከሚገኘው ከበጎች በር ይጀምርና በሰሜን አድርጎ በምዕራብ በኩል በቅጥሩ ዙሪያ ያለውን ሁሉ የሚገልጽ ነው። አርባ አምስት ያህል ምድብ ባሉት ቅጥሩን መልሶ የመገንባት ሥራ ውስጥ የተሳተፉ አርባ የሚሆኑ ዋና ዋና ሰዎች ተጠቅሰዋል። የግንባታው ሠራተኞች መኖሪያ ናቸው ተብለው የተመዘገቡት ከተሞች የይሁዳን አውራጃ የአስተዳደር ማዕከሎች የሚወክሉ ሊሆኑ ይችላሉ። ዐሥር በሮች ስማቸው ተጠቅሶአል፤ እነዚህም፤ (1) የበጎች በር (ቍ 1)፤ (2) የዓሣ በር (ቍ 3)፤ (3) አሮጌው በር (ቍ 6)፤ (4) የሸለቆ በር (ቍ 13)፤ (5) የቈሻሻ መጣያ በር (ቍ 14)፤ (6) የምንጭ በር (ቍ 15)፤ (7) የውሃ በር (ቍ 26)፤ (8) የፈረስ በር (ቍ 28)፤ (9) የምሥራቅ በር (ቍ 29)፤ (10) መቈጣጠሪያ በር (ቍ 31) ነበሩ። የዕድሳቱ ሥራ በአብዛኛው የጠላት ጥቃት በበረታበት በቅጥሩ በር ላይ ያተኰረ መሆኑን ዘገባው ይጠቁማል። ይኸውም በኢየሩሳሌም ቅጥርና ሕንጻዎች ላይ የደረሰው ጕዳት እኩል ነበር ማለት አይደለም። ጠላት ጥቃት የሚያደርሰው ቦታ እየለየ እንደ ነበር በ2ነገ 25፥9 ላይ ተመልክቶአል።

3፥1 *ሊቀ ካህናቱ ኤልያሴብና*፤ ሊቀ ካህናቱ በሥራው ቀዳሚ ሆኖ አርአያነቱን ማሳየቱ ተገቢ ነበር። በጥንት ሱሜራውያን ዘንድ አንድ ቤተ ጣዖት በሚሠራበት ጊዜ ንጉሡ ራሱ ጡብ ተሸክሞ በመውሰድ የሥራው ተሳታፊ መሆኑን መግለጽ የተለመደ ነበር። *የበጎች በር*፤ ቍ 32፤ 12፥39 ይመ። ይህም በአዲስ ኪዳን ዘመን የታወቀ ሲሆን (ዮሐ 5፥2)፣ የሚገኘውም በኢየሩሳሌም ሰሜን ምሥራቅ ማእዘን በኩል በቤተሳይዳ መጠመቂያ አጠገብ ነበር። በአሁኑ ጊዜ እንኳ በዚሁ ስፍራ የደራ የበግ ገበያ ይካሄዳል። አሁን የበጎች በር የተባለው ቀደም ሲል የብንያም በር የተባለውን ሳይተካ አልቀረም (ኤር 37፥13፤ 38፥7፤ ዘካ 14፥10)። *መቶ ማማ*፤ 12፥39 ይመ። "መቶ" የሚለው ምናልባት (1) ከፍታውን (መቶ ክንድ ያህል መሆኑን)፤ 2) የመወጣጫ ደረጃውን ብዛት፤ ወይም (3) አንድ ወታደራዊ ክፍልን (ከዘዳ 1፥15 ጋር ያነጻጽሩ) ሊያመለክት ይችላል። *የ ... ሐናንኤል ማማ*፤ ማማዎቹ በሰሜን በኩል ለጥቃት የተጋለጠውን የከተማዪቱን ክፍል በመጠበቅ አንጻር፣ በቤተ መቅደሱ አጠገብ ካለው ግንብ ጋር (2፥8) ተመሳሳይነት አላቸው።

3፥3 *የዓሣ በሩን*፤ 12፥39 ይመ። የመጀመሪያው ቤተ መቅደስ በነበረበት ዘመን፣ ይህ በር ወደ ኢየሩሳሌም ከሚያስገቡት ዋና በሮች አንዱ ነበር (2ዜና 33፥14፤ ሶፎ 1፥10)። ነጋዴዎች ከጢሮስ ከተማ ወይም ከገሊላ ባሕር ዓሣ አምጥተው በዚህ በር በኩል ለገበያ ያቀርቡ ነበር (13፥16)፤ ይህ በር በአሁኑ ጊዜ የደማስቆ በር በሚባለው ቦታ አቅራቢያ የሚገኝ ሳይሆን አይቀርም።

3፥4 *ሜሪሞት*፤ የዕዝ 8፥33 ማብ ይመ። *ሜሱላም*፤ ሁለተኛውን ክፍል አድሶአል (ቍ 30)። ሴት ልጁን ለጦብያ ልጅ በመዳሩ ነህምያ በሜሱላም ላይ ቅሬታ ነበረው (6፥17-18 እና የ2፥10 ማብ ይመ)።

3፥5 *ቴቁሐ*፤ ከቤተ ልሔም በስተ ደቡብ 10 ኪ.ሜ.፣ ከኢየሩሳሌም ደግሞ 18 ኪ.ሜ ያህል ርቃ የምትገኝ አነስተኛ ከተማ ስትሆን፣ የነቢዩ የአሞጽ የትውልድ ስፍራ ናት (አሞ 1፥1)። *መኳንንታቸው*፤ የዕብራይስጡ ቃል በ2፥16 ላይ ካለው የተለየ

ኣሠሪዎቻቸው[ሀ] ሥር ሆነው በሥራው መጠ
መድ አልፈለጉም::
6አሮጌውን[ለ] በር የፋሴሐ ልጅ ዮዳሄና
የበሶድያ ልጅ ሜሱላም መልሰው ሠሩ፤ እነ
ርሱም ምሰሶዎቹን አቁመው መዝጊያዎቹን፣
ማያያዣዎቹንና መወርወሪያዎቹን በየቦታ
ቸው አኖሩ:: 7ከእነርሱም ቀጥሎ የዕድሳቱ
ሥራ የተከናወነው በኤፍራጥስ ማዶ በሚገ
ኘው አገረ ገዥ ሥልጣን ሥር ባሉት በገባ
ዖንና በምጽጳ ሰዎች በገባዖናዊው በመል
ጥያና በሜሮኖታዊው በያዶን ነበር:: 8ከወ
ርቅ አንጥረኞች አንዱ የሆነው የሐርሃያ
ልጅ ዑዝኤል የሚቀጥለውን ክፍል ሠራ፤
ከሽቱ ቀማሚዎች አንዱ የሆነው ሐናንያ
ደግሞ ከዚያ ቀጥሎ ያለውን መልሶ ሠራ::
እነርሱም "ሰፊው ቅጥር" ተብሎ እስከሚጠ
ራው ድረስ ኢየሩሳሌምን መልሰው ሠሩ::
9ከዚያ የሚቀጥለውን ክፍል የኢየሩሳሌም
አውራጃ እኩሌታ ገዥ የሆነው የሆር ልጅ
ረፋያ መልሶ ሠራ:: 10የኤርማፍ ልጅ ይዳያ
ከቤቱ ፊት ለፊት ያለውን ክፍል መልሶ
ሠራ፤ የአሰበንያ ልጅ ሐጡስ ደግሞ ከእ
ርሱ ቀጥሎ ያለውን መልሶ ሠራ:: 11የካሪም
ልጅ መልኪያና የፈሐት ሞዓብ ልጅ አሱብ
ሌላውን ክፍልና "የእቶን ግንብ" ተብሎ
የሚጠራውን መልሰው ሠሩ:: 12የኢየሩሳ
ሌም አውራጃ እኩሌታ ገዥ የሆነው የአጠ
ሎኤስ ልጅ ሰሎም ከሴት ልጆቹ ጋር በመ
ሆን ቀጥሎ ያለውን ክፍል መልሶ ሠራ::
13"የሸለቆ በር" ተብሎ የሚጠራውን የሐ
ኖንና የዛኖ ነዋሪዎች ዐደሱት፤ መልሰው
ሠሩት፤ ከሠሩትም በኋላ መዝጊያዎቹን በየ
ቦታቸው አኖሩ፤ መወርወሪያዎቹንና መቀር
ቀሪያዎቹንም አበጁ:: እንዲሁም "የቆሻሻ
መጣያ በር" ተብሎ እስከሚጠራው ድረስ
ያለውን አንድ ሺህ ክንድ[ሐ] ቅጥር መልሰው
ሠሩ::
14"የቈሻሻ መጣያ በር" ተብሎ የሚጠራው
የቤት ሐካሪም አውራጃ ገዥ የሆነው የሬካብ
ልጅ መልኪያ መልሶ ሠራ፤ መልሶ ከሠራ
በኋላም መዝጊያዎቹን፣ መቀርቀሪያዎቹንና
መወርወሪያዎቹን በየቦታቸው አኖረ::
15የምጽጳ አውራጃ የኮልሖዜ ልጅ ሰሎም
"የምንጭ በር" ተብሎ የሚጠራውን መልሶ
ሠራ፤ መልሶ ከሠራም በኋላ ከድኖ መዝጊ
ያዎቹን በየቦታቸው አኖረ፤ መወርወሪያዎቹ
ንና መቀርቀሪያዎቹንም አበጀ:: "የንጉሥ
አትክልት ቦታ" ተብሎ በሚጠራው አጠገብ
የሚገኘውን የሺላን መዋኛ ግንቡም፣ ከዳዊት
ከተማ ጀምሮ ቍልቍል እስከሚወርደው ደረጃ
ድረስ መልሶ ሠራ:: 16ከእርሱም በኋላ የቤት
ጹር አውራጃ እኩሌታ ገዥ የዓዝቡቅ ልጅ
ነህምያ እስከ ዳዊት መቃብር ትይዩ እስከ
ሰው ሠራሹ ኵሬና "የጀግኖች ቤት" ተብሎ
እስከሚጠራው ድረስ ያለውን መልሶ ሠራ::
17ከእርሱ ቀጥሎ ሌዋውያኑ በባኒ ልጅ
በሬሁ ሥር ሆነው የዕድሳት ሥራ ሠሩ::

3፥6 ነህ12፥39
3፥7 ኢሳ9፥3
3፥8 ነህ12፥38
3፥11 ነህ12፥38
3፥13 ኢሱ 15፥34፤ 2ዜና26፥9፤ነህ2፥13
3፥14 ኤር6፥1
3፥15 ኢሳ8፥6፤ ዮሐ9፥7
3፥16 ኢሱ15፥58፤ ሐሥ2፥29
3፥17 ኢሱ15፥44

[ሀ]5 *ጌቶቻቸው፤ ወይም ገዦቻቸው*
[ለ]6 *ወይም የይሻናን*
[ሐ]13 450 ሜትር ያህል ነው::

ነው (የዚያኑ ክፍል ማብ ይመ)፤ ትርጕሙም፣ "ኀያል" ወይም "ባለ ግርማ" ማለት ነው (10፥29፤ 2ዜና 23፥20፤ ኤር 14፥3 ይመ):: እነዚህ ባላባቶች የጕልበት ሥራ የሚንቁ ነበሩ (ኤር 27፥12)::

3፥6 ***አሮጌውን በር***፤ በሰሜን ምዕራብ ማእዘን በይሁዳና በሰማርያ ድንበር ላይ የሚገኝ የይሻናህ በር (2ዜና 13፥19) ወይም የሚሽና በር ("ዐዲስ ሰፈር" ለሚለው የዕብራይስጥ ቃል፤ ሶፎ 1፥10) ሊሆን ይችላል:: ያም ሆነ ይሀ፣ "የኤፍሬም በር" ለተባለው የተሰጠ ሌላ ስም ሳይሆን አይቀርም (12፥39 ይመ)፤ ይህም በም 3 ውስጥ ከዚህ በስተቀር በሌላ ቦታ አልተጠቀሰም::

3፥7 ***ሥልጣን*** ቃል በቃል ሲተረጐም "ዙፋን" ማለት ሲሆን፣ ይህም ሥልጣንን ያመለክታል::

3፥8 ***ከወርቅ አንጥረኞች፣*** ቍ 31–32 ይመ:: ***ከሽቱ ቀማሚዎች፣*** 1ሳሙ 8፥13 ይመ:: ***ሰፊው ቅጥር፤*** 12፥38 ይመ:: ከ1970-71 ዓ.ም. በኢየሩሳሌም በተደረገው የሥነ ቅርስ ቍፋሮ፣ እንደዚህ ያለ ቅጥር በቤተ መቅደሱ ግቢ በምዕራብ በኩል ተገኝ ቶአል:: ቅጥሩም በሰባተኛው ዓ.ቅ.ክ. በንጉሥ ሕዝቅያስ እንደ ተገነባ (2ዜና 32፥5) ይገመታል:: ከተማዪቱ እስከ ሰፊው ቅጥር ድረስና ከዚያም ዐልፋ እንድትስፋፋ ያስፈለገበት ምክንያት ሰማ ርያ በ722-721 ዓ.ቅ.ክ በወደቀች ጊዜ ብዙ ስደተኞች ሸሽተው ወደ ከተማዪቱ በመግባታቸው ሳይሆን አይቀርም::

3፥10 ***ይዳያ ከቤቱ ፊት ለፊት ያለውን ክፍል መልሶ ሠራ፤*** ቍ 23፡28-30 ይመ:: እርሱና ሌሎቹም ሰዎች ለየቤታ ቸው የሚቀርበውን የቅጥሩን ክፍል እንዲጠግኑ ማድረጉ ተገቢ ነበር::

3፥11 ***የእቶን ግንብ፣*** ይህ ግንብ በምዕራብ በኩል የሚገኘው ሲሆን ዖዝያን ቀደም ሲል በገነባበት (2ዜና 26፥9) ቦታ ላይ የተሠራ ሳይሆን አይቀርም:: የተጠቀሰው እቶን፣ "የጋጋሪዎች ሰፈር" (ኤር 37፥21) ተብሎ በሚጠራው ጐዳና ላይ የነበረ ሳይሆን አይቀርም::

3፥12 ***ከሴት ልጆቹ፤*** በቅጥሩ ሥራ ላይ ሴቶች መሰማራ ታቸውን የሚገልጽ ነው:: የአቴና ሰዎች ከተሞቻቸው በፋርሶች ከወደመ በኋላ መልሰው ለመገንባት ሲነሡ፣ "የከተማው ነዋሪዎች በሙሉ ወንድ፣ ሴት፣ ሕፃን ሳይቀር በቅጥሩ የዕድሳት ሥራ ላይ እንዲሰማሩ" ዐዋጅ ወጥቶ ነበር (ቱሲዲዲስ፣ 1.90.3)::

3፥13 ***የሸለቆ በር፤*** የ2፥13 ማብ ይመ:: ***አንድ ሺህ ክንድ፤*** ከመጠን በላይ ረጅም በመሆኑ፣ ምናልባት አብዛኛው ክፍሉ አልተነካ ይሆናል:: ***የቈሻሻ መጣያ በር፣*** የ2፥13 ማብ ይመ::

3፥14 ***የቤት ሐካሪም፤*** "የወይን እርሻ ቤት" ማለት ነው:: ይህ ቦታ የእሳት ምልክት የሚደረግበት ስፍራ ሲሆን (ኤር 6፥1)፣ ከኢየሩሳሌም በስተ ደቡብ ሦስት ኪ.ሜ. ያህል ርቃ ከምትገኘው ራማት ራሔል ጋር አንድ ነው:: በፋርስ ዘመነ መንግሥት የአንድ አውራጃ ገዥ መኖሪያ ሳይሆን አይቀርም::

3፥15 ***የምንጭ በር፤*** የ2፥14 ማብ ይመ:: ***የሺላን መዋኛ፣*** ምናልባት በኢሳ 22፥9 የተገለጸው "የታችኛው ኵሬ" ይሆናል (የኢሳ 8፥6 ማብ ይመ):: ***የንጉሥ አትክልት ቦታ፣*** የ2፥14 ማብ ይመ:: ***ከዳዊት ከተማ፣*** 12፥37 ይመ፤ እንዲሁም የ2ሳሙ 5፥7 ማብ ይመ::

3፥16 ***ቤትጹር፤*** ከኢየሩሳሌም በስተ ደቡብ ሃያ ኪ.ሜ. ላይ የምትገኝ የአውራጃ ዋና ከተማ ነበረች:: በፋርስ ዘመነ መንግሥት መጀመሪያ ላይ የዚህች ከተማ ሕዝብ ብዛት አነስተኛ እንደ ነበር፣ ከአምስተኛው ዓ.ቅ.ክ. ጀምሮ ግን እየጨ መረ መሄዱን በ1931 እና 1957 ዓ.ም. የተደረገው የሥነ ቅርስ ቍፋሮ ያመለክታል:: ***ዳዊት መቃብር፣*** ከ2፥5 ጋር ያነጻጽሩ:: ዳዊት የተቀበረው በከተማዪቱ ውስጥ ነበር (1ነገ 2፥10፤ 2ዜና 21፥20፤ 32፥33፤ ሐሥ 2፥29):: ይህ በጽዮን ተራራ ላይ የሚገኘው የዳዊት መቃብር እየተባለ የሚጠራውና በአሁኑ ጊዜ በአይሁድ ተሳላሚዎች በየጊዜው የሚጐበኘው ይህ ስፍራ በ14ኛው ምእተ ዓመት በተገነባው ከናኩለም በተባለው ሕንጻ ውስጥ ይገ ኛል:: የዳዊትን መቃብር በተመለከተ እንዲህ ያለ ቦታ ስለ መኖሩ ከዘጠነኛው ምእተ ዓመት በፊት የሚታወቅ ነገር የለም:: ***የጀግኖች ቤት፤*** ምናልባት የንጉሥ ዳዊት ኀያላን የሚኖሩበት ቤት ሳይሆን አይቀርም (2ሳሙ 23፥8-39 ይመ)፤ ከጊዜ በኋላ ግን የወታደሮች መኖሪያ ሳይሆን አልቀረም::

3፥17-18 ***ቅዒላ፣*** ከኢየሩሳሌም በስተ ደቡብ ምዕራብ 24 ኪ.ሜ. ያህል ርቃ የምትገኝ ከተማ ነበረች፤ ይህችም ከተማ በዳ

ከእርሱ ቀጥሎ የቅዒላ አውራጃ እኩሌታ
ገዥ ሐሸብያ አውራጃውን መልሶ ሠራ::
18ከእርሱ ቀጥሎ ያለውን ክፍል ደግሞ የሌላው
የቅዒላ አውራጃ እኩሌታ ገዥ የኤንሐዳድ
ልጅ በዋይና በእርሱም ሥር የነበሩት የአ
ገሩ ሰዎች መልሰው ሠሩ:: 19ከእርሱም ቀጥሎ
ወደ ጦር መሣሪያ ግምጃ ቤት በሚያወጣውና
እስከ ማእዘኑ በሚደርሰው ትይዩ ያለውን
ሌላ ክፍል የምጽጳ ገዥ የኢያሱ ልጅ ኤጽር
መልሶ ሠራ:: 20ከእርሱም ቀጥሎ የዘባይ
ልጅ ባሮክ ከማእዘኑ ጀምሮ እስከ ሊቀ
ካህኑ እስከ ኤልያሴብ ቤት መግቢያ ያለ
ውን ሌላ ክፍል በትጋት መልሶ ሠራ::
21ከእርሱ ቀጥሎ ከኤልያሴብ ቤት መግቢያ
ጀምሮ እስከ መጨረሻው ያለውን ሌላ
ክፍል የአቆስ ልጅ የኦርዮ ልጅ ሜሪሞት
መልሶ ሠራ::

22ከእርሱም ቀጥሎ ያለውን ክፍል ከአካ
ባቢው የመጡት ካህናት መልሰው ሠሩ::
23ከእነርሱ ቀጥሎ ብንያምና አሱብ ከቤታ
ቸው ፊት ለፊት ያለውን መልሰው ሠሩ፤
ከእነርሱም ቀጥሎ የሐናንያ ልጅ የመዕሤያ
ልጅ ዓዛርያስ በቤቱ አጠገብ ያለውን መልሶ
ሠራ:: 24ከእርሱም ቀጥሎ ከዓዛርያስ ቤት
ጀምሮ እስከ ማዕዘኑና እስከ ማዕዘኑም ጫፍ
ያለውን ሌላውን ክፍል የኤንሐደድ ልጅ
ቢንዊ መልሶ ሠራ፤ 25የኡዛይ ልጅ ፋላል
ከቅጥሩ ማእዘን ትይዩና በዘብ መጠበቂ
ያው አደባባይ አጠገብ ካለው ከላይኛው
ቤተ መንግሥት መጠበቂያ ግንብ ጀምሮ
ያለውን መልሶ ሠራ:: ከእርሱም ቀጥሎ የፋ
ሮስ ልጅ ፈዳያና 26በዖፌል ኰረብታ ላይ
የሚኖሩት የቤተ መቅደሱ አገልጋዮች "የውሃ
በር" ተብሎ ከሚጠራው ትይዩ ጀምሮ በስተ
ምሥራቅ እስከሚገኘው ግንብ ድረስ መል
ሰው ሠሩ:: 27ከእነርሱ ቀጥሎ የቴቁሐ
ሰዎች ከታላቁ ግንብ ትይዩ ጀምሮ እስከ
ዖፌል ቅጥር ድረስ ያለውን ሌላ ክፍል
መልሰው ሠሩ::

28"የፈረስ በር" ተብሎ ከሚጠራው በላይ
ያለውን ደግሞ ካህናቱ እያንዳንዳቸው በየ
መኖሪያ ቤታቸው ትይዩ ያለውን መልሰው
ሠሩ:: 29ከእነርሱም ቀጥሎ የኢሜር ልጅ
ሳዶቅ በቤቱ ትይዩ ያለውን መልሶ ሠራ::
ከእርሱ ቀጥሎ ያለውን "የምሥራቅ በር"
ጠባቂ የሆነው የሴኬንያ ልጅ ሸማያ መልሶ
ሠራ:: 30ከእርሱ ቀጥሎ ያለውን ሌላ ክፍል
ደግሞ የሰሌምያ ልጅ ሐናንያና የሴሌፍ
ስድስተኛ ልጅ ሐኖን መልሰው ሠሩ::
ከእነርሱም ቀጥሎ የበራክያ ልጅ ሜሱላም
ከመኖሪያው ትይዩ ያለውን መልሶ ሠራ::
31ከእርሱ ቀጥሎ ከወርቅ አንጥረኞች አንዱ
መልክያ በመቈጣጠሪያው በር ትይዩ እስከ
ሚገኘው እስከ ቤተ መቅደሱ አገልጋዮችና
እስከ ነጋዴዎቹ ቤት፣ እንዲሁም ከማእዘኑ
በላይ እስከሚገኘው ክፍል ያለውን መልሶ
ሠራ፤ 32ከማእዘኑ በላይ ከሚገኘው ክፍል
ጀምሮ እስከ በጎች በር ያለውን ደግሞ
ወርቅ አንጥረኞቹና ነጋዴዎቹ መልሰው
ሠሩ::

## ቅጥሩ እንዳይሠራ የተደረገ ተቃውሞ

4 ሰንባላጥ ቅጥሩን እንደምንሠራ በሰማ
ጊዜ ተቈጣ፤ እጅግም ተበሳጨ:: በአይ
ሁድም ላይ ተሣለቀ፤ 2በተባባሪዎቹና በሰ
ማርያ ሰራዊት ፊት፣ "እነዚህ ደካማ አይ
ሁድ ምን እያደረጉ ነው? ቅጥራቸውን
መልሰው ሊሠሩ ነውን? መሥዋዕት ሊያ
ቀርቡ ነውን? በአንዲት ጀንበር ሠርተው
ሊጨርሱ ነውን? እንደዚያ ተቃጥሎ የፍር
ስራሽ ክምር የሆነውን ድንጋይ ነፍስ ሊዘሩ
በት ይችላሉን?" አለ::

3በአጠገቡም ቆሞ የነበረው አሞናዊው
ጦቢያ፣ "ለመሆኑ የሚገነቡት ምንድን ነው?

3፥21 ዕዝ8፥33
3፥24 ዕዝ8፥33
3፥25 ዕዝ2፥3፤ ኤር32፥2፤37፥21፤ 39፥14
3፥26 2ዜና 33፥14፤ነህ7፥46፤8፥1፤ 3፡16፤11፥21፤12፥37
3፥27 ቍ5፤ መዝ48፥12
3፥28 2ነገ 11፥16
3፥32 ቍ1፣ዮሐ5፥2
4፥1 ነህ2፥10
4፥2 ዕዝ4፥9-10፤ መዝ79፥1፤ኤር26፥18
4፥3 ነህ2፥10 ኢዮ13፥12፤15፥3

ዊት ዘመን መጀመሪያ ላይ ትልቅ ሚና ተጫውታለች (1ሳሙ 23፥1-13)::

3፥19 *ከ ... ጦር መሣሪያ ግምጃ ቤት፤* የቍ16 ማብ ይመ::

*3፥20-21* የሊቀ ካህናቱና የካህናቱ *መኖሪያ* በከተማዋ ውስጥ በምሥራቁ ቅጥር በኩል ነበር::

3፥25 *ከላይኛው ቤተ መንግሥት፤* ጥንታዊው የንጉሥ ዳዊት ቤተ መንግሥት ሊሆን ይችላል (12፥37 ይመ):: እንደ ንጉሥ ሰሎሞን ቤተ መንግሥት ሁሉ የዘብ ቤት ሳይኖረው አይቀርም (ኤር 32፥2)::

3፥26 *ዖፌል፤* ቍ 27 ይመ:: ትርጕሙም "ያበጠ" ወይም "የተነፋ" ማለት ነው፤ ይህም በሚክ 4፥8 (አማራጭ ትርጕሙን ይመ) ላይ እንደ ተመለከተው፣ የተመሸገ "ኰረብታ" ማለት ሊሆን ይችላል:: የሚገኘውም ከቤተ መቅደሱ በስተ ደቡብ፣ የመጀመሪያው የዳዊት ከተማ በነበረበት፣ በተለይ በኢየሩሳሌም ደቡብ ምሥራቅ ኰረብታ ሰሜናዊ ክፍል አካባቢ ነው (2ዜና 27፥3):: *የውሃ በር፤* ይህ ስም ሊሰጥ የቻለው የኢየሩሳሌም ከተማ ውሃ ወደሚፈልቅበት ወደ ግዮን ምንጭ ስለሚወስድ ነው:: የኦሪት መጻሕፍት የሚነበቡት በዚያ ስለ ነበር (8፥1፡3፡16፤ 12፥37) በሩ በሰፋት መከፈት ነበረበት:: *ግንብ፤* ምናልባት በዖፌል ኰረብታ ጫፍ ላይ ከ1923-25 ዓ.ም. በተደረገው የሥነ ቅርስ ተመራማሪዎች ጥናት የተገኘው ትልቅ ግንብ ሊሆን ይችላል:: በ1978 ዓ.ም. ግንቡ በተገነባበት ቦታ ላይ የተደረገው የሥነ ቅርስ ቍፋሮ፣ ግንቡ በፋርስ ዘመነ መንግሥት የነበረ መሆኑን ይገልጻል::

3፥27 *የቴቁሐ ሰዎች፤* ተራዎቹ የቴቁሐ ሰዎች ዕጥፍ ድርብ ተግባር ሲያከናውኑ፣ ከባላባት ወገን የሆኑት ግን ከኀላፊነታቸው ይሸሹ ነበር (የቍ 5 ማብ ይመ)::

3፥28 *የፈረስ በር፤* ጎቶልያ የተገደለችበት ቦታ ነው (2ዜና 23፥15):: በከተማው ምሥራቃዊ ቅጥር ጫፍ ላይ የነበረ በር ሳይሆን አይቀርም፤ በዚህም በር ወደ ቄድሮን ሸለቆ መውጣት ይቻል ነበር (ኤር 31፥40)::

3፥29 *የምሥራቅ በር፤* በአሁኑ ጊዜ "ወርቃማው በር" የሚባለው ሳይሆን አይቀርም ::

3፥31 *ከወርቅ አንጥረኞች፤* ቍ8 ይመ:: *በመቈጣጠሪያው በር፤* በምሥራቁ ቅጥር ሰሜናዊ ክፍል የሚገኝ ነው::

3፥32 *በጎች በር፤* የቅጥሩ ሥራ ተጠናቆ ሥራው ወደ ተጀመረበት ቦታ ዞሮ መግጠሙን ያሳያል (ቍ 1ይመ)

4፥2 *አለ፤* ተቀናቃኝ በሆኑ የፋርስ ባለ ሥልጣኖች መካከል ጠብና ክርክር የተለመደ ነበር:: ሰንባላጥ ብዙ የፌዝ ጥያቄ እያቀረበ የአይሁድን ሕዝብ ለማበሳጨትና ተስፋ ለማስቈረጥ ጥረት ያደርግ ነበር:: *ተቃጥሎ፤* የቅጥሩ ድንጋዮች በእሳት ከመቃጠላቸው የተነሣ፣ ቅጥሩ ተፈረካክሶ ፈራርሶአል፤

4፥3 *ቀበሮ፤* መሳ 15፥4፤ ማሕ 2፥15 ይመ:: ይህን ለመግለጽ የገባው የዕብራይስጡ ቃል "ተኵላ" ማለት ሊሆን ይችላል (መዝ 63፥10፤ ሰቆ 5፥18፤ ሕዝ 13፥4):: ተኵላዎች ምግብ ፍለጋ የሚወጡት በቡድን ሲሆን፣ ቀበሮ ግን ሌሊት ሌሊት የምትሄድ ብቸኛ እንስሳ ናት::

በድንጋይ የሚሠሩት ቅጥር እኮ ቀበሮ
እንኳ ብትወጣበት ሊፈርስ ይችላል" አለ።
4አምላካችን ሆይ፤ ተንቀናልና ስማን፤ ስድ
ባቸውን በራሳቸው ላይ አውርድባቸው፤ በም
ርኮ ምድር እንዲበዘበዙ አሳልፈህ ስጣቸው።
5የፈረሰውን በሚሠሩት ፊት የስድብ ናዳ
አውርደዋልና“ በደላቸውን ይቅር አትበል፤
ኀጢአታቸውንም ከፊትህ አታጥፋው።
6ሕዝቡ ከልቡ ስለሚሠራ፣ ቅጥሩን እኩ
ሌታው ድረስ መልሰን ሠራነው።
7ሰንባላጥ፣ ጦቢያ፣ ዐረቦች፣ የአሞንና
የአሽዶድ ሰዎች፣ የኢየሩሳሌም ቅጥር ሥራ
እየተፋጠነና ክፍት ቦታዎቹም ሁሉ እየ
ተሞሉ መሆናቸውን በሰሙ ጊዜ እጅግ
ተቈጡ። 8መጥተውም ኢየሩሳሌምን ይወጉ
ዘንድ፣ ሽብርንም ይፈጥሩ ዘንድ ሁሉም በአ
ንድነት አደሙ። 9እኛ ግን ወደ እግዚአብ
ሔር ጸለይን፤ ዛቻቸውንም ለመቋቋም ቀንና
ሌሊት የሚጠብቁ ዘቦችን መደብን።
10በዚህ ጊዜ የይሁዳ ሕዝብ፣ "የሠራተ
ኞቹ ጒልበት እየደከመ ነው፤ ከፍርስራሹም
ብዛት የተነሣ ቅጥሩን መልሰን ለመሥራት
አንችልም" አሉ።
11ጠላቶቻችን ደግሞ፣ "በመካከላቸው ገብ
ተን እስክንገድላቸውና ሥራውን እስክናስ
ቆም ድረስ አያውቁም ወይም አያዩም"
አሉ።
12ከዚያም በአጠገባቸው የሚኖሩ አይሁድ
መጥተው፣ "እናንተ የትም ቦታ ብትሆኑ፣
እኛን ማጥቃታቸው አይቀርም!" በማለት ዐሥር
ጊዜ ደጋግመው ነገሩን።
13ስለዚህ ከቅጥሩ በስተኋላ በሚገኙ ግልጽ
ቦታዎች ላይ ከሕዝቡ አንዳንዶቹ ሰይፋቸ
ውን፣ ጦራቸውንና ቀስታቸውን እንደ ያዙ
በየቤተ ሰባቸው በመመደብ ቦታቸውን እንዲ
ይዙ አደረግሁ። 14ነገሩን በጥሞና ከተመለከ
ትሁ በኋላ መኳንንቱን፣ ሹማምቱንና የቀረ
ውን ሕዝብ፣ "አትፍሯቸው፤ ታላቁንና የተፈራ
ውን እግዚአብሔርን አስቡ፤ ስለ ወንድሞቻ
ችሁ፣ ስለ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁ፣ ስለ
ሚስቶቻችሁና ስለ ቤት ንብረታችሁ ተዋጉ
አልኋቸው።
15አድማቸውን እንዳወቅንባቸውና እግዚ
አብሔርም ዕቅዳቸውን ከንቱ እንዳደረገባቸው
ጠላቶቻችን በሰሙ ጊዜ፣ ሁላችን ወደ ቅጥሩ፣
እያንዳንዳችንም ወደየሥራችን ተመለስን።
16ከዚያን ቀን ጀምሮ ከሰዎቼ እኩሌቶቹ
ሥራውን ሠሩ፤ የቀሩት ደግሞ ጋሻና ጦር፣
ቀስትና ጥሩር ይዘው ነበር። የጦር አለቆች
ከመላው የይሁዳ ሕዝብ በስተኋላ ቆሙ፤
17እነርሱም ቅጥሩን ይገነቡ ነበር ዕቃ የሚሸ
ከሙት በአንድ እጃቸው ሥራቸውን ሲሠሩ፣
በሌላው እጃቸው የጦር መሣሪያቸውን ይዘው
ነበር፤ 18እያንዳንዱም ግንበኛ ቅጥሩን በሚ
ሠራበት ጊዜ ሰይፉን በወገቡ ላይ ታጥቆ
ነበር፤ መለከት የሚነፋው ሰው ግን ከእኔ
አይለይም ነበር።
19ከዚያም ለመኳንንቱ፣ ለሹማምቱና ለቀ
ረው ሕዝብ እንዲህ አልሁ፤ "ሥራው ታላቅ
ነው፤ ብዙም ነው፤ እርስ በርሳችን በቅጥሩ
ላይ እጅግ ተራርቀናል፤ 20የመለከት ድምፅ
በምትሰሙበት ጊዜ፣ ወደ እኛ ተሰብሰቡ።
አምላካችን ስለ እኛ ይዋጋል።"
21ስለዚህ ጎሕ ሲቀድ ጀምሮ ከዋክብት እስ
ኪወጡ ድረስ እኩሌቶቹ ሰዎች ጦራቸውን
እንደ ያዙ ሥራውን ቀጠልን። 22በዚያን ጊዜ
ለሕዝቡ፣ "ሌሊት ዘብ በመጠበቅና ቀን ሥራ
በመሥራት እንዲያገለግለን እያንዳንዱ ሰው
ከነረዳቱ በኢየሩሳሌም ይቈይ" አልኋቸው።
23እኔም ሆንሁ ወንድሞቼ፣ ሰዎቼም ሆኑ
ከእኔ ጋር ያሉት ጠባቂዎች ልብሳችንን አላ
ወለቅንም፤ ለውሃ እንኳ በምንሄድበት ጊዜ

4፥4 መዝ44፥13፤ 123፥3-4፤ኤር33፥24
4፥5 2ነገ14፥27፤ መዝ51፥1፤69፥27-28፤ 109፥14፤ኢሳ2፥9፤ ኤር18፥23፤ሰቆ1፥22
4፥7 ነህ2፥10
4፥8 መዝ2፥2፤ 83፥1-18
4፥10 1ዜና23፥4
4፥14 ዘኍ28፥15፤ ዘዳ1፥29፤2ሳሙ10፥12፤ነህ1፥5፡8
4፥15 2ሳሙ 17፥14፤ ኢዮ5፥12
4፥17 መዝ149፥6
4፥18 ዘኍ10፥2
4፥20 ዘፀ14፥14፤ ዘዳ20፥4፤ ኢሱ10፥14፤ሕዝ33፥3

“5 *ወይም የፈረሰውን በሚሠሩት ፊት እንድትቈጣ አድር ገውሃልና*

*4፥4-5፤* የርግማን መዝሙሮች እንደሚባሉት የዳዊት መዝሙሮች ሁሉ (መዝ 79፥12፤ 83፤94፥1-3፤ 109፥14፤137፥7-9)፣ ነህምያም እግዚአብሔር ተቃዋሚቹን እንዲበቀልለት ይጸልያል እንጂ በራሱ እንዳች ርምጃ *አይወስድም፤* ቍ5 ላይ የሚገኘው የነህምያ ጸሎት ኤር 18፥23 ላይ ያለውን የሚያስተጋባ ነው።

4፥7 *የአሽዶድ፤* የኢሳ 20፥1 ማብ ይመ። በፋርስ ዘመነ መንግሥት የወረዳ ዋና ከተማ ነበረች።

4፥9 *ጸለይን... ዘቦችን መደብን፤* ጸሎትና ነቅቶ መገኘት የእምነትንና የሥራን አንድነት ያመለክታል፤ የሰዎችን ኀላፊነትና የእግዚአብሔርን ድርሻ አጒልቶ የሚያሳይ ነው።

4፥10 *እየደከመ ነው፤* ይህ አገላለጽ አንድ ሠራተኛ ሸክሙ ከብዶት፣ ጒልበት ከድቶት ለመውደቅ መንገዳገዱን ያሳያል።

4፥11 *ጠላቶቻችን ... አሉ፤* ነህምያ በምስጢር ወሬ የሚያቀብለው ወዳጅ እንደ ነበረው ወይም ጠላት ሆን ብሎ ሐሰተኛ ወሬ እንደሚነዛበት ያመለክታል።

4፥12 *ዐሥር ጊዜ፤* ብዙ ጊዜ እንደ ማለት ነው።

4፥13 *ግልጽ ቦታዎች፤* ነህምያ ቅጥሩ ለጥቃት በተጋለጠበት በኩል ሰዎቹን አቆማቸው። *ጦራቸውንና፤* በጊዜው ለመከላከል ይጠቀሙበት የነበረ የጦር መሣሪያ ነው (ዘኍ 25፥7-8፤ 1ነገ 18፥28)።

4፥14 *አትፍሯቸው ... እግዚአብሔርን አስቡ፤* የ1፥8 ማብ ይመ። መፈራት የሚገባውን እግዚአብሔርን ብቻ ማሰብ ፍርሀትን ለማስወገድ ሁነኛ መንገድ ነው (ዘዳ 3፥22፤ 20፥3፤ 31፥6 ይመ)።

4፥16 *ጋሻ፤* ከእንጨትና ከሸምበቆ መስል አገዳ የሚሠራ በመሆኑ ሊቃጠል የሚችል ነው (ሕዝ 39፥9)። *ጥሩር፤* የዕብራይስጡ ቃል ደረትን የሚሸፍን ወይም እንደ ኮት የሚጠለቅ ከብረት የተሠራ መሆኑን ያመለክታል (2ዜና 18፥33 ይመ)።

4፥17 *በአንድ እጃቸው ... ሲሠሩ፣ በሌላው ... የጦር መሣሪያቸውን፤* ሠራተኞቹ በአንድ እጃቸው የሥራ ዕቃቸውን፣ በሌላው እጃቸው ደግሞ የጦር መሣሪያቸውን ይይዙ ወይም በአጠገባቸው ያስቀምጡ ነበር።

4፥18 *መለከት፤* የኢሳ 18፥3 ማብ እና ኢሱ 6፥4፡6፡8፡13 ይመ።

4፥20 *አምላካችን ስለ እኛ ይዋጋል፤* እግዚአብሔር ስለ ሕዝቡ የሚዋጋውን ቅዱስ ጦርነት ያመለክታል፤ ይህንም ሐሳብ በኢሱ 10፥14፡42፤ መሳ 4፥14፤ 20፥35፤2ሳሙ 5፥24 ላይ ይመ። የኢያሱን መግቢያ ይመ።

4፥21 *ከዋክብት እስኪወጡ ድረስ፤* ምን ያህል ለሥራ ታጥቀው እንደ ተነሡ ያሳያል፤ የተለመደው የሥራ ማቆሚያ ጊዜ ጀንበር ስትጠልቅ ነበርና (ዘዳ 24፥15፤ ማቴ 20፥8)።

4፥22 *ሌሊት ዘብ በመጠበቅና፤* ከኢየሩሳሌም ውጭ ይኖሩ የነበሩ ሰዎች እንኳ ሳይቀሩ፣ በጥበቃ ሥራ ላይ ለመሰማራት በከተማዪቱ ውስጥ ያድሩ ነበር።

*4፥23፤* አማራጭ ትርጒሙን ይመ። ምንም እንኳ የዚህ ጥቅስ የመጨረሻ ሐረግ ትክክለኛ ትርጒም በውል ባይታወቅም፣ መርሑ ምን ጊዜም ዝግጁ ሆኖ መገኘት ነው። ነህምያ "ራሱ

እያንዳንዱ ሰው የጦር መሣሪያውን እንደ
ያዘ ነበር::ʻ

## ነህምያ ድኾችን ረዳ

**5** በዚህ ጊዜ ወንዶቹና ሚስቶቻቸው አይ
ሁድ ወንድሞቻቸውን በመቃወም ብርቱ
ጩኸት አሰሙ፤ 2 አንዳንዶቹ፣ “እኛም ሆን
ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችን በቍጥር ብዙ
ነን፤ ታዲያ ለመብላትም ሆነ በሕይወት
ለመቈየት እህል ማግኘት አለብን” አሉ::
3 ሌሎቹ በራብ ወቅት እህል ለማግኘት
ስንል እርሻችንን፣ የወይን ተክል ቦታችንንና
ቤታችንን እስከ ማስያዝ ደርሰናል አሉ::
4 ሌሎቹ ደግሞ እንዲህ አሉ፤ “የእርሻችን
ንና የወይን ተክል ቦታችንን ግብር ለንጉሡ
ለመክፈል ገንዘብ እስከ መበደር ደርሰናል::
5 ምንም እንኳ ከአገራችን ሰዎች ጋር በሥ
ጋና በደም አንድ ብንሆንም፣ እንደ እነርሱ
ልጆች ሁሉ የእኛም ወንዶች ልጆች ጥሩ
ዎች ቢሆኑም፣ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻች
ንን ባሮች እንዲሆኑ ሰጥተናል፤ አንዳንድ
ሴቶች ልጆቻችን አሁንም በባርነት ላይ
ናቸው፤ እርሻችንና የወይን ተክል ቦታችን
የሌሎች በመሆናቸው እኛ ደካሞች ሆነናል::
6 እኔም ጩኸታቸውንና እነዚህን አቤቱ
ታዎች በሰማሁ ጊዜ፣ እጅግ ተቈጣሁ፤
7 ከዚያም ነገሩን በሐሳቤ ካወጣሁ ካወረድሁ
በኋላ፣ መኳንንቱንና ሹማምቱን ገሥጿቸው፤
“ከገዛ አገራችሁ ሰዎች ላይ እንዴት ዐራጣ
ትበላላችሁ!” አልኋቸውም:: ስለዚህ ከእነርሱ
ጋር ለመነጋገር ታላቅ ስብሰባ ጠራሁ፤
8 ለአሕዛብ ተሸጠው የነበሩትን አይሁድ ወንድ
ሞቻችንን በተቻለን ሁሉ ተቤዥተናቸዋል፤
አሁንም እናንተ ወንድሞቻችሁን ትሸጣላ
ችሁ፤ ይህም መልሰን እንድንቤዣቸው ለማ
ድረግ ብቻ ነው!” አልኋቸው፤ እነርሱም
የሚመልሱት አልነበራቸውምና ዝም አሉ::
9 ስለዚህ በመቀጠል እንዲህ አልሁ፤ “ይህ
የምታደርጉት ነገር ትክክል አይደለም፤ የጠ
ላቶቻችንን የአሕዛብን ስድብ ለማስወገድ
የአምላካችንን መንገድ በፍርሀት መከተል

5፥3 ዘፍ47፥23፤ መዝ109፥11
5፥4 ዕዝ4፥13
5፥5 ዘፍ29፥14፤ ዘሌ25፥39-43፤ 47፤ዘዳ15፥7-11፤ 2ነገ4፥1፤ኢሳ50፥1
5፥7 ዘፀ22፥25-27፤ ዘሌ25፥35-37፤ ዘዳ23፥19-20፤ 24፥10-13
5፥8 ዘሌ25፥47፤ ኤር34፥8
5፥9ኢሳ52፥5

ʻ23 በዕብራይስጡ የዚህ ሐረግ ትርጒም በትክክል አይታወቅም::

በሥራ ብዛት ድካም ሳይሰማው፣ ራብ ሳይበግረው፣ እንቅልፍ ሳያምረው ከተማዪቱን ሲዞር ያድር እንደ ነበርና ይህንም የሚያ ደርገው ለደስታ ሳይሆን አንገብጋቢ መሆኑን ስለተገነዘበ ነው በማ ለት” ዮሴፍ ወልደ ኮሪዮን ዘግቦአል::

*5፥1-19*፤ ነህምያ የኢየሩሳሌምን ቅጥር መልሶ ለመገንባት ባደረገው ጥረት የገንዘብ ችግር ገጥሞት ነበር:: ቅጥሩን ለመሥራት የፈጀው ጊዜ አምሳ ሁለት ቀን ብቻ ሆኖ ሳለ (6፥15)፣ በዚህ መካ ከል “ታላቅ ስብሰባ” መጥራቱ የሚያስደንቅ ነው (ቍ 7):: ምና ልባት የቅጥሩ ሥራ ዕቅድ የፈጠረው የኢኮኖሚ ጫና፣ የታመ ቀውን ችግር በግልጽ ያሳየና፣ ሥራው ዳር ከመድረሱም በፊት ምን መደረግ እንዳለበት በጥሞና እንዲታሰብበት ለማድረግ ነው:: ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ካጋጠማቸው ክፍሎች መካከል (1) የምግብ እጥረት የገጠማቸው መሬት የለሾች (ቍ 2)፤ (2) ንብረታቸውን አስይዘው እህል የወሰዱ ባለ ርስቶች (ቍ3)፤ እንዲሁም (3) ከፍ ተኛ ወለድ የሚያስከፍል ገንዘብ የተበደሩና ልጆቻቸውን በባርነት የሸጡ (ቍ 4-5) ይገኙበታል::

5፥1 ***ሚስቶቻቸው***፤ በገንዘብ እጥረት ምክንያት ቤተ ሰቦቻቸውን መመገብ የተሳናቸውም ሴቶች በተቃውሞው ተሳ ታፊ ሆነው ነበር፤ ይህም ሁኔታው ምን ያህል አስከፊ እንደ ነበር ያሳያል:: ጩኸታቸውን ያሰሙት በባዕዳን ባለ ሥልጣናት ላይ ሳይሆን፣ ሰው ሁሉ አገሩን ከጥቃት መከላከል በሚገባው ሰዓት፣ ድኻ ወንድሞቻቸውን በጨቈኑት ወገኖቻቸው ላይ ነበር::

5፥2 ***እህል***፤ አንድ ሰው መላ ቤተ ሰቡን አንድ ወር ለመ ቀለብ፣ ስድስት ወይም ሰባት ቍና እህል ያስፈልገው ነበር::

5፥3 ***ማስያዝ***፤ ብዙ ንብረት የነበራቸው እንኳ ያንኑ ለማ ስያዝ ተገደው ነበር፤ ይህ ደግሞ ለጥቂት ባለጠጎች ሲሳይ መሆን ነበር (ከኢሳ 5፥8 ጋር ያነጻጽሩ):: የኑሮ ውጥረት ወይም ችግር በሚከሠትበት ጊዜ ባለጠጋው እየበለጠገ ሲሄድ፣ ድኻው ደግሞ ይበልጥ እየደኸየ ይሄዳል:: *በራብ፤* የተፈጥሮ ሁኔታዎች መቃወስ የኢኮኖሚውን ሚዛን አዛብቶታል፤ ራብንም አስከትሎአል:: ከስባ አምስት ዓመት በፊት ነቢዩ ሐጌ በቂ ምግብ ያልነበረበትን የድ ርቅ ዘመን አውስቶ ነበር (ሐጌ 1፥5-11):: እንደዚህ ዐይነቱ የች ግር ወቅት የእግዚአብሔርን ቍጣ ወይም ፍርድ እንደሚያመለ ክት ይታመን ነበር (ኢሳ 51፥19፤ ኤር 14፥13-18፤ አሞ 4፥6):: ራብ በፓለስቲና ብዙ ጊዜ ተከሥቶአል፤ ለምሳሌ በአብርሃም (ዘፍ 12፥10)፣ በይስሐቅ (ዘፍ 26፥1)፣ በዮሴፍ (ዘፍ 41፥27:54)፣ በሩት (ሩት 1፥1)፣ በዳዊት (2ሳሙ 21፥1)፣ በኤልያስ (1ነገ 18፥2)፣ በኤልሳዕ (2ነገ 4፥38)፤ እንዲሁም በቀላውዴዎስ ዘመን (ሐሥ 11፥28) ራብ ተከሥቶ ነበር::

5፥4 ***ግብር***፤ የፋርስ ንጉሥ በያመቱ ሃያ ሚሊዮን ያህል ዳሪክ ወርቅ ከግብር ያገኝ እንደ ነበር ይገመታል:: ከዚህም ውስጥ አብዛኛው እየቀለጠ ተጠፍጥፎ ወደ ግምጃ ቤት ይገባ ስለ ነበር፣ በግዛቱ ውስጥ ለነበሩት አውራጃዎች ጥቅምና ልማት የሚውለው እጅ ጥቂት ነበር:: ታላቁ እስክንድር በሱሳ ከተማ ግምጃ ቤት ብቻ 340 ቶን ያህል ጥፍጥፍ ወርቅና 1500 ቶን ያህል ጥፍጥፍ ብር አግኝቶአል:: ሳንቲሞች በግብር መልክ ይሰበሰቡ ስለ ነበር፣ የዋጋው ግሽበት ከቍጥጥር ውጭ ይሆን ነበር የፋርስ ሰዎች መሬትን በርስትነት ይዘው እንዲሁ ስለሚያስ ቀምጡ፣ ጠሙን የሚያድረው ቦታ እየሰፋ እንዲሄድ አድርጎአል፤ ይህም በፋርስ ዘመነ መንግሥት የዋጋ ንረት አምሳ በመቶ ከፍ እንዲል ምክንያት ሆኖአል::

5፥5 ***ባሮች***፤ የኑሮ ጫና አይሎ፣ አንድ ቤተ ሰብ ከመጠን በላይ ሲቸገር ከቤተ ሰቡ አንዱን ሰው መያዣ አድርጎ ገንዘብ መበደር የተለመደ ነበር:: ይሁን እንጂ የብድሩን ገንዘብ በወቅቱ ከነወለዱ መመለስ ካልተቻለ፣ የተበዳሪው ልጆች ወይም ሚስቱ ወይም ተበዳሪው ራሱ በባርነት ይሸጥ ነበር:: አንድ እስራኤላዊ በዚህ ዐይነት ችግር ውስጥ ቢገባ ግን ለአበዳሪው እንደ ተቀጣሪ ሠራተኛ ሆኖ በማገልገል ዕዳውን ከራሱ ላይ እንዲያወርድ ይደረጋል (ዘሌ 25፥39-40):: ባለ ዕዳው ራሱ ካልፈለገ በቀር፣ በሰባተኛው ዓመት ነጻ የመውጣት መብትም ነበረው (ዘዳ 15፥12-18):: በግብፅ ለሰባት ዓመት ራብ በነበረበት ጊዜ፣ ሰዎች ወደ ዮሴፍ ሄደው ርስታቸውንና ራሳቸውን ወስዶ በምትኩ እህል እንዲሰጣቸው ጠይቀውት ነበር (ዘፍ 47፥18-19):: እስራኤላ ውያንን ግራ የገባቸው ነገር ቢኖር፣ ተማርከው በመስጴጦምያ በነበሩበት ዘመን ቢያንስ ቤተ ሰባቸው ሳይለያይ በአንድነት ይኖሩ ነበር፤ አሁን ግን ከኑሮው ውድነት የተነሣ ልጆቻቸው በባርነት ይሸጡ ነበር::

5፥6 ***እጅግ ተቈጣሁ፤*** ***በወንድሞቹ ላይ*** የፍትሕ መጓደል ሲፈጸም ተቃውሞን በቍጣ መግለጽ ተገቢ ነው (ከማር 11፥15-18፤ ኤፌ 4፥26 ጋር ያነጻጽሩ)::

5፥7 ***ዐራጣ***፤ የዘፀ 22፥25-27፣ ዘሌ 25፥36፣ ዘዳ 23፥20 ማብ ይመ:: ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን “የወገንን ችግር የገቢ ምንጭ ማድረግ ስለማይገባ፣ ማንኛውም ዕብራዊ ለሚበላ ወይም ለሚጠጣ ነገር በዐራጣ ማበደር የለበትም፤ ከዚህ ይልቅ ወንድምህን በመከ ራው በማጽናናት ከእርሱ የምታገኘውን ውለታ እንዲሁም እግዚ አብሔር ለሠራኸው በጎ ሥራ ያዘጋጀልህን ወሮታ ማሰቡ ይሻ ላል” በማለት ጽፎአል (“አንቲኩዊቲ 4.8.25)::

5፥8 ***ለአሕዛብ***፤ አንድ ዕብራዊ ሌላውን ዕብራዊ ወንድ ሙን ለባዕድ አሳልፎ መሸጥ የተከለከለ ነው (ዘፀ 21፥8):: ***ተሸጠው የነበሩትን አይሁድ ወንድሞቻችንን***፤ የደኸየው ወንድም እንደ አገልጋይ ተቀጥሮ ሊሠራ ይችላል፤ ነገር ግን እንደ ባሪያ ሊሸጥ አይገባም (ዘሌ 25፥39-42):: ***ዝም አሉ***፤ የፈጸሙት በደል ግልጽ ስለ ነበረ፣ ሊከራከሩ ወይም ምክንያት ሊያቀርቡ አልቻሉም (ከዮሐ 8፥7-10 ጋር ያነጻጽሩ)::

5፥9 ***ትክክል አይደለም***፤ ሌላውን ሰው በተለይም በእምነት ወንድማችን የሆነውን በርኅራኄ ዐይን አለመመልከት ፈጣሪያችንን እንደ ማቃለል ይቈጠራል፤ የሕይወት ምስክርነታች ንንም ያጕድፋል (ከምሳ 14፥31፤1ጴጥ 2፥12-15 ጋር ያነጻጽሩ)::

አይገባችሁምን? 10እኔ፣ ወንድሞቼና ሰዎ
ቼም እንደዚሁ ለሕዝቡ ገንዘብና እህል አበ
ድረናል፤ ዐራጣው ግን ያብቃ:: 11እርሻቸ
ውን፣ የወይንና የወይራ ዘይት ተክል ቦታቸ
ውንና ቤታቸውን በቶሎ መልሱላቸው፤ እን
ዲሁም የምታስከፍሏቸውን የገንዘቡን፣ የእህ
ሉን፣ የአዲሱን ወይንና ዘይት አንድ መቶኛ
ዐራጣ መልሱላቸው":: 12እነርሱም፣ "እንመል
ሳለን፤ ምንም ዐይነት ትርፍ አንጠይቃቸ
ውም፤ እንዳልኸን እናደርጋለን" አሉ:: ካህና
ቱን ጠራኋቸው፤ መኳንንቱንና ሹማምቱ
ንም የገቡትን ቃል እንዲፈጽሙ አማልኋ
ቸው:: 13እንዲሁም የልብሴን ዘርፍ አራ
ግፌ፣ "ይህን የተስፋ ቃል የማይፈጽመውን
ማናቸውንም ሰው ስምባክ ቤቱንና ንብረቱን
እንደዚህ ያራግፈው፤ እንደዚህ ያለውም
ሰው ይርገፍ፤ ባዶም ይሁን" አልሁ:: በዚህም
ጉባኤው ሁሉ፣ "አሜን" በማለት እግዚአ
ብሔርን አመሰገነ፤ ሕዝቡም የገቡትን
ቃል ፈጸሙ::

14ከዚህም በላይ በይሁዳ ምድር አገረ
ገዥ ሆኜ ከተሾምሁበት፣ ከአርጤክስስ
ሃያኛ ዓመት ጀምሮ እስከ ሠላሳ ሁለተኛው
ዘመነ መንግሥቱ ድረስ፣ ለዐሥራ ሁለት
ዓመት እኔም ሆንሁ ወንድሞቼ ለአንድ
አገረ ገዥ የተመደበውን ምግብ ተቀብለን
አልበላንም:: 15ከእኔ በፊት የነበሩት የቀ
ድሞዎቹ አገረ ገዦች ግን ከምግቡና ከወይኑ
ሌላ፣ በሕዝቡ ላይ ከባድ ሸክም በመጫን
አርባ ሰቅል[ሀ] ብር ይወስዱ ነበር፤ ረዳቶቻ
ቸውም እንዲሁ ይጭኑባቸው ነበር:: እኔ
ግን እግዚአብሔርን ከመፍራቴ የተነሣ እንዲህ
ያለውን አላደረግሁም:: 16ከዚህ ይልቅ ራሴን
ለዚህ ቅጥር ሥራ ሰጠሁ:: ሰዎቼም ሁሉ
ለሥራው እዚያው ይሰበሰቡ ነበር፤ ምንም
መሬት አልነበረንም[ለ]::

17ከዚህም በላይ በዙሪያችን ካሉት፣ ወደ
እኛ ከሚመጡት አሕዛብ ሌላ አንድ መቶ
አምሳ አይሁድና ሹማምት ከማእዴ ይካ
ፈሉ ነበር:: 18በየዕለቱም አንድ በሬ፣ ስድ
ስት ምርጥ በጎችና የተወሰኑ ዶሮዎች፣ በየዐ
ሥሩም ቀን ብዛት ያለው ልዩ ልዩ የወ
ይን ጠጅ ይዘጋጅልኝ ነበር:: ይህም ሁሉ
ሆኖ ለአንድ አገረ ገዥ የተመደበውን ምግብ
ከቶ ጠይቄ አላውቅም፤ በሕዝቡ ላይ የተጣ
ለው ሸክም ከባድ ነበርና::

19አምላኬ ሆይ፤ ለዚህ ሕዝብ ያደረግሁ
ትን ሁሉ በበጎነት አስብልኝ::

## በቅጥሩ ሥራ ላይ የተነሣ ሌላ ታቃውሞ

6 እስከዚያች ጊዜ ድረስ ለበሮቹ መዝጊያ
ባልገጥምላቸውም እንኳ፣ ቅጥሩን መሥ

5፥10 ዘፀ22፥25
5፥11 ኢሳ58፥6
5፥12 ዕዝ10፥5
5፥13 ዘዳ27፥15-26፤ ማቴ10፥14
5፥14 ዘፍ42፥6፤ ዕዝ6፥7፤ ነህ2፥6፤ኤር40፥7፤ ሐጌ1፥1
5፥15 ዘፍ20፥11
5፥16 2ተሰ3፥7-10
5፥18 1ነገ4፥23
5፥19 ዘፍ8፥1፤ 2ነገ20፥3፤ነህ1፥8
6፥1 ነህ2፥10፡19

[ሀ]15 0.5 ኪሎ ግራም ያህል ነው::
[ለ]16 ብዙ የዕብራይስጥ ቅጆች ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ አንዳንድ የዕብራይስጥ ቅጆች፣ የሰብዓ ሊቃናት፣ የቩልጌትና የሱረሰት ቅጆች ግን *አልነበረኝም* ይላሉ::

5፥10 *ዐራጣው ግን ያብቃ፤* ብሉይ ኪዳን በሌላው ሰው ትክሻ ትርፍ ለማግኘት መስገብገብን አጥብቆ ያወግዛል፤ (መዝ 119፥36፤ ኢሳ 56፥9-12፤57፥17፤ኤር 6፥13፤ 8፥10፤ 22፥13-17፤ ሕዝ 22፥12-13፤ 33፥31):: ነህምያ ሕዝቡ የደረሰበትን የኑሮ ቀውስ ከግምት ውስጥ በማስገባት አበዳሪዎች የሚገባቸውን ወለድ እንዲተዉ ይጠይቃቸዋል::

5፥11 *የእህሉን፣ የአዲሱን ወይንና ዘይት፤* የ10፥37፤ ዘዳ 7፥13 ማብ ይመ::

5፥13 *የልብሴን ዘርፍ አራግፌ፤* ድርጊቱ የመሐላውን ክብደት የሚያመለክት ሲሆን፣ ካልተፈጸመም የሚያስከትለውን ርግማን ያሳያል:: *አሜን፤* 8፥6፤ ዘኍ 5፥22 እና የዘዳ 27፥15 ማብ ይመ::

5፥14 *ሠላሳ ሁለተኛው ዘመነ መንግሥቱ፤* ከሚያዝያ 1 ቀን 433 ዓ.ቅ.ክ እስከ ሚያዝያ 19 ቀን 432 ዓ.ቅ.ክ ድረስ ማለት ነው:: ነህምያ በመጀመሪያው ዙር ገዥ ሆኖ ዐሥራ ሁለት ዓመት ካገለገለ በኋላ፣ ወደ ቤተ መንግሥት እንዲመለስ ተጠራ (13፥6)፤ ከዚያም እንደ ገና ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ (13፥7)፤ በዚህ ጊዜ ገዥ ሆኖ ምን ያህል እንደ ቈየ ማወቅ አይቻልም:: *ለአንድ አገረ ገዥ የተመደበውን ምግብ፤* ቍ 18 ይመ:: የአውራጃ ገገዦች አብዛኛውን ጊዜ በሚያስተዳድሩት አገር ከሚገኘው ሕዝብ ክብርን ለማግኘት ይጥሩ ነበር:: ነህምያ ግን ልክ እንደ ጳውሎስ (1ቆሮ 9፤ 2ተሰ 3፥8-9)፣ ለሕዝቡ አርአያ ለመሆን ሲል የሚገባውን እንኳ ትቶአል::

5፥15 *አገረ ገዦች፤* ሰሳብሳር (ዕዝ 5፥14)፣ ዘሩባቤልና (ሐጌ 1፥1፡14፤2፥2) የተለያዩ የፋርስ ባለሥልጣናት በዚህ ማዕረግ ተጠ ርተዋል (ዕዝ 5፥3፡6፤ 6፥6-7፡13፤8፥36፤ነህ 2፥7፡9፤3፥7):: ነህምያ እዚህ ላይ የሚጠቅሰው በዘሩባቤል ደረጃ የሚገኙትን ሰዎች አይደለም:: አንዳንድ ሰዎች የይሁዳ አውራጃ ከነህምያ በፊት ገዥ እንዳልነበራትና፣ እዚህም ላይ የተጠቀሱት ቢሆን የሰማርያ ገዦች እንደ ሆኑ ይናገራሉ:: ይሁን እንጂ በቅርቡ በተደረገው የሥነ ቅርስ ቍፋሮ የተገኙ ማኅተሞችና በማኅተም የታተሙ ሰነዶች እንደሚያመለክቱ ከሆነ፣ የይሁዳ አውራጃ ቀደም ሲልም ገዦች ነበሯት:: *ከባድ ሸክም፤* በፋርስ መንግሥት አሠራር መሠ ረት በቤተ መቅደስ የሚያገለግሉትን ሰዎች ከግብር ነጻ ማድ ረግ የተለመደ ነበር፤ ይህም በተራው ሕዝብ ላይ ቀረጥ እንዲ ጨመር ምክንያት ሆኖአል:: *ረዳቶቻቸውም፤* ገዦቹ በጕልበት የሚቀሙ ከሆነ፣ የበታች ሹማምታቸውም የባሰ ቀማኞች መሆና ቸው የታወቀ ነበር (ከማቴ 18፥21-35፤ 20፥25-28 ጋር ያነጻ ጽሩ):: *እግዚአብሔርን ከመፍራቴ፤* በከፍተኛ የሥልጣን እርከን ላይ የሚገኙ ሹማምት እነርሱ ራሳቸው "በሰማይ ላለው ጌታ" አገልጋይ መሆናቸውን ረስተው (ቈላ 4፥1፤ ከዘፍ 39፥9፤ 2ቆሮ 5፥11 ጋር ያነጻጽሩ)፣ ከበታቻቸው በሚገኘው ሕዝብ ላይ ሥልጣ ናቸውን ያለ አግባብ የሚጠቀሙ ከሆነ፣ የሚጠብቃቸው ፍርድ የባሰ ነው::

5፥16 *ምንም መሬት አልነበረንም፤* ነህምያ የገዢነቱን ሥልጣን በመጠቀም ለራሱ ሳያደላ፣ የሕዝቡ አገልጋይ በመሆን ተግባሩን ያከናውን ነበር::

5፥17 *ከማእዴ ይካፈሉ ነበር፤* አንድ መሪ ወይም ገዥ ካለበት ማኅበራዊ ኀላፊነት የተነሣ በነጻ ማብላትና ማጠጣት ይጠበቅበት ነበር:: በኒምሩድ የተገኘ አንድ ጽሑፍ ዳግማዊ አሹርናሲርፓል 69,574 ሰዎችን ዐሥር ቀን ሙሉ እንዳበላና እንዳጠጣ ይናገራል:: ንጉሥ ሰሎሞን ቤተ መቅደሱን መርቆ በከፈተበት ዕለት 22,000 ከብት እንዲሁም 12,0000 በግና ፍየል ታርዶ፣ ዐሥራ አራት ቀን ሙሉ ጉባኤውን ሲያበላና ሲያጠጣ እንደ ሰነበተ ተጽፎአል (1ነገ 8፥62-65):: ሆኖም ስንት ሰው እንዳበላና እንዳጠጣ አልተገለጸም (ከ1ነገ 4፥27 ጋር ያጻጽሩ)::

5፥18 *በየዕለቱም፤* በዚህ ስፍራ የተጠቀሱት ከብቶች ሥጋ፣ ከ600 እስከ 800 ለሚደርሱ ሰዎች ለአንድ ጊዜ የሚቀርብ ማእድ ሲሆን፣ ይኸውም በቍ 18 ላይ የተጠቀሱትን 150 አይሁ ድና ባለሥልጣኖች የሚጨምር ነው:: ሰሎሞን ለአንድ ቀን ካዘጋ ጀው ግብዣ ጋር ያነጻጽሩ (1ነገ 4፥22-23):: *ምርጥ በጎችና፤* ከሚል 1፥8 ጋር ያነጻጽሩ:: *ዶሮዎች፤* በ2000 ዓ.ቅ.ክ ዶሮዎች በሕን ዱስ ወንዝ ሸለቆ ለማዳ የቤት እንስሳት የነበሩ ሲሆን፣ በሣልሳ ዊው ቱትሞስ ዘመን (በ15ኛው ምእተ ዓመት ዓ.ቅ.ክ) ወደ ግብፅ ተወስደዋል:: በ8ኛው ምእተ ዓመት ዓ.ቅ.ክ በመስጴጦምያና በግሪክ ይታወቁ ነበር:: በፓለስቲና ከተገኙት ጽሑፎች መካከል እጅግ ጥንታዊ የሆነው የያእዛንያ ማኅተም (600 ዓ.ቅ.ክ. ገደማ) አንድ የሚናገር አውራ ዶሮ ሥዕል ይታ ይበት ነበር::

5፥19 *አስብልኝ፤* የ1፥8 ማብ ይመ፤ ከዕብ 6፥10 ጋር ያነጻ ጽሩ:: ነህምያ የጻፈው ማስታወሻ ምናልባት በቤተ መቅደሱ ውስጥ ተቀርጾ ለመታሰቢያነት ተቀምጦ ይሆናል (በዕዝራ መጽሐፍ መግቢያ ላይ፣ "ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጹና ጸሓፊው" የሚለውን ይመ):: ከነህምያ ጸሎት ጋር የሚመሳሰል ጸሎት ናቡከደነፆር አቅርቦ ነበር፤ ጸሎቱም እንዲህ የሚል ነው፤ "ጌታዬ ማርዱክ ሆይ፤ ሥራዬን በመልካም አስብልኝ፤ በጎ ሥራዬም ሁልጊዜ በፊትህ ይሁን"::

6፥1 *ለንባላጥ፣ጦብያ፣ ... ጌሳምና፤* የ2፥10፡19 ማብ ይመ::

ራቴንና የቀረ ክፍት ቦታ አለመኖሩን ሰን
ባላጥ፣ ጦብያ፣ ዓረባዊው ጌሳምና የቀሩትም
ጠላቶቻችን በሰሙ ጊዜ፣ [2]ሰንባላጥና ጌሳም
"ናና በኦኖ ሜዳ ከሚገኙት መንደሮች⁺ በአ
ንዲቱ እንገናኝ" ሲሉ ይህችን መልእክት
ላኩብኝ:: እነርሱ ግን እኔን ለመጕዳት ዐቅ
ደው ነበር:: [3]እኔም፣ "ታላቅ ሥራ እየሠራሁ
ስለሆነ፣ ወዳላችሁበት ስፍራ መውረድ
አልችልም፤ ትቼው ወደ እናንተ ወርጄ
ሥራው ለምን ይቆማል?" በማለት ይህን
መልስ የሚያደርሱ መልእክተኞችን ወደ
እነርሱ ላክሁ::
[4]አራት ጊዜም ይህንኑ ዐይነት መልእ
ክት ላኩብኝ፤ እኔም በእያንዳንዱ ጊዜ ያንኑ
መልስ ሰጠሁ::
[5]ከዚያም ሰንባላጥ ለአምስተኛ ጊዜ ያንኑ
መልእክት በረዳቱ ላከብኝ፤ በእጁም ማኅ
ተም የሌለው ያልታሸገ ደብዳቤ ይዞ ነበር፤
[6]የተጻፈበትም እንዲህ የሚል ነበር፤
"አንተና አይሁዳውያን ለማመፅ እንደ
ምትዶልቱና ቅጥሩንም እንደምትሠሩ
በሕዝቦች መካከል ተወርቶአል፤ ጌሳምም
እውነት መሆኑን አረጋግጦአል፤ ከዚህም
በተጨማሪ በተወራው መሠረት አንተ
ንጉሣቸው እንደምትሆን፣ [7]ስለ አንተም
'በአይሁድ ንጉሥ አለ' ብለው በኢየሩሳ
ሌም የሚያውጁ ነቢያትን እንኳ ሳይቀር
እንደ ሾምህ ተወርቷል፤ ይህም ነገር ለንጉሡ
መድረሱ አይቀርም፤ ስለዚህ መጥተህ በአ
ንድነት እንመካከር::"

6፥2 1ዜና8፥12
6፥5 ነህ2፥10
6፥6 ነህ2፥19
6፥10 ዘኍ18፥7
6፥12 ነህ2፥10፤ ሕዝ13፥22-23
6፥13 ኤር20፥10
6፥14 ዘፀ 15፥20፤ ነህ1፥8፤2፥10፤ ኤር23፥9-40፤ ሕዝ13፥17-23፤ ዘካ13፥2-3፤ ሐሥ21፥9፤ራእ2፥20

[8]እኔም "አንተ የምትለውን የመሰለ ምንም
ነገር አልተደረገም፤ ይህ አንተ በአእምሮህ
የፈጠርኸው ነው" ብዬ መልስ ላክሁበት::
[9]ሁሉም፣ "እጃቸው መሥራት እስኪ
ሳነው ድረስ ይዝላል፤ ሥራውም ሳይጠና
ቀቅ ይቀራል" ብለው በማሰብ ሊያስፈራሩን
ሞከሩ:: እኔ ግን፣ "አሁንም እጄን አበርታ"
ስል ጸለይሁ::
[10]አንድ ቀን ቤቱ በላዩ ላይ ተዘግቶበት
ወደ ነበረው ወደ መሔጣብኤል ልጅ ወደ
ድላያ ልጅ ወደ ሸማያ ሄድሁ፤ እርሱም፣
"ሰዎች ሊገድሉህ ይመጣሉ፤ ብእርግጥም በሌ
ሊት ሊገድሉህ ይመጣሉ፤ በእግዚአብሔር ቤት
ባለው በቤተ መቅደሱ ውስጥ እንገናኝ፤ የቤተ
መቅደሱንም በሮች እንዝጋቸው" አለኝ::
[11]እኔ ግን፣ "እንደ እኔ ያለ ሰው ሸሽቶ
ይደበቃል? ወይም ደግሞ ሕይወቱን ለማ
ዳን ሲል ወደ ቤተ መቅደስ መግባት ይገባ
ዋልን? አልሄድም!" አልሁ:: [12]በእኔ ላይ ትን
ቢት የተናገረው ጦብያና ሰንባላጥ በገንዘብ
ስለ ደለሉት እንጂ እግዚአብሔር ወደ እኔ እን
ዳልላከው ተረዳሁ:: [13]በገንዘብ የተገዛው
እኔን ለማስፈራራት ነው፤ ይኸውም ይህን
በመፈጸም ኀጢአት እንድሠራና በዚህም
መጥፎ ስም ሰጥተው ተቀባይነት እንዳይኖ
ረኝ ለማድረግ ነው::
[14]አምላኬ ሆይ፤ ስለ ፈጸሙት ድርጊት
ጦብያንና ሰንባላጥን አስብ፤ ሊያስፈራሩኝ

⁺2 የዕብራይስጡ ቅጅ፣ *ኪፍሪም* ይላል::

6፥2 *በኦኖ፤* ከኢዮጴ በደቡብ ምሥራቅ በኩል ዐሥራ አንድ ኪ.ሜ. ያህል ርቃ ሉድ አጠገብ ትገኛለች (ሉድ በአሁኑ ጊዜ ልዳ ትባላለች፤ የዕዝ 2፥33 ማብ ይመ)፤ በአካባቢው ምዕራባዊ ጫፍ ላይ ከምርኮ የተመለሱ አይሁድ ሰፍረውበታል (ነህ 7፥37፤ 11፥35):: ሜዳው ገለልተኛ ስፍራ እንዲሆንና በማንም ግዛት ውስጥ እንዳይመደብ የተወሰነ ይመስላል፤ ነህምያ ግን ይህን ጥሪ እንደ ወጥመድ ቈጥሮታል (ከዘፍ 4፥8፤ኤር 41፥1-3 ጋር ያነጻ ጽሩ)::

6፥3፤ ነህምያ እንዲህ ያለውን ቆራጥ መልስ ወዲያውኑ መስጠቱ የንቀት ሊያስመስልበት ይችላል፤ ነገር ግን በትክክል የጠላቶቹን ደባ የተረዳ ሰው ነበር:: የኢየሩሳሌምን ቅጥር ለመሥራት ከሚያስተጓጉለውና ጕልበቱን ከሚያባክን ነገር ርቆ ተገኝቶአል::

6፥4 *አራት ጊዜም፤* የነህምያ ጠላቶች ተስፋ ሳይቈርጡ መልእክቶችን ይልኩበት ነበር፤ ነህምያም እንዲህ በቀላሉ እጅ የሚሰጥ ሰው አልነበረም::

6፥5 *ያልታሸገ ደብዳቤ፤* በዚያ ዘመን ደብዳቤ የሚጻፈው በፓፒረስ ወይም በብራና ላይ ነበር፤ የደብዳቤው ምስጢር እንዲጠበቅም ተጠቅልሎ በክር ከታሰረ በኋላ በርጥብ የሸክላ ጭቃ ተጣብቆ ማኅተም ይደረግበታል፤ ሰንባላጥ ደብዳቤውን ሳያሽግ እንዲሁ የላከው፣ የመልእክቱ ይዘት በሕዝቡ ዘንድ በሰፊው እንዲታወቅ ሆን ብሎ ያደረገው ሊሆን ይችላል::

6፥6 *ንጉሣቸው፤* የፋርስ ነገሥታት ሊታገሡት የማይችሉት ነገር ቢኖር የሥልጣን ተቀናቃኛቸውን እንደ ሆነ ቤሂስቱን (ወይም ቢሲቱን) የተባለው የቀዳማዊ ዳርዮስ የቅርጽ ጽሑፍ ያስረዳል:: በአዲስ ኪዳንም ዘመን፣ የሮም ቄሳሮች በዙፋናቸው ላይ ተቀናቃኝ እንዳይነሣ ነቅተው ይጠብቁ ነበር (ዮሐ 19፥12፤ ከማቴ 2፥1-13 ጋር ያነጻጽሩ)::

*6፥7፤* በዚህ ጊዜ ትንቢት ተናጋሪው ነቢዩ ሚልክያስ ሳይሆን አይቀርም፤ ነቢዩ ስለሚመጣው መሲሕ የተናገረውን ትንቢት ሰንባላጥ ሆን ብሎ በመጠምዘዝ ስለ ነህምያ የተተነበየ አድርጎ አቀረበው::

6፥8 *ምንም ነገር፤* ነህምያ ነገር ማለሳለስ አልፈለገም፤ የቀረበበትን ክስ ውሸት መሆኑን ተናገረ:: ምናልባትም ለፋርስ ንጉሥ ያለውን ታማኝነት ለመግለጽ መልእክተኞች ልኮ ይሆናል::

6፥9 *እጃቸው ... ይዝላል፤* ተስፋ መቍረጥን የሚያመለክት አባባል ነው:: በዕብራይስጡ ትርጕም ይህ ሐረግ በዕዝ4፥4፤ ኤር 38፥4 ላይ ይገኛል፤ እንዲሁም በለኪሶ አካባቢ በተደረገው ሥነ ቅርስ ቍፋሮ፣ ይህ ሐረግ በሸክላ ስሌዳ ላይ ተጽፎ ተገኝቶአል፤ ይህም በ588 ዓ.ቅ.ክ አካባቢ እንደ ተጻፈ ይገመታል::

6፥10 *በላዩ ላይ ተዘግቶበት ወደ ነበረው ... ሸማያ፤* ሕይወቱ በአሥጊ ሁናቴ ላይ መሆኑን የሚያሳይ ምልክት ሊሆን ይችላል፤ ከዚህም የተነሣ እርሱና ነህምያ ወደ ቤተ መቅደሱ መሸሽ አስፈልጎአቸው ነበር (ስለ ሌሎች የምልክት ድርጊቶች 1ነገ 22፥11፤ ኢሳ 20፥2-4፤ ኤር 27፥2-7፤ 28፥10-11፤ ሕዝ 4፥1-17፤ 12፥3-11፤ ሐሥ 21፥11 ይመ):: ሸማያ ወደ ቤተ መቅደስ መግባት እስከ ቻለ ድረስ፣ ካህን ነበር ማለት ይቻላል፤ የጦብያ ወዳጅ (ከቍ 12 ጋር ያነጻጽሩ)፣ በነህምያ ግን ጠላት እንደ ሆነ ግልጽ ነው:: ነህምያ ወደ "እግዚአብሔር ቤት" ማለትም ወደ ቤተ መቅደሱ ሕንጻ ውስጥ ሳይሆን፣ ወደ ቤተ መቅደሱ አደባባይ ሸሽቶ የመማጸኛውን መሠዊያ (ዘፀ 21፥13-14 እና ማብ ይመ) ለመያዝ ሄዶአል ብሎ ሐሳብ ለማቅረብ ቢያንስ በሸማያ ዘንድ የሚታመን ነበር::

*6፥11፤* ሞት ዐይኑን አፍጦ ቢመጣበት እንኳ ነህምያ ሕይወቱን ለማዳን ሸሽቶ የሚደበቅ ፈሪ ሰው አልነበረም፤ ሕይወቱን ለማትረፍ ሲል ሕጉን የሚተላለፍ ሰው አልነበረም፤ ተራ ምእመን በመሆኑ፣ ወደ መቅደስ ዘሎ እንዲገባ አይፈቀድለትም (ዘኍ 18፥7):: ንጉሥ ዖዝያን ዕጣን ለማጠን ወደ ቤተ መቅደስ በገባ ጊዜ፣ በለምጽ ደዌ ተመቶ ተቀጥቶአል (2ዜና 26፥16-21)::

*6፥12፤* ሸማያ የእግዚአብሔርን ቃል የሚቃረን ሐሳብ በማቅረቡ፣ ሐሰተኛ ነቢይ መሆኑን ያሳያል (ከዘዳ 18፥20፤ ኢሳ 8፥19-20 ጋር ያነጻጽሩ)::

*6፥13፤* ነህምያ በሚደርስበት ማስፈራራት የሚናወጥ ሰው ቢሆን ኖሮ፣ መሪነቱ አጣብቂኝ ውስጥ ይገባ ነበር፤ የሕዝቡም ወኔ ይዘቅጥ ነበር::

6፥14 *አስብ፤* የ1፥8 ማብ ይመ:: *ነቢያቱን፤* የዘፀ 15፥20

የሞከሩትን ነቢያቱን ኖዓድያንና ሌሎቹን
ነቢያትም አስብ።

## የቅጥሩ ሥራ መጠናቀቅ

[15]ቅጥሩም ኤሉል በተባለው ወር ሃያ አም
ስተኛ ቀን፣ በአምሳ ሁለት ቀን ውስጥ ተጠ
ናቀቀ። [16]ጠላቶቻችን ሁሉ ይህን ሲሰሙ፣
በዙሪያችን ያሉ አሕዛብ ሁሉ ፈሩ፤ በራ
ሳቸው መተማመንም አልቻሉም፤ ምክንያ
ቱም ይህ ሥራ የተከናወነው በአምላካችን
ርዳታ መሆኑን ተገንዝበዋል።
[17]በዚያን ጊዜ የይሁዳ መኳንንት ለጦብያ
ብዙ ደብዳቤ ይልኩ ነበር፤ ከጦብያም መልስ
ይላክላቸው ነበር። [18]በይሁዳ የሚኖሩ ሰዎች
ምለውለት ነበር፤ ምክንያቱም የኤራ ልጅ
የሴኬንያ አማች ከመሆኑም በላይ ልጁ
የሆሐናን የሌራክያን ሴት ልጅ አግብቶ
ነበር። [19]ከዚህም በተጨማሪ ስለ መልካም
ሥራው በየጊዜው ይነግሩኝና እኔም ያልሁ
ትን ይነግሩት ነበር፤ ጦብያም እኔን ለማ
ስፈራራት ደብዳቤ ይልክብኝ ነበር።

7 ቅጥሩ እንደ ገና ከተሠራና መዝጊያዎቹ
ንም በየቦታቸው ከገጠምሁ በኋላ፣ በር
ጠባቂዎች፣ መዘምራንና ሌዋውያን ተመ
ደቡ። [2]በኢየሩሳሌምም ላይ ወንድሜን አና
ኒን እንዲሁም ፍጹም ታማኝና ከሌሎች
ሰዎች ይልቅ እግዚአብሔርን ይበልጥ የሚፈራ
ውን የግንቡን አዛዥ ሐናንያን ኀላፊ አደረ
ግኋቸው። [3]ለእነርሱም፣ "የኢየሩሳሌም በሮች
ፀሐይ ሞቅ እስክትል ድረስ አይከፈቱም፤
በር ጠባቂዎቹ ዘብ በሚቆሙበት ጊዜ ሁሉ፣
በሮቹን ይዘጓቸው፣ መወርወሪያም ያድርጉ
ባቸው፣ እንዲሁም ከኢየሩሳሌም ነዋሪዎች
አንዳንዶቹን በየጥበቃ ቦታቸው፣ አንዳንዶ
ቹን ደግሞ በየቤታቸው አጠገብ እንዲቆሙ
መድቡ" አልኋቸው።

## ከምርኮ የተመለሱት ሰዎች ዝርዝር

[4]ከተማዪቱ ታላቅና ሰፊ ነበረች፤ የሚኖር
ባት ሕዝብ ግን ጥቂት ሲሆን፣ ቤቶች ገና
አልተሠሩባትም ነበር። [5]ስለዚህ መኳንንቱን፣
ሹማምቱንና ተራውን ሕዝብ ሰብስቤ በየ
ቤተ ሰቡ ይመዘገቡ ዘንድ እግዚአብሔር ይህን
በልቤ አኖረ። ወደ ምድራቸው ለመመለስ
የመጀመሪያ የሆኑትን ሰዎች የትውልድ ሐረግ
መዝገብ አገኘሁ፤ ተጽፎ ያገኘሁትም ይህ
ነው።
[6]የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር ማርኮ ከወ
ሰዳቸው ምርኮኞች መካከል የተመለሱት
የአውራጃው ተወላጆች እነዚህ ናቸው፤ እያ
ንዳንዳቸውም በኢየሩሳሌምና በይሁዳ ወደ
ሚገኙት ወደየራሳቸው ከተሞች ተመለሱ፤
[7]የተመለሱትም ከዘሩባቤል፣ ከኢያሱ፣
ከነህምያ፣ ከአዛርያስ፣ ከረዓምያ፣ ከነሐማኒ፣
ከመርዶክዮስ፣ ከበላሳን፣ ከሚስጴሬት፣ ከበ
ጉዋይ፣ ከነሑምና ከበዓና ጋር ነው። የእስ
ራኤል ሰዎች ዝርዝር፤

| | |
|---|---|
| [8]ከፋሮስ ዘሮች | 2,172 |
| [9]ከሰፋጥያስ ዘሮች | 372 |
| [10]ከኤራ ዘሮች | 652 |
| [11]ከኢያሱና ከኢዮአብ ዘር የሆኑት የፈሐት ሞዓብ ዘሮች | 2,818 |
| [12]ከኤላም ዘሮች | 1,254 |
| [13]ከዛቱዕ ዘሮች | 845 |
| [14]ከዘካይ ዘሮች | 760 |
| [15]ከቢንዊ ዘሮች | 648 |
| [16]ከቤባይ ዘሮች | 628 |
| [17]ከዓዝጋድ ዘሮች | 2,322 |
| [18]ከአዶኒቃም ዘሮች | 667 |
| [19]ከበጉዋይ ዘሮች | 2,067 |
| [20]ከዓዲን ዘሮች | 655 |
| [21]በሕዝቅያስ የትውልድ ሐረግ ከአጤር ዘሮች | 98 |
| [22]ከሐሱም ዘሮች | 328 |
| [23]ከቤሳይ ዘሮች | 324 |
| [24]ከሐሪፍ ዘሮች | 112 |
| [25]ከገባዖን ዘሮች | 95 |
| [26]ከቤተ ልሔምና ከነጦፋ ሰዎች | 188 |
| [27]ከዓናቶት ሰዎች | 128 |
| [28]ከቤት አዝሞት ሰዎች | 42 |
| [29]ከቂርያት ይዓሪም፣ ከከፊራና ከብኤሮት ሰዎች | 743 |
| [30]ከራማና ከጌባ ሰዎች | 621 |
| [31] ከማክማስ ሰዎች | 122 |
| [32]ከቤቴልና ከጋይ ሰዎች | 123 |
| [33]ከሌላው ናባው ሰዎች | 52 |
| [34]ከሌላው ኤላም ዘሮች | 1,254 |
| [35]ከካሪም ዘሮች | 320 |
| [36]ከኢያሪኮ ዘሮች | 345 |
| [37]ከሎድ፣ ከሐዲድና ከኦኖም ዘሮች | 721 |
| [38]ከሴናዓ ዘሮች | 3,930 |

7፥1 1ዜና 9፥27፤ 26፥12-19፤ ነህ8፥9 መዝ68፥25
7፥2 1ነገ18፥3፤ ነህ1፥2፤2፥8፤10፥23
7፥4 ነህ11፥1
7፥6 2ዜና36፥20፤ ነህ1፥2
7፥7 1ዜና3፥19
7፥20 ዕዝ8፥6
7፥26 2ሳሙ 23፥28 1ዜና 2፥54
7፥27 ኢሱ21፥18
7፥29 ኢሱ 18፥25፡26
7፥32 ዘፍ12፥8
7፥36 ነህ3፥2
7፥37 1ዜና8፥12

ማብ ይመ።
6፥15 *ኤሉል ... ሃያ አምስተኛ፤* ይህም ጥቅምት 2 ቀን 445 ዓ.ቅ.ክ ነው። *በአምሳ ሁለት ቀን፤* በነህምያ መሪነት ሕዝቡ አንድ ልብ ሆኖ በመነሣቱ፣ ወደ አንድ መቶ አምሳ ዓመት ገደማ ፈርሶ የነበረው ቅጥር ከሁለት ወር ባነሰ ጊዜ ውስጥ ሥራው ተጠናቆአል። የሥነ ቅርስ ቍፋሮ ግኝት እንደሚያመለክተው፣ በነህምያ ዘመን የነበረው ቅጥር ከበፊቱ ይልቅ ጠባብ ነበር። ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን የቅጥሩን ሥራ የማጋጌጥና የማስማመር ተግባሩን ጨምሮ፣ ሁለት ዓመት ከአራት ወር መፍጀቱን ጽፎአል፤ የምረቃውም ሥርዐት መከናወኑ በ12፥27-47 ተገልጾአል።
6፥17-18፤ ጦብያ፣ በይሁዳ ከታወቀ ቤተ ሰብ ጋር በጋብቻ ተሳስሮአል፤ ምክንያቱም ወንድ ልጁ ዮሐናን የኢየሩሳሌም ቅጥር ሲሠራ ከረዳው ከሜሱላም ሴት ልጅ ጋር ተጋብተዋል።
7፥2 *በኢየሩሳሌምም ላይ ... ኀላፊ፤* በረፋያና በሰሎም ላይ ማለት ነው (3፥9፡12)። *አናኒን፤* የ1፥2 ማብ ይመ። *የግንቡን፤* የ2፥8፤3፥1 ማብ ይመ።
7፥3 *ፀሐይ ሞቅ እስክትል፤* በመሠረቱ የከተማው በር መከፈት የነበረበት በማለዳ ነው፤ በዚህ ጊዜ ግን እስከ ቀትር ድረስ ሳይከፈት እንዲቈይ ተደርጎአል፤ ይኸውም ሕዝቡ ከመኝታው ሳይነሣ፣ ጠላት በድንገት መጥቶ ጥቃት እንዳያደርስ ነበር።
7፥6-73፤ ከዕዝ 2 ጋር ፍጹም ተመሳሳይ ነው። በሁለቱም ክፍሎች የተዘረዘሩ የስሞችና የብዛታቸውን ልዩነት መንሥኤ ለማስተዋል የዕዝራ ም2 ማብ ይመ።
7፥7 *ነሐማኒ፤* ይህ ስም በዕዝ 2፥2 ላይ አይገኝም።

39ካህናቱ:-
በኢያሱ ቤተ ሰብ መስመር
ከዮዳኤ ዘሮች 973
40ከኢሜር ዘሮች 1,052
41ከፋስኮር ዘሮች 1,247
42ከካሪም ዘሮች 1,017
43ሌዋውያኑ:-
በቀድምኤል በኩል
በሆዳይዋ የትውልድ
መስመር የኢያሱ
ዘሮች 74
44መዘምራኑ:-
ከአሳፍ ዘሮች 148
45በር ጠባቂዎቹ:-
ከሰሎም፣ ከአጤር ፣
ከጤልሞን፣ ከዓቁብ፣
ከሐጢጣና ከሶባይ ዘሮች 138
46የቤተ መቅደሱ አገልጋዮች:-
ከሲሐ፣ ከሐሡፋ፣ ከጠብዖት ዘሮች፣
47ከኬራስ፣ ከሲዓ ፣ ከፋዶን፣
48ከልባና፣ ከአጋባ፣ ከሰምላይ ዘሮች፣
49ከሐናን፣ ከጌዴል፣ ከጋሐር ዘሮች፣
50ከራያ፣ ከረአሶን፣ ከኔቆዳ ዘሮች፣
51ከጋሴም፣ ከዖዛ፣ ከፋሴሐ ዘሮች
52ከቤሳይ፣ ከምዑኒም፣ ከንፉሰሲም
ዘሮች፣
53ከበቅቡቅ፣ ከሐቀፋ፣ ከሐርሑር ዘሮች፣
54ከበስሎት፣ ከምሒዳ፣ ከሐርሻ ዘሮች፣
55 ከቦርቆስ፣ ከሲሣራ፣ ከቴማ ዘሮች፣
56ከንስያ፣ ከሐጢፋ ዘሮች::
57የሰሎሞን አገልጋዮች ዘሮች:-
የሶጣይ፣ የሶፌሬትና፣ የፍሩዳ ዘሮች፣
58የየዕላ፣ የደርቆን፣ የጊዴል ዘሮች፣
59የሰፋጥያስ፣ የሐጢል፣ የፌከራት ዘሮች፣
የሐፂቦይምና የአሞን ዘሮች::
60የቤተ መቅደሱ አገልጋዮችና
የሰሎሞን አሽከሮች ዘሮች 392
61ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ደግሞ ከቴልሜላ፣
ከቴላሬሳ፣ ከክሩብ፣ ከአዳንና ከኢሜር የተ
መለሱ ናቸው፤ ይሁን እንጂ ዘሮቻቸው
ከእስራኤል ወገን መሆናቸውን ማስረዳት
አልቻሉም፤
62የዳላያ፣ የጦብያ፣ የኔቆዳ ዘሮች 642
63ከካህናቱ መካከል:-
የኤብያ፣ የአቆስ፣ የቤርዜሊ ዘሮች፤
ይህ ሰው የገለዓዳዊውን የቤርዜሊን ሴት
ልጅ አግብቶ በዚሁ ስም ለመጠራት በቅቶ
አል፤
64እነዚህም (የየቤተ ሰብ) ትውልድ ሐረ
ጋቸውን ከመዝገብ ለማግኘት ፈልገው
ነበር፤ ነገር ግን ሊያገኙት አልቻሉም፤ ስለ
ዚህ እንዳልነጹ ተቈጥረው ከክህነት ተከለ
ከሉ:: 65ስለዚህም አገረ ገዡ በኡሪምና በቱ
ሚም አገልግሎት የሚሰጥ ካህን እስኪነሣ
ድረስ እጅግ ከተቀደሰው ምግብ እንዳይበሉ
አዘዛቸው::
66የማኅበሩ ቍጥር በሙሉ 42,360
ነበር፤ 67ይህ 7,337 የወንድና የሴት
አገልጋዮቻ ቸውን አይጨምርም፤ 245
ወንዶችና ሴቶች መዘምራን ነበሯቸው::
68736 ፈረሶች፣ 245 በቅሎዎች[a]፣ 69435
ግመሎችና 6,720 አህ ዮችም ነበሯቸው::
70አንዳንድ የየቤተ ሰቡ አባቶች ለሥራው
መዋጮ አደረጉ፤ አገረ ገዡም 1,000 የወ
ርቅ ዳሪክ[†]፣ 50 ድስቶቹ 530 አልባሰ ተክ
ህኖ ለግምጃ ቤቱ ሰጠ:: 71ከየቤተ ሰቡ
አባቶችም አንዳንዶች ለሥራው የሚሆን
20, 000 የወርቅ ዳሪክ[‡] 2,200 የብር ምናን
ለግምጃ ቤቱ ሰጡ:: 72የቀረው ሕዝብ ባጠ
ቃላይ የሰጠው 20,000 የወርቅ ዳሪክ[ʾ]
2,000 የብር ምናንና 67 አልባሰ ተክህኖ
ነበር::
73ካህናቱ፣ ሌዋውያኑ፣ በር ጠባቂዎቹ፣
መዘምራኑና የቤተ መቅደሱ አገልጋዮች፣
ከሕዝቡም የተወሰነው ክፍልና የቀሩት እስ
ራኤላውያን በየራሳቸው ከተሞች ሰፈሩ::

## ዕዝራ ሕጉን አነበበ

ሰባተኛው ወር በደረሰና እስራኤላውያን
ሁሉ በየከተሞቻቸው በተቀመጡ ጊዜ፣
8 ሕዝቡ ሁሉ ከ"ውሃ በር" ፊት ለፊት በሚ
ገኘው አደባባይ ላይ እንደ አንድ ሰው
ተሰበሰቡ፤ ከዚያም እግዚአብሔር ለእስራ
ኤል ያዘዘውን የሙሴን ሕግ መጽሐፍ እንዲ
ያመጣ ለጸሓፊው ለዕዝራ ነገሩት::
2ስለዚህ ካህኑ ዕዝራ በሰባተኛው ወር የመ
ጀመሪያ ቀን ወንዶች፣ ሴቶችና ማስተዋል

7፥44 ነህ11፥23
7፥45 1ዜና 9፥17
7፥46 ነህ3፥26
7፥60 1ዜና9፥2
7፥65 ዘፀ28፥30
7፥71 1ዜና29፥7
7፥72 ዘፀ25፥2
7፥73 ዕዝ3፥1ነህ1፥10፤ 11፥1መዝ34፥22፤ 103፥21፤ 113፥1፥135፥1
8፥1 ዘዳ28፥61፤ 2ዜና34፥15፤ነህ3፥26
8፥2 ዘሌ23፥23-25፤ ዘኍ29፥1-6፤ ዘዳ31፥11

[a]68 አንዳንድ የዕብራይስጥ ቅጆች (እንዲሁም ዕዝ 2፥66) ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ ብዙ የዕብራይስጥ ቅጆች ግን ይህንን ጥቅስ አይጨምሩም::
[†]70 8.5 ኪሎ ግራም ያህል ነው::
[‡]71 170 ኪሎ ግራም ያህል ነው::
[ʾ]72 1.1 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው::

7፥43-74፤ የዕዝ 2፥40 ማብ ይመ::
7፥70 *ዳሪክ፤* የዕዝ 2፥69 ማብ ይመ::
7፥73 *በየራሳቸው ከተሞች ሰፈሩ፤* የዕዝ 2፥70 ማብ ይመ:: *ሰባተኛው ወር፤* ከጥቅምት እስከ ኅዳር 445 ዓ.ቅ.ል.ክ ነው::
*8፥1-18፤* ዕዝራ በ458 ዓ.ቅ.ክ. ወደ ኢየሩሳሌም ከተመለሰ በኋላ፣ በዐሥራ ሦስት ዓመት ውስጥ ስሙ ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀሰው ሕጉን ሲያነብ እንደ ሆነ የጥንት አባቶች ተናግ ረዋል:: ሕጉን እንዲያስተምር ኀላፊነት ተሰጥቶት ሳለ (ዕዝ 7፥6፡10፡14፡25-26)፣ ሕጉ ወጥቶ ሳይነገር ይህን ያህል ጊዜ መቈየቱ የሚያስደንቅ ነው::
8፥1 *ሕዝቡ ሁሉ ... ተሰበሰቡ፤* በትውፊታዊው የዘመን አቈጣጠር መጀመሪያ ላይ በሰባተኛው ወር ስለ ተሰበሰበው ጉባኤ የሚያወሳውን ከዕዝ 3፥1 ይመ፤ (የዕብራይስጡን የዘመን አቈጣጠር ሠንጠረዥ ገጽ 101 ይመ) *የሙሴን ሕግ መጽሐፍ፤* ከቍ 2-3፡5፡8-9፡13-15፡18 ጋር ያነጻጽሩ:: የዚህን መጽሐፍ ይዘት በሚ መለከት አራት ዐይነት አመለካከቶች አሉ፤ እነዚህም:- (1) የሕ ግጋት ጽሑፎች ስብስብ፣ (2) ከዘፀአትና ከዘሌ ዋውያን የተወሰዱ የክህነት ሕጎች፣ (3) በዘዳግም መጽሐፍ የሚገኙ ሕግጋት፤ (4) አም ስቱ የሙሴ መጻሕፍት ናቸው:: ዕዝራ መጻሕፍት ማለት አምስ ቱን የሙሴ መጻሕፍት ይዞ ከምርኮ መመለሱ የሚያጠራጥር አይደለም:: *ከውሃ በር ፊት ለፊት ... አደባባይ፤* ቍ16 እን ዲሁም የ3፥26፤የዕዝ10፥9 ማብ ይመ:: ምን ጊዜም አደባባዮች የሚገኙት በከተማ በሮች አቅራቢያ ነበር (2ዜና 32፥6):: *ለጸሓ ፊው፤* የዕዝ 7፥6 ማብ ይመ::
8፥2 *በሰባተኛው ወር የመጀመሪያ ቀን፤* ይህም ጥቅምት 8 ቀን 445 ዓ.ቅ.ክ ነው፤ ይኸውም በሕዝባዊው የዘመን አቈጣጠር

የሚችሉ ሁሉ በተገኙበት ጉባኤ ፊት የሕ
ጉን መጽሐፍ አመጣ:: 3እርሱም
በ"ውሃው በር" ትይዩ ወደሚገኘው አደባባይ
ፊቱን አቅንቶ፣ በወንዶች፣ በሴቶችና በሚያ
ስተውሉ ሰዎች ሁሉ ፊት በመቆም፣ ከማለዳ
ጀምሮ እስከ ቀትር ድረስ ድምፁን ከፍ
አድርጎ አነበበ፤ ሕዝቡም ሁሉ የሕጉን መጽ
ሐፍ በጥሞና አደመጡ::
4ጸሓፊው ዕዝራ ለዚሁ ተብሎ በተሠራ
ውና ከፍ ብሎ በሚገኘው የዕንጨት መድ
ረክ ላይ ቆሞ ነበር፤ በአጠገቡም በስተ ቀኙ
በኩል መቲትያ፣ ሽማዕ፣ ዓናያ፣ ኦርዮ፣ ኬል
ቅያስ፣ መዕሤያ፣ በስተ ግራው በኩል ደግሞ
ፈዳያ፣ ሚሳኤል፣ መልክያ፣ ሐሱም፣ ሐሽ
በዳና፣ ዘካርያስና ሜሱላም ቆመው ነበር::
5ዕዝራም መጽሐፉን ከፈተ፤ ከሕዝቡ ከፍ
ብሎ ቆሞ ስለ ነበረ፣ ሁሉም ያዩት ነበረ፣
በከፈተውም ጊዜ ሕዝቡ ሁሉ ቆሙ:: 6ዕዝ
ራም ታላቁን ስምላክ *እግዚአብሔርን* አመ
ሰገነ፤ ሕዝቡም ሁሉ እጆቻቸውን በማንሣት፣
"አሜን! አሜን!" ብለው መለሱ፤ ከዚህ
በኋላ በግምባራቸው ወደ መሬት ተደፍ
ተው *ለእግዚአብሔር* ሰገዱ::
7ሌዋውያኑ ኢያሱ፣ ባኒ፣ ሰራብያ፣ ያሚን፣
ዓቁብ፣ ሳባታይ፣ ሆዲያ፣ መዕሤያ፣ ቆሊ
ጣስ፣ ዓዛርያስ፣ ዮዛባት፣ ሐናን፣ ፈልያ ሕዝቡ
በዚያው ቆመው እንዳሉ ሕጉን አስረዷ
ቸው::
8ሕዝቡ የሚነበበውን መረዳት እንዲችሉ

8፥3 ነህ3፥26
8፥4 2ዜና 6፥13
8፥5 መሳ3፥20
8፥6 ዕዝ9፥5፤ 1ጢሞ2፥8
8፥7 ዘሌ10፥11፤ 2ዜና17፥7፤ዕዝ10፥23
8፥9 ዘዳ12፥7:12፤ 16፥14-15 ነህ7፥1
8፥10 ዘሌ23፥40፤ ዘዳ12፥18፤16፥11: 14-15፤1ሳሙ25፥8፤ 2ሳሙ6፥19፤አስ9፥22፤ ሉቃ14፥12-14
8፥12 አስ9፥22
8፥14 ዘፀ23፥16

ከእግዚአብሔር ሕግ መጽሐፍ ካነበቡላቸው
በኋላ ይተረጉሙላቸውና ይተነትኑላቸው ነበር::
9ከዚያም አገረ ገዢ ነህምያ፣ ካህኑና ጸሓ
ፊው ዕዝራ፣ ሕዝቡንም የሚያስተምሩት ሌዋ
ውያን፣ "ይህች ቀን *በሰምላካችሁ ለእግዚአ
ብሔር* የተቀደሰች ናት፤ አትዘኑ፤ አታልቅ
ሱም" አሏቸው፤ ምክንያቱም ሕዝቡ ሁሉ
የሕጉን ቃል በሚሰሙበት ጊዜ ያለቅሱ
ነበር::
10ነህምያም፣ "ሂዱ፤ ጥሩ ምግብ በመብ
ላት፣ ጣፋጩን በመጠጣት ደስ ይበላችሁ፤
ምንም የተዘጋጀ ነገር ለሌላቸውም ካላችሁ
ላይ ከፍላችሁ ላኩላቸው:: ይህች ቀን ስጌታ
ችን የተቀደሰች ናት፤ *የእግዚአብሔር*
ደስታ ብርታታችሁ ስለ ሆነ አትዘኑ"
አላቸው::
11ሌዋውያኑም፣ "ይህች ቀን የተቀደሰች
ስለ ሆነች ዝም በሉ፤ አትዘኑም" በማለት
ሕዝቡን ሁሉ አረጋጉ::
12ስለዚህ ሕዝቡ ሁሉ የተነገራቸውን ቃል
ተረድተው ስለ ነበረ፣ ለመብላት፣ ለመጠጣት፣
ከምግባቸው ከፍለው ለመላክና ሐሤትም
ለማድረግ ሄዱ::
13ከወሩም በሁለተኛው ቀን የየቤተ ሰቡ
ሁሉ ኀላፊዎች፣ የሕጉን ቃል ለመማር ከካ
ህናቱና ከሌዋውያኑ ጋር በጸሓፊው በዕዝራ
ዙሪያ ተሰበሰቡ:: 14እስራኤላውያን በሰባተ
ኛው ወር በሚውለው በዓል በዳስ ውስጥ
እንዲቀመጡ *እግዚአብሔር* በሙሴ አማካይ

---

የአዲሱ ዓመት በዓል ማክበሪያ ቀን ነበር (የዘሌ 23፥24 ማብ ይመ)፤ በዓሉም መለከት የሚነፋበት ቀን በመባል ሲታወቅ (ዘኍ 29፥1-6)፣ በዚህ ቀን ሥራ ሁሉ ቆሞ፣ የተቀደሰ ጉባኤ ይደረግ ነበር:: *ሴቶችና፤* 10፥28 ይመ:: ሴቶች አብዛኛውን ጊዜ በጉባኤ አይሳተፉም ነበር (የዘፀ 10፥11 ማብ ይመ)፤ ይሁን እንጂ እንዲህ ባለው የተቀደሰ በዓል ላይ ከሕፃናቻቸው ጋር ይገኙ ነበር (ዘዳ 31፥12፤ ኢሱ 8፥35፤ 2ነገ 23፥2)::

8፥3 *ከማለዳ ጀምሮ እስከ ቀትር ድረስ፤* ሕዝቡ ቅዱሳት መጻሕፍት እየተነበቡ ትርጕማቸው በሚብራራበት ጊዜ፤ በሚገባ እያደመጡ (ቍ 7-8:12)፣ ለአምስት ወይም ለስድስት ሰዓት ያህል ይቆሙ እንደ ነበር ግልጽ ነው (ቍ 5:7):: *ድምፁን ከፍ አድርጎ አነበበ፤* ዘፀ 24፥7፤ ሐሥ 8፥30 ይመ::

8፥4 *የዕንጨት መድረክ፤* እንዲህ ዐይነት መድረክ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሲጠቀስ ይህ የመጀመሪያው ነው፤ መድረኩም ዕዝራን ጨምሮ ዐሥራ አራት ሰው መሸከም ይችል ነበር::

8፥5 *መጽሐፉን፤* ጥቅልል የብራና መጽሐፍ ነው (የዘፀ 17፥14 ማብ ይመ):: *ሕዝቡ ሁሉ ቆሙ፤* ከዚህ ጥቅስ የተነሣ የአይሁድ ሃይማኖት መምህራን (ረበናት)፣ የሕጉ መጽሐፍ በሚነበብበት ጊዜ ጉባኤው መቆም እንዳለበት ወስነዋል:: በምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናትም ቅዳሴ በሚካሔድበት ጊዜ ተጀምሮ እስከ ሚፈጸም ድረስ ሕዝቡ መቆሙ የተለመደ ነው::

8፥6 *እጆቻቸውን በማንሣት፤* ዘፀ 9፥29 እና፤ ማብ ይመ፤ እንዲሁም መዝ28፥2፤ 134፥2፤ 1ጢሞ 2፥8 ይመ:: *አሜን! አሜን!* የዘዳ 27፥15፤ሮሜ 1፥25 ማብ ይመ:: ቃሉ መደጋገሙ ከአባባሉ በስተ ጀርባ ያለው ስሜት ከበድ ያለ መሆኑን ያመለክታል (ስለ ሌላ ድግግሞሽ ዘፍ 22፥11 እና ማብ ይመ፤ ከ2ነገ 11፥14፤ ከሉቃ 23፥21 ጋር ያነጻጽሩ):: *ሰገዱ፤* የዕብራይስጡ ቃል፣ በመሬት ላይ መደፋትን ያመለክታል:: በግል አምልኮ ወይም በስግደት ጊዜ ወደ ምድር መደፋት የተለመደ ነበር፤ ለምሳሌ የአብርሃምን ሎሌ (ዘፍ 24፥52)፣ ሙሴን (ዘፀ 34፥8)፣ ኢያሱን (ኢሱ 5፥14) እንዲሁም ኢዮብን (ኢዮ1፥20) መጥቀስ ይቻላል:: በዘፀአት መጽሐፍ ውስጥ ሦስት ጊዜ ይህን መሰል ስግደት ሲሰጥ እናያለን (4፥31፤12፥27፤ 33፥10):: በ2ዜና 20፥19 ላይ ኢዮሣ

ፍጥና ሕዝቡ የድሉን የተስፋ ቃል በሰሙ ጊዜ፣ "በእግዚአብሔር ፊት ወደቁ"::

8፥7 *አስረዷቸው፤* ቍ 8፤ ዕዝ 8፥16 እና ማብ ይመ፤ መዝ 119፥34:73:130፤ኢሳ 40፥14 ይመ::

8፥8 *ካነበቡላቸው፤* የቍ 3 ማብ ይመ:: *ይተረጉሙላቸውና፤* በረበናት ትውፊት መሠረት ይህ ሐረግ ከዕብራይስጥ ወደ አረማይስጥ ትርጕም መተርጐምን ያመለክታል:: "ታርጉም" የተባለው ቅጅ በአረማይስጥ ቋንቋ የተጻፈ ሲሆን፣ የብሉይ ኪዳንን መጻሕፍት ወይም አንዱን ክፍል ነጻ በሆነ መንገድ ከዕብራይስጥ ወደ አረማይስጥ ቋንቋ መተርጐም ነበር:: ይሁን እንጂ በዚህ ጊዜ "የታርጉም" ቅጅ ተዘጋጅቶ ነበር ለማለት ምንም ማስረጃ የለም:: እጅግ የቈየ ነው የሚባለው የ"ታርጉም" ቅጅ የመጽሐፈ ኢዮብ ሲሆን፣ ይህም ከቍምራን የተገኘ ነው፤ ቅጅው ተጻፈ ተብሎ የሚገመተውም ከ150-100 ዓ.ቅ.ክ አካባቢ ነው:: ከትንቢተ ዳንኤል፣ ከመጽሐፈ ዕዝራና ከመፅሐፈ ነህምያ በስተቀር እያንዳንዱ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ በ"ታርጉም" ተተርጕመው ይገኛሉ:: *መረዳት፤* ቍ 12 ይመ::

8፥9 *ነህምያ ... ዕዝራ፤* ሁለቱም በአንድ ዘመን እንደ ኖሩ በግልጽ የሚያሳይ ክፍል ነው (12፥26:36 ይመ):: *አትዘኑ፤* ዕዝ 10፥6 እና ማብ፤ አስ 9፥22፤ ኢሳ 57፥18-19፤ ኤር 31፥13 ይመ:: *አታልቅሱም፤* 1፥4፤ ዕዝ 3፥13 እና ማብ፤ 10፥1 ይመ::

8፥10 *ጥሩ ምግብ፤* ጣዕም ያለውና ደስ የሚያሰኝ የድግስ መብል ማለት ነው:: ለመሥዋዕት የሚቀርቡት እንስሳት ስብ ደስ የሚያሰኝ የሚቃጠል መሥዋዕት (ዘሌ 1፥8:12)፣ የደኅንነት መሥዋዕት (ዘሌ 3፥9-10)፣ የኀጢአት መሥዋዕትና (ዘሌ 4፥8-10) የበደል መሥዋዕት (ዘሌ 7፥3-4) ሆኖ ለእግዚአብሔር ይቀርብ ነበር:: በዚህ ምክንያት ስቡ አይበላም ነበር:: *ምንም ... ለሌላቸውም ካላችሁ ላይ ... ላኩላቸው፤* ምስኪኖችን በደስታ ወቅት ማስታወስ በእግዚአብሔር ሕዝብ ዘንድ የተለመደ ነበር (2ሳሙ 6፥19፤ አስ 9፥22፤ ከ1ቆሮ 11፥20-22፤ ከያዕ 2፥14-16 ጋር ያነጻጽሩ)::

8፥14 *በዳስ፤* የዘፀ 23፥16፤ የዘሌ 23፥34:42፤ የዮሐ 7፥37-39 ማብ ይመ::

ነት የሰጠውን ትእዛዝ በሕጉ ውስጥ ተጽፎ
አገኙ፤ [15]ስለዚህ በየከተሞቻቸውና በኢየሩ
ሳሌም ይህን ቃል እንዲያውጁና እንዲያሠ
ራጩ እንዲህ በማለት አዘዟቸው፤ “ወደ
ኰረብቶች ውጡ፤ ከዘይትና ከበረሓ ወይራ፣
ከባርስነት፣ ከዘንባባና ከለምለም ዛፎች ቅር
ንጫፎችን አምጡ[1]፤ በተጻፈው መሠረት
ዳሶችን ሥሩ።”

[16]ስለዚህ ሕዝቡ ወጥተው ቅርንጫፎች
አመጡ፤ እያንዳንዳቸውም በየቤታቸው ጣራ
ስገነት፣ በየግቢያቸው፣ በእግዚአብሔር ቤት
አደባባይ፣ በ“ውሃ በር” አደባባይና በኤፍ
ሬም በር አደባባይ ላይ ዳስ ሠሩ። [17]ከም
ርኮ የተመለሰውም ማኅበር ሁሉ ዳሱን
ሠርቶ ተቀመጠ። ከነዌ ልጅ ከኢያሱ
ዘመን ጀምሮ እስከዚያን ጊዜ ድረስ እስራ
ኤላውያን እንደዚያ አድርገው በዓሉን አክ
ብረው አያውቁም፤ ደስታቸውም ታላቅ
ነበር።

[18]ከመጀመሪያው ቀን ጀምሮ እስከ መጨ
ረሻው ድረስ፣ ዕዝራ በየዕለቱ ከእግዚአብሔር
ሕግ መጽሐፍ ያነብ ነበር። እነርሱም በዓ
ሉን ሰባት ቀን አከበሩ፤ በስምንተኛውም
ቀን በሕጉ መሠረት የተቀደሰ ጉባኤ
ተደረገ።

8፥16 2ዜና25፥23፤ ነህ3፥26
8፥17 1ነገ8፥2፤ 2ዜና7፥8፤8፥13፤ ሆሴ12፥9
8፥18 ዘሌ 23፥36፤ ዘዳ28፥61፤31፥11፤ 33፥10፤ዕዝ3፥4
9፥1 ዘሌ 26፥40-45 ኢሱ7፥6፤2ዜና7፥14-16
9፥2 ዘሌ 26፥40፤ ዕዝ6፥21፤10፥11፤ ነህ10፥28፤13፥3፤30፤ መዝ106፥6
9፥4 አስ10፥23
9፥5 2ሳሙ7፥26፤ መዝ78፥4
9፥6 ዘፍ1፥1፤ ዘፀ8፥19፤ዘዳ6፥4፤ 10፥14፤መዝ95፥5፤ 103፥20፤146፥6፤ 148፥2፤ኢሳ37፥16፤ 40፥26፤45፥12፤ ዮና1፥9፤ሐሥ4፥24፤ ራእ10፥6

## እስራኤላውያን ኀጢአታቸውን ተናዘዙ

9 በዚያኑ ወር ሃያ አራተኛ ቀን እስራ
ኤላውያን ጾመው፣ ማቅ ለብሰው፣ በራ
ሳቸው ላይ ትቢያ ነስንሰው በአንድነት
ተሰበሰቡ። [2]የእስራኤላውያን ዘር የሆኑትም
ራሳቸውን ከባዕዳን ሁሉ ለዩ። ቆመውም
ኀጢአታቸውንና የአባቶቻቸውን በደል ተና
ዘዙ። [3]በያሉበትም ቦታ ቆመው ከአምላካቸው
*ከእግዚአብሔር* ሕግ መጽሐፍ ሩብ ቀን አነ
በቡ፤ የቀረውን ሩብ ቀን ደግሞ ንስሓ በመግ
ባትና ለአምላካቸው *ለእግዚአብሔር* በመስገድ
አሳለፉ። [4]ሌዋውያኑ ኢያሱ፣ ባኒ፣ ቀድም
ኤል፣ ሰበንያ፣ ቡኒ፣ ሰራብያ፣ ባኒ፣ ክናኒ፣
በመውጫ ደረጃዎች ላይ ቆሙ፤ ወደ
አምላካቸው ወደ *እግዚአብሔርም* በታላቅ
ድምፅ ጮኹ። [5]ሌዋውያኑ ኢያሱ፣ ቀድም
ኤል፣ ባኒ፣ አሰበንያ፣ ሰራብያ፣ ሆዲያ፣
ሰበንያና ፈታያ፣ “ተነሡታችሁ ቁሙ፤ ከዘለዓ
ለም እስከ ዘለዓለም የሚኖረውን አምላካ
ችሁን *እግዚአብሔርን* ወድሱ” አሉ።

“ክቡር ስምህ የተመሰገነ ይሁን፤ ከምስ
ጋና ሁሉና ከውዳሴም በላይ ከፍ ከፍ ይበል።
[6]አንተ ብቻ *እግዚአብሔር* ነህ። ሰማያትን፣
ከሰማያት በላይ ያሉትን ሰማያትና የከዋክ
ብታቸውን ሰራዊት ሁሉ፣ ምድርንና በላ
ይዋ ያለውን ሁሉ፣ ባሕሮችንና በውስጣቸው

[1]15 ዘሌ23፥37-49 ይመ

8፥15 *ወይራ፤* በሜድትራኒያን አካባቢ ባሉ አገሮች በብ ዛት የሚገኝ ዛፍ ነው። እስራኤላውያን ምድሪቱን ከመውረራቸው በፊት በከነዓን ምድር ይበቅል ነበር (ዘዳ 8፥8)። አንድ የወይራ ዛፍ የተሟላ ዕድገት ለማግኘት ሠላሳ ዓመት ስለሚፈጅበት፣ ከፍተኛ ጥንቃቄና እንክብካቤ ያስፈልገዋል። ከበረሓ *ወይራ፤* በቀሙ፣ “የዘይት ዛፍ” ማለት ነው፤ አብዛኛውን ጊዜ እንደ ዱር የወይራ ዛፍ ይቈጠር ነበር፤ የበረሓ ዕንጨት ለቤተ መቅደሱ ሥራ እምብዛም የማይፈለግ ሆኖ፣ የዘይት ዛፍ ግን ለቤተ መቅደሱ ግንባታ እንኳ እንዲውል መደረጉ አጠያያቂ ነው (1ነገ 6፥23፡ 31-33)። በተጨማሪም የበረሓው ወይራ ብዙ ዘይት አይወጣውም፤ አባባሉ ሙጫነት ያለውን የጥድ ዛፍ ዘር ሊያመለክት ይችላል። *ከባርሰነት፤* ከዓመት እስከ ዓመት አረንጓዴ የሆነና ጥሩ መዐዛ ያለው የዛፍ ዘር ነው (ኢሳ 41፥19፤ 55፥13፤ ዘካ 1፥8፡10-11)። *ከዘንባባ፤* በኢያሪኮ አካባቢ ብዙ ዘንባባ ነበር (ዘዳ 34፥3፤ 2ዜና 28፥15)። *ከለምለም፤* ከሕዝ 6፥13፤ 20-28 ጋር ያነጻጽሩ። አይሁድ የዳስን በዓልን በሚያከብሩበት ጊዜ፣ በቀኝ እጃቸው ከዘንባባ፣ ከባርሰነትና ቅርንጫፎቻቸው ሰፋፊ ከሆኑ የውሃ ዳር ተክሎች የተሠሩ ዝንጥጣፊዎችን፣ በግራ እጃቸው ደግሞ በፖለስ ቲና የታወቀውን የፍራፍሬ ዛፍ ቅርንጫፍ ይዘው ያወዛውዙ ነበር።

8፥16 *በእግዚአብሔር ቤት አደባባይ፤* የ13፥7 ማብ ይመ። ሕዝቅኤል በራእይ ያየው ቤተ መቅደስ የውስጥና የውጭ አደባባዮች ነበሩት (በገጽ 1280 ላይ የሚገኘውን ሥዕል ይመ)። ሕዝ ቅኤል ያየው ቤተ መቅደስ ከሰሎሞን ቤተ መቅደስ ጋር በጥቂቱ ይመሳሰላል፤ የሰሎሞን ቤተ መቅደስ ካህናቱ ሥራቸውን የሚከያ ናውኑበት የውስጥ አደባባይና የውጭ አደባባይ ነበረው። (1ነገ 6፥36፤ 7፥12፤ 2ነገ 21፥5፤ 23፥12፤ 2ዜና 4፥9፤ 33፥5)። የአዲስ ኪዳኑ ዘመን ቤተ መቅደስ የሴቶች አደባባይ፣ የእስራኤል አደባ ባይና የካህናት አደባባይ እየተባለ በንኡሳን ክፍሎች የሚከፈል የውስጥ አደባባይና የአሕዛብ አደባባይ ነበረው። በቁምራን የተገኘው የቤተ መቅደስ ጥቅልል ብራና፣ እግዚአብሔር ለቤተ መቅደሱ አሠራር ንድፍ አድርጎ የሰጠውን ትክክለኛ ምስል የያዘ ነው። በዚህ ጥቅልል ብራና ላይ ከ40-46 ባሉት ዐምዶች ስለ ውጪው አደባባይ እንዲህ የሚል ተጽፎ ይገኛል፤ “በሦስተኛው ደርብ ጣራ ላይ ምሰሶዎች አሉ፤ በእነዚህም ምሰሶዎች ላይ ለዳስ በዓል የሚሆን መጠለያ ይቀለሳል፤ በውስጡ የሚቀመጡትም ሽማግሌ ዎች፣ የነገድ አለቆች፣ ሻለቆችና መቶ አለቆች ናቸው።” *በኤፍ ሬም በር፤* የጥንቱ የኢየሩሳሌም ቅጥር በር ነው (የ3፥6 ማብ ይመ፤ እንዲሁም 2ነገ 14፥13 ይመ)። ይህ በር በነህምያ ተጠ ግኖአል (12፥39)።

8፥17 *ከኢያሱ ዘመን ጀምሮ እስከዚያን ጊዜ ድረስ፤* አባ ባሉ ከኢያሱ ዘመን ጀምሮ የዳስ በዓል ተከብሮ አያውቅም ለማ ለት አይደለም፤ ምክንያቱም ንጉሥ ሰሎሞን ያሠራው ቤተ መቅደስ ተመርቆ ከተከፈተበት ጊዜና (2ዜና 7፥8-10) ከምርኮ ከተመለሱ በኋላ እንዲህ ዐይነቱ በዓል ተከብሮ ነበረ (ዕዝ 3፥4)። ነገር ግን በዓሉ በዚህ ዐይነት ድምቀትና ደስታ አለመከበሩን ለመግለጽ ነው (ከ2ዜና 30፥26፤ 35፥18 ጋር ያነጻጽሩ)።

8፥18 *ጉባኤ፤* ዘኍ 29፥35 ይመ።

*9፥1-37፤* የመጽሐፈ ዕዝራ፣ የመጽሐፈ ነህምያና የትንቢተ ዳንኤል ዘጠነኛ ምዕራፎች ስለ ሕዝቡ ኀጢአት የቀረበውን ኑዛዜና የእግዚአብሔርን ጸጋ ለማግኘት የተደረገውን ጸሎት የያዙ ናቸው።

9፥1 *ሃያ አራተኛ ቀን፤* ጥቅምት 30 ቀን 445 ዓ.ቅ.ክ ነው፤ በዐሥረኛው ቀን እንደሚውለው እንደ ስረየት ቀን ሁሉ (ዘሌ 16፥29-30)፣ በዚያው መንፈስ የሚዋልበት የንስሓ ዕለት ነው። *ጾመው፣ ማቅ ... ትቢያ ነስንሰው፤* የዘፍ 37፥34፤ ዕዝ 8፥23፤ 10፥6፤ የኢል 1፥13-14 ማብ ይመ።

9፥3 *ሩብ ቀን፤* ወደ ሦስት ሰዓት ገደማ ነው።

*9፥5-37፤* ከመዝሙረ ዳዊት ውጭ ከሚገኙና እጅግ ውብ ከሆኑ የጸሎት ዐይነቶች አንዱ ነው፤ ይህም፦ (1) በፍጥረት ሥራ ውስጥ (ቍ 6)፣ (2) ለአብርሃም በተደረገው ቃል ኪዳን (ቍ 7-8)፣ (3) በቀይ ባሕርና በግብፅ በተፈጸመው ታሪክ (ቍ 9-11)፣ (4) በበረሓው ጕዞና በሲና ተራራ ላይ በነበረው ሁኔታ (ቍ 12-21)፣ (5) ከነዓን በተወረረች ጊዜ በነበረው ሁኔታ (ቍ 22-25)፣ (6) በመሳፍንት (ቍ 26-28)፣ (7) በነቢያት አማካይነት (ቍ 29-31) እንዲሁም (8) በጊዜው በነበረው ሁኔታ (ቍ 32-37) የእግዚአብሔር ጸጋ መገለጡን የሚያመለክት ነው። ከመዝ 78፥105-106 ጋር ያነጻጽሩ።

9፥6 *አንተ ብቻ እግዚአብሔር ነህ፤* ዘዳ 6፥4 ላይ ካለው ጋር አንድ ባይሆንም፣ ጸሎቱ ተመሳሳይ በሆነ አገላለጽ ይጀምራል (ከ2ነገ 19፥15፤ ከመዝ 86፥10 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ዘዳ 6፥4 እስራ ኤል በአንድ እግዚአብሔር ላይ ብቻ የነበራትን ጽኑ እምነት ይገልጻል። *ከሰማያት በላይ ያሉትን ሰማያትና፤* ዘዳ 10፥14፤ 1ነገ 8፥27፤ 2ዜና 2፥6፤ መዝ 148፥4 ይመ። *የሰማይ ሰራዊትም*

ያሉትንም ሁሉ ፈጥረሃል። ለሁሉም ሕይ
ወትን ትሰጣለህ፤ የሰማይ ሰራዊትም
ይሰግዱልሃል።
7“አብራምን የመረጥኸውና ከከለዳውያን
ዑር አውጥተህ አብርሃም የሚል ስም የሰጠ
ኸው አንተ እግዚአብሔር አምላክ ነህ።
8ልቡ ለአንተ የታመነ ሆኖ ስላገኘኸውም፣
የከነዓናውያንን የኬጢያውያንን፣ የአሞራ
ውያንን፣ የፌርዛውያንን፣ የኢያቡሳውያን
ንና የጌርጌሳውያንን ምድር ለዘሮቹ ለመ
ስጠት ከእርሱ ጋር ቃል ኪዳን ገባህ፤ ጻድቅ
ስለ ሆንህም የሰጠኸውን ተስፋ ጠበቅህ።
9“አንተ በግብፅ የአባቶቻችንን ሥቃይ
አየህ፤ በቀይ ባሕርም[9] ጩኸታቸውን ሰማህ።
10ታምራታዊ ምልክቶችንና ድንቆችን በፈ
ርዖንና፣ በሹማምቱ ሁሉ፣ በምድሩም ሕዝብ
ሁሉ ላይ ላክህ፤ ይህንም ያደረግኸው ግብፃ
ውያን እንዴት በእብሪት እንዳስጨነቋ
ቸው ስላወቅህ ነው። እስከ ዛሬም የሚጠራ
ስም ለራስህ እንዲኖርህ አደረግህ። 11በደረቅ
ምድር እንዲሻገሩ ባሕሩን በፊታቸው ከፈ
ልህ፤ ያሳደዷቸውን ግን በኀይለኛ ውሃ ውስጥ
እንደሚጣል ድንጋይ ወደ ጥልቁ ውስጥ ወረ
ወርሃቸው። 12ቀን በደመና ዐምድ፣ በሚሄዱ
በት መንገድ ታበራላቸውም ዘንድ ሌሊት
በእሳት ዐምድ መራሃቸው።
13“በሲና ተራራ ላይ ወረድህ፤ ከሰማይም
ተናገርሃቸው። ትክክለኛ ደንቦችንና እውነ
ተኛ ሕጎችን፣ መልካም ሥርዐቶችንና ትእ
ዛዞችን ሰጠሃቸው። 14የተቀደሰች ሰንበትህን
አስታወቅሃቸው፤ ትእዛዞችን፣ ሥርዐቶችንና
ሕጎችን በባሪያህ በሙሴ አማካይነት ሰጠ
ሃቸው። 15በተራቡ ጊዜ ከሰማይ መና ሰጠ
ሃቸው፤ በተጠሙም ጊዜ ከዐለት ውሃ
አፈለቅህላቸው፤ ልትሰጣቸው በተዘረጋች
እጅ ወደ ማልህላቸውም ምድር ገብተው
እንዲወርሱ አዘዝሃቸው።
16“እነርሱና አባቶቻችን ግን ትምክሕተኞ
ችና ዐንገተ ደንዳኖች ሆኑ፤ ትእዛዞችህንም
አልፈጸሙም። 17ለመስማት አልፈለጉም፤

9፥7 ዘፍ11፥28፤ 16፥11፤17፥5
9፥8 ዘፍ15፥6፤ 15፥18-21፤ ኢሱ21፥45፤ ዕዝ9፥1:15
9፥9 ዘፀ2፥23-25፤ 3፥7፤14፥10-30
9፥10 ዘፀ3፥20፤ 6፥6፤10፥1፤ ዘኍ6፥27፤ መዝ74፥9፤ ኤር32፥20፤ዳን9፥15
9፥11 ዘፀ14፥28፤ 15፥4-5፤ 5፤10መዝ78፥13፤ ዕብ11፥29
9፥12 ዘፀ13፥21፤ 15፥13፥ዘዳ1፥33
9፥13 ዘፀ19፥11: 19፤20፥1:22፤ ዘዳ4፥7-8፤ መዝ119፥137
9፥14 ዘፍ2፥3፤ ዘፀ20፥8-11
9፥15 ዘፍ14፥22፤ ዘፀ16፥4፤17፥6፤ ዘኍ20፥7-13፤ ዘዳ1፥8:21፣ መዝ78፥24-25፤ ዮሐ6፥31
9፥16 ዘፀ32፥9፤ ዘዳ1፥26-33፤ 31፥29፤ኤር7፥26፤ 17፥23፥19፥15
9፥17 ዘፀ22፥27፤ 34፥6፤ዘኍ14፥1-4: 17-19፤ ዘዳ4፥31፤ መሳ8፥34፤መዝ77፥1 1፤78፥11:12:42፤ 86፥15፤103፥8፤ 105፥5፤ 106፥7፤ 130፥4፤ ኤር7፥26፤19፥15፤ ሕዝ5፥6፤ዳን9፥9፤ ናሆ1፥3
9፥18 ዘፀ20፥23፤ 32፥4
9፥19 ዘፀ13፥21:22

በመካከላቸውም ያደረግሃቸውን ታምራት
ማስታወስ አልቻሉም። አንገታቸውን አደነ
ደኑ፤ በዐመፃቸውም ወደ ባርነታቸው ለመ
መለስ መሪ ሾሙ። አንተ ግን ይቅር ባይ
አምላክ፣ ቸርና ርኅሩኅ፣ ለቍጣም የዘገ
የህና ምሕረትህ የበዛ ነህ። ስለዚህ አልተ
ውሃቸውም፤ 18የጥጃ ምስል ለራሳቸው አቅ
ልጠው፣ ‘ከግብፅ ያወጣህ አምላክ ይህ ነው’
ባሉና አስጸያፊ የስድብ ቃል በተናገሩ ጊዜ
እንኳ አልተለየሃቸውም።
19“ከርኅራኄህ ብዛት የተነሣ በምድረ
በዳ አልተውሃቸውም፤ ቀን የደመናው ዐምድ
በመንገዳቸው ላይ መምራቱን፣ ሌሊትም
የእሳቱ ዐምድ በሚሄዱበት ላይ ማብራቱን
አላቆመም። 20ያስተምራቸው ዘንድ ቸር መን
ፈስህን ሰጠሃቸው፤ መናውን ከአፋቸው
አልከለከልህም፤ በተጠሙ ጊዜ ውሃ ሰጠሃ
ቸው። 21በምድረ በዳ አርባ ዓመት መገብ
ሃቸው፤ ምንም ያጡት አልነበረም፤ ልብሳ
ቸው አላለቀም፤ እግራቸውም አላበጠም።
22“በሩቅ የሚገኙትን ድንበሮች እንኳ ሳይ
ቀር፣ መንግሥታትንና አሕዛብን ሰጠሃቸው።
የሐሴቦን ንጉሥ የሴዎንን ምድር፣ የባሳን
ንጉሥ የዐግን ምድር ወረሱ። 23ወንዶች
ልጆቻቸውን እንደ ሰማይ ከዋክብት አበዛ
ሃቸው፤ አባቶቻቸው ገብተው እንዲወርሱ
ወዳዘዝሃቸውም ምድር አገባሃቸው። 24በም
ድሪቱ ወንዶች ልጆቻቸው ገቡባት፤ ወረ
ሷትም። በምድሪቱ ላይ ይኖሩ የነበሩትን
ከነዓናውያን በፊታቸው አንበረከክህ፤ ያሻ
ቸውን ያደርጉባቸው ዘንድ ከነዓናውያንን
ከንጉሦቻቸውና ከምድሪቱ ሕዝቦች ጋር በእ
ጃቸው አሳልፈህ ሰጠሃቸው። 25የተመሸጉ ከተ
ሞቻቸውንና የሰባውን ምድር ያዙ፤ በመል

9፥20 ዘፀ16፥15፤ 17፥6፤ዘኍ9፥17፤ 1፥17፤ መዝ23፥3፤143፥10፤ ኢሳ 63፥11-14፤ሐጌ2፥5፤ ዘካ4፥6 9፥21 ዘፀ16፥35፤ ዘዳ2፥7፤8፥4 9፥22 ዘኍ21፥21: 33፤ዘዳ2፥26፤3፥11፣ 9፥23 ዘፍ12፥2፤ ዘሌ26፥9፤ ዘኍ10፥36፤ 9፥24 ኢሱ 11፥23፤ መሳ4፥23፤ 2ዜና14፥13 9፥25 ዘፀ18፥9፤ ዘዳ6፥10-12፤8፥8-11፤11፥11፤ 2፥12-15፤መዝ23፥6፤ 25፥7፤69፥16

[9] ዕብራይስጡ፣ ያም ሱፍ ይላል፤ ይኸውም የደንገል ባሕር ማለት ነው።

*ይሰግዱልሃል፤* መዝ 89፥5-7 ይመ።

9፥7 *ከከለዳውያን ዑር፤* የዘፍ 11፥28 ማብ ይመ። *አብርሃም የሚል ስም የሰጠኸው፤* የዘፍ 17፥5 ማብ ይመ።

9፥8 *የታመነ፤* ሮሜ4፥16-22ን ከያዕ2፥21-23 ጋር ያነጻጽሩ። *ከእርሱ ጋር ቃል ኪዳን ገባህ፤* የዘፍ 15፥18 ማብ ይመ። *የከነዓ ናውያንን ... የጌርጌሳውያንን፤* የዘፍ 10፥6:15-18፤13፥7፤ የዘፀ 3፥8፤ የዕዝ 9፥1 ማብ ይመ።

9፥9 *በቀይ ባሕርም፤* የዘፀ 13፥18፤ 14፥2 ማብ ይመ።

9፥11 *ባሕሩን...ከፈልህ፤* ዘፀ 14፥21-22፤1ቆሮ 10፥1 ይመ።

9፥13 *ሕጎችን፤* ይህን ለመግለጽ የገባው የዕብራይስጡ ነጠላ ስም “ቶራ” የሚል ሲሆን፣ ትርጕሙም “መመሪያ” “ሕግ” ማለት ነው፤ ከጊዜ በኋላ አምስቱን የሙሴ መጻሕፍት የሚያመለክት ሆኖአል።

9፥14 *የተቀደሰች ሰንበትህን፤* ረበናቱ የአይሁድ ሕግ መምህራን፣ “ሰንበት ከሌሎች ሕግጋት ሁሉ ትበልጣለች” ይላሉ። (10፥31-33፤ 13፥15-22) ይመ።

9፥15 *ከሰማይ መና፤* የዘፀ 16፥4 ማብ ይመ፤ *ከዐለት ውሃ፤* የዘፀ 17፥6 ማብ ይመ። *በተዘረጋች ... ማልህላቸውም፤* ዘፍ 14፥22 እና ማብ ይመ፤ እንዲሁም 22፥15-17፤ ዘፀ 6፥8፤ ሕዝ 20፥6፤ 47፥14 ይመ።

9፥16 *ዐንገተ ደንዳኖች፤* ቍ 17:29 ይመ፤ እንዲሁም የ3፥5፤ የዘፀ 32፥9 ማብ ይመ።

9፥17 *መሪ ሾሙ፤* ይህን ያደረጉበት ዓላማ በዘኍ 14፥4 ላይ ተጽፎ ይገኛል። *ቸርና ... ምሕረትህ የበዛ፤* የዘፀ 34፥6-7 ማብ ይመ።

9፥18 *የስድብ ቃል፤* ቍ 26፤ ሕዝ 35፥12 ይመ።

9፥19 *ከርኅራኄህ ብዛት፤* ቍ 27-28 ይመ፤ እንደ እናት የሚያሳሳ ፍቅር ማለት ነው (የዘካ 1፥16 ማብ ይመ)።

9፥20 *ያስተምራቸው ዘንድ ... መንፈስህን፤* ዘፀ 31፥3 ይመ።

9፥21 *ልብሳቸው አላለቀም፤* የእግዚአብሔርን ልዩ መግቦት ያመለክታል (ዘዳ 8፥4፤ 29፥5 ይመ፤ ከኢሱ 9፥13 ጋር ያነጻጽሩ)። *አላበጠም፤* በሌላ አባባል፣ “ውሃ አልቋጠረም” ማለት ነው፤ ይህን ለመግለጽ የገባው የዕብራይስጡ ቃል እዚህና በዘዳ 8፥4 ላይ ብቻ ይገኛል።

9፥22 *የሴዎንን ... የዐግን፤* ዘኍ 21፥21-35 ይመ።

9፥23 *እንደ ... ከዋክብት አበዛሃቸው፤* የዘፍ 13፥16፤15፥5፤ 22፥17 ማብ ይመ።

*9፥25፤* ዘዳ 6፥10-12 እና ማብ ይመ፤ ኢሱ 24፥13 ይመ። *የሰባውን፤* ቍ 35 ይመ፤ ከዘኍ 14፥7፤ ከዘዳ 8፥7፤ ከኢሱ 23፥1 ጋር ያነጻጽሩ። *የተቈፈሩ የውሃ ጕድጓዶቻቸውን፤* በዓመቱ ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ ዝናብ ስለማይኖር፣ እያንዳንዱ ቤተ ሰብ ከብዙ በጥቂቱ የራሱ የሆነ የውሃ ጕድጓድ ወይም የክረምቱን

ካም ነገር ሁሉ የተሞሉ ቤቶቻቸውን፣ የተ
ቈፈሩ የውሃ ጕድጓዶቻቸውን፣ የወይን ተክ
ላቸውን፣ የወይራ ዛፎቻቸውንና ስፍር ቍጥር
የሌላቸውን የፍሬ ዛፎች ያዙ:: እስኪጠግቡ
በሉ፤ ወፈሩም፤ በታላቅ በጎነትህም ደስ
ተሰኙ::

26"ነገር ግን እንቢተኞች ሆኑ፤ ዐመፁብ
ህም፤ ሕግህንም አሽቀንጥረው ጣሉ፤ ወደ አንተ
እንዲመለሱ ሲያስጠነቅቋቸው የነበሩት ነቢ
ያትህን ገደሉ፤ አስጸያፊ የስድብ ቃልም
ተናገሩ:: 27ስለዚህ ላስጨነቋቸው ጠላቶቻ
ቸው አሳልፈህ ሰጠሃቸው:: በተጨነቁ ጊዜ
ግን ወደ አንተ ጮኹ፤ አንተም ከሰማይ ሰማ
ሃቸው፤ ከርኅራኄህም ብዛት የተነሣ ከጠ
ላቶቻቸው እጅ የሚያድኗቸውን ታዳጊዎች
ሰጠሃቸው::

28"ነገር ግን ዕረፍት ባገኙ ጊዜ፣ በፊትህ
ክፉውን ነገር እንደ ገና ፈጸሙ፤ ከዚያም
ይገዟቸው ዘንድ በጠላቶቻቸው እጅ ጣልሃ
ቸው፤ እንደ ገና ወደ አንተ በጮኹ ጊዜ፣
ከሰማይ ሰማህ፤ በርኅራኄህም በየጊዜው
ታደግሃቸው::

29"ወደ ሕግህ እንዲመለሱ አስጠነቀቅሃ
ቸው፤ እነርሱ ግን እብሪተኞች ሆኑ:: ትእ
ዛዞችህንም አልፈጸሙም፤ አንድ ሰው ቢፈ
ጽማቸው በሕይወት የሚኖርባቸውን ሥርዐ
ቶችህን ተላለፉ:: እምቢተኞች ሆነው ጀር
ባቸውን አዞሩብህ፤ ዐንገታቸውን አደነደኑ፤
መስማትም አልፈለጉም:: 30ብዙ ዘመን ታገ
ሥሃቸው፤ በነቢያትህ አማካይነት በመንፈ
ስህ አስጠነቀቅሃቸው:: ነገር ግን አላደመጡ
ህም፤ ከዚህም የተነሣ ጎረቤቶቻቸው ለሆኑ
አሕዛብ አሳልፈህ ሰጠሃቸው:: 31አንተ ግን
ቸርና መሓሪ አምላክ ነህና ከምሕረትህ
ብዛት የተነሣ፣ ፈጽመህ አላጠፋሃቸውም፤
አልተውሃቸውምም::

32"አሁንም አምላካችን ሆይ፤ ቃል ኪዳንህ
ንና ዘላለማዊ ፍቅርህን የምትጠብቅ ታላቅ፣
ኀያልና የተፈራህ አምላክ ሆይ፤ ከአሦር
ነገሥታት ዘመን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ
በእኛ፣ በነገሥታታችንና በመሪዎቻችን፣

9፥26 ኢሱ7፥25፤ 1ነገ14፥9፤ መሳ2፥12-13፤ ኤር2፥30፤26፥8፤ 44፥10፤ማቴ21፥35-36፤ 23፥29-36ሐሥ7፥52
9፥27 ዘኍ25፥17፤ መሳ2፥14፤3፥9፤ መዝ51፥1፤103፥8፤ 106፥45፤ 119፥156፤
9፥29 ቀኍ16-17፤ ዘዳ30፥16፤ መሳ6፥8፤1ሳሙ8፥3፤ መዝ5፥5፤ኢሳ2፥11፤ ኤር19፥15፤43፥2፤ ዘዳ7፥11-12
9፥28 ዘፀ32፥22፤ መሳ2፥17፤ 2ኛሳሙ24፥14፤ መዝ22፥4፤106፥43፤ 136፥24
9፥30 2ነገ17፥13-18፤ 2ዜና36፥16፤ ኤር16፥11፤ዘካ7፥12
9፥31 ዘዳ4፥31፤ ኢሳ48፥9፤65፥9
9፥32 ዘፀ18፥8፤ ዘዳ7፥9፡21፤1ነገ8፥23፤ ኢዮ9፥19፤ መዝ24፥8፤89፥8፤ 93፥4፤ዳን9፥4
9፥33 ዘፍ18፥25፤ ኤር44፥3ዳን9፥7-8፡14
9፥34 2ነገ23፥11፤ ኤር44፥17
9፥35 ዘዳ28፥45-48፤ ኢሳ63፥7
9፥36 ዕዝ9፥9
9፥37 ዘዳ28፥33፤ ሰቆ5፥5
9፥38 2ዜና23፥16፤ ኢሳ44፥5
10፥1 ዕዝ2፥2
10፥2 1ዜና9፥12
10፥5 1ዜና24፥8
10፥8 ነህ12፥1
10፥9 ነህ12፥1

በካህናታችንና በነቢያታችን፣ በአባቶቻ
ችንና በመላው ሕዝብህ ላይ የደረሰው ይህ
ሁሉ መከራ በፊትህ እንደ ቀላል ነገር
አይታይ:: 33በደረሰብን ሁሉ አንተ ጻድቅ
ነህ፤ እኛ በደለኞች ነን፤ አንተ ግን ትክክ
ለኛውን አደረግህ:: 34ነገሥታታችን፣ መሪ
ዎቻችን፣ ካህናታችንና አባቶቻችን ሕግ
ህን አልጠበቁም፤ ትእዛዞችህን ወይም የሰጠ
ሃቸውን ማስጠንቀቂያዎች አልሰሙም:: 35በገዛ
መንግሥታቸው፣ በሰጠሃቸው ታላቅ በጎነት
ህና በፊታቸውም ባዘጋጀህላቸው ሰፊና ለም
ምድር እንኳ፣ አንተን አላገለገሉም፤ ከክፉ
መንገዳቸውም አልተመለሱም::

36"እነሆ፤ ዛሬም ባሮች ነን፤ አባቶቻችን
ፍሬዋንና በረከቷን እንዲበሉ በሰጠሃቸው
ምድር ባሮች ነን:: 37ከኀጢአታችን የተነሣ
የተትረፈረፈው መከር ሲሳይ የሆነው በላ
ያችን ላስቀመጥሃቸው ነገሥታት ነው፤ እነር
ሱም ደስ እንዳሰኛቸው በሰውነታችንና በቀ
ንድ ከብቶቻችን ላይ ያዛሉ:: እኛም በታ
ላቅ ጭንቀት ውስጥ እንገኛለን::

## የሕዝቡ መስማማት

38"ከዚህ ሁሉ የተነሣም ጽሑፍ ላይ በማ
ስፈር ግዴታ የምንገባበትን የውል ስምምነት
እናደርጋለን፤ መሪዎቻችን፣ ሌዋውያኖቻች
ንና ካህናቶቻችንም ማኅተሞቻቸውን ያኖሩበ
ታል::"

10 ያተሙትም እነዚህ ናቸው፤
የሐካልያ ልጅ አገረ ገዡ ነህምያ፣
ሴዴቅያስ፣ 2ሠራያ፣ ዓዛርያስ፣ ኤርምያስ፣
3 ፋስኮር፣ አማርያ፣ መልክያ፣
4ሐጡስ፣ ሰበንያ፣ መሉክ፣
5 ካሪም፣ ሜሪሞት፣ አብድዩ፣
6 ዳንኤል፣ ጌንቶን፣ ባሮክ፣
7 ሜሱላም፣ አብያ፣ ሚያሚን፣
8መዓዝያ፣ ቢልጋይ፣ ሸማያ፤ እነዚህ
ካህናት ነበሩ::
9ሌዋውያኑ:-
የአዛንያ ልጅ ኢያሱ፣ ከኤንሐዳድ
ወንዶች ልጆች ቢንዊ፣ ቀድምኤል፣

---

ውሃ የሚያጠራቅምበት ሰው ሠራሽ ጕድጓድ ነበረው (2ነገ 18፥31፤ ምሳ 5፥15):: ውሃ ሳያባክኑ ቋጥረው መያዝ የሚችሉትን ጕድጓዶች የማዘጋጀት ጥበብ በ1200 ዓ.ቅ.ክ. ተጀምሮ ነበር፤ ይህም በመካከለኛው የይሁድ ኰረብታማ አካባቢ ብዙ ሰው እንዲሰፍር ምክንያት ሆኖአል:: *የወይን ተክላቸውን፣ የወይራ ዛፎቻቸውንና ... የፍሬ ዛፎች፤* ከዘዳ 8፥8 ጋር ያነጻጽሩ:: የግብፁ የሲኑሄ ታሪክ (2000 ዓ.ቅ.ክ ገደማ) የከነዓንን ምድር እንዲህ ሲል ይገልጻል፤ "የበለስ ዛፍና የወይን ተክል ይገኝባታል፤ በምድሪቱ ያለው የወይን ጠጅ ብዛት በአገሪቱ ካለው ውሃ ይበልጣል፤ ማርና የወይራ ዘይት የተትረፈረፈባት፣ ፍራፍሬም በየዛፉ ላይ ተንዠርግጎ የሚገኝባት ነበረች::" *ወፈሩም፤* የዕብራይስጡ ቃል በሌላ ቦታ የገባው የአካልን መዳበርና የመንፈስን መደንዘዝ ለመግለጽ ነው::

*9፥26-28፤* የመሳ 2፥6-3፥6 ማብ ይመ::

9፥27 *ታዳጊዎች፤* የእስራኤልን በደል አይቶ ቅጣትን የሚልክባቸው፣ ንስሓቸውንም ተመልክቶ ታዳጊ የሚሆኑ መሪዎችን የሚያስነሣላቸው ራሱ እግዚአብሔር ነበር (በመጽሐፈ መሳፍንት መግቢያ ላይ "ርእስ" የሚለውን ይመ)

9፥29 *ቢፈጽማቸው በሕይወት የሚኖርባቸውን፤* የዘሌ 18፥5 ማብ ይመ:: *እምቢተኞች ሆነው ጀርባቸውን አዞሩብህ፤* ዘካ 7፥11 ይመ፤በቍ 16፤3፥5፤ሆሴ 4፥16 ላይ ያለውን ተመሳሳይ አገላለጽ ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ::

9፥32 *ከአሦር ነገሥታት፤* እነርሱም ጹል ተብሉ የሚጠራው ቲግላሳዊው ቴልጌልቴልፌልሶር (1ዜና 5፥26)፣ ስልምናሶር አምስተኛው (2ነገ 18፥9)፣ ዳግማዊው ሳርጎን (ኢሳ 20፥1)፣ ሰናክሬም (2ነገ 18፥13)፣ አስራዶንና (ዕዝ 4፥2) አስናፍር (ዕዝ 4፥10) ናቸው::

9፥37 *በሰውነታችንና ... ላይ ያዛሉ፤* 1ሳሙ 8፥11-13 ይመ:: የፋርስ ገዦች የሚስተዳድሩትን ሕዝብ እየመለመሉ ወደ ውትድርና አገልግሎት ያስገቡት ነበር:: ንጉሥ አርጤክስስ በ480 ዓ.ቅ.ክ ላይ ግሪክን በወረረ ጊዜ፣ ጥቂት አይሁድ አብረውት ሳይዘምቱ አልቀሩም::

*10፥1-27፤* የሰማንያ አራት ሰዎችን ስም ዝርዝር የያዘ፣ ሕጋዊ ማኅተም ያለበት ሕጋዊ የስም ዝርዝር ነው::

*10፥2-8፤* ከእነዚህም ስሞች ግማሽ ያህሉ በ12፥1-7ላይ በድጋሚ ተጠቅሰአል::

*10፥9-13፤* ከእነዚህም አብዛኛው በሌዋውያኑ የስም ዝርዝር ውስጥ (8፥7፤9፥4-5) ተጠቅሶ ይገኛል::

*10፥14-27፤* በዚህ ዝርዝር ከሚገኙት ግማሽ ያህል ስሞች

10ወንድሞቻቸው:-
ሰብንያ፣ ሆዲያ፣ ቆሊጣስ፣ ፌልያ፣
ሐናን፣
11ሚካ፣ ረአብ፣ ሐሸብያ፣
12ዘኩር፣ ሰራብያ፣ ሰበንያ፣
13ሆዲያ፣ ባኒ፣ ብኒኑ።
14የሕዝብ መሪዎች:-
ፋሮስ፣ ፈሐት፣ ሞዓብ፣ ኤላም፣
ዛቱዕ፣ ባኒ፣
15ቡኒ፣ ዓዝጋድ፣ ቤባይ፣
16አዶንያስ፣ በጉዋይ፣ ዓዲን፣
17አጤር፣ሕዝቅያስ፣ዓዙር፣
18ሆዲያ፣ ሐሱም፣ ቤሳይ፣
19ሐሪፍ፣ ዓናቶት፣ ኖባይ፣
20መግጲዓስ፣ ሜሱላም፣ ኤዚር፣
21ሜሴዜቤል፣ ሳዶቅ፣ ያዱአ፣
22ፈላጥያ፣ ሐናን፣ ዓናያ፣
23ሆሴዕ፣ ሐናንያ፣አሱብ፣
24አሎኤስ፣ ፈልሃ፣ ሰቤቅ፣
25ሬሁም፣ ሐሰብና፣ መዕሤያ፣
26አኪያ፣ ሐናን፣ ዓናን፣
27መሉክ፣ ካሪምና በዓና።
28የቀሩት ሕዝብ:- ማለት ካህናቱ፣ ሌዋ
ውያኑ፣ በር ጠባቂዎቹ፣ መዘምራኑ፣ የቤተ
መቅደሱ አገልጋዮች፣ ስለ እግዚአብሔር ሕግ
ብለው ራሳቸውን ከጎረቤት አሕዛብ የለዩ
ሁሉ፣ ሚስቶቻቸው፣ ወንዶችና ሴቶች ልጆ
ቻቸው፣ የሚያውቁና የሚያስተውሉ ሁሉ፣
ቃለ መሐላ ፈጽሙ፤ 29እነርሱም ከወንድሞ
ቻቸውና ከመኳንንታቸው ጋር በመሆን
በእግዚአብሔር ባሪያ በሙሴ አማካይነት የተ
ሰጠውን የእግዚአብሔርን ሕግ የጌታችንን የእግዚ
አብሔርን ትእዛዞች፣ ደንቦችና ሥርዐቶች
ሁሉ ለመታዘዝ በዚህ ርግማንና መሐላ
ቃል ገቡ። 30"ሴት ልጆቻችንን በዙሪያችን
ላሉት አሕዛብ አንሰጥም፤ የእነርሱን ሴቶች
ልጆች ለወንዶች ልጆቻችን አንወስድም።
31"አሕዛብ ጎረቤቶቻችን በሰንበት ቀን
ለመሸጥ ሸቀጣ ሸቀጥ ወይም እህል ቢያ
መጡ፣ በሰንበት ወይም በማናቸውም በተ
ቀደሰ ቀን ከእነርሱ አንገዛም። በየሰባት ዓመ
ቱም ምድሪቱን እናሳርፋለን፤ ዕዳንም ሁሉ
እንሠርዛለን።
32"በየዓመቱ ለእግዚአብሔር ቤት አገልግ
ሎት የሚሆን የሰቅል[a] አንድ ሦስተኛ ለመ
ስጠት ቃል እንገባለን፤ 33ይህም በጠረጴዛው
ላይ ለሚቀርበው ኅብስት፣ ዘወትር ለሚ
ቀርበው የእህል ቍርባን፣ የሚቃጠል መሥ
ዋዕት፣ በሰንበት፣ በወር መባቻና በተደነ
ገጉ በዓላት ለሚቀርበው መሥዋዕት፣ ለተ
ቀደሱ መባዎች፣ ለእስራኤል ስርየት ለሚ
ቀርበው የኀጢአት መሥዋዕትና ለአምላካችን
ቤት ሥራ ሁሉ የሚውል ነው።
34"እኛ፣ ማለት ካህናቱ፣ ሌዋውያኑና ሕዝቡ
በየዓመቱ በተወሰነው ጊዜ በሕጉ እንደተጻ
ፈው፣ በአምላካችን በእግዚአብሔር መሠዊያ
ላይ የሚነደውን ዕንጨት የእያንዳንዳችን
ቤተ ሰብ መቼ ወደ አምላካችን ቤት ማምጣት
እንዳለበት ለመወሰን ዕጣ ተጣጣልን።
35"የሰብላችንንና የእያንዳንዱን ዛፍ ፍሬ
በኵራትም ወደ እግዚአብሔር ቤት ለማምጣት
ቃል እንገባለን።
36"እንዲሁም በሕጉ እንደ ተጻፈው የወ
ንድ ልጆቻችንንና፣ የቀንድ ከብቶቻችንን፣
የመንጋዎቻችንን፣ የበግና የፍየል መንጋ
ዎቻችንን በኵራት ወደ አምላካችን ቤት፣
ወደ ሚያገለግሉትም ካህናት እናመጣለን።
37"ከዚህም በላይ የቡሆአችንን፣ የእህል
ቍርባናችንን፣ የዛፎቻችንን ፍሬ ሁሉ፣ አዲ

10፥16 ዕዝ8፥6
10፥20 1ዜና24፥15
10፥23 ነህ7፥2
10፥28 2ዜና 6፥26፤ ነህ9፥2፤ መዝ135፥1
10፥29 ዘኍ5፥21፤ መዝ119፥106
10፥30 ዘፀ34፥16፤ ነህ13፥23
10፥31 ዘፀ23፥11፤ ዘሌ25፥1-7፤ዘዳ15፥1፤ ነህ13፥16፡18፤ ኤር17፥27፤ ሕዝ23፥38፤አሞ8፥5
10፥33 ዘሌ 24፥6፤ ዘኍ10፥10፤2ዜና24፥5፤ መዝ81፥3፤ኢሳ1፥14
10፥34 ዘሌ 16፥8፤ ነህ13፥31
10፥35 ዘፀ22፥29፤ ዘኍ18፥12፤ዘዳ26፥1-11
10፥36 ዘፀ13፥2፤ ዘኍ18፥14-16፤ ነህ13፥31
10፥37 ዘሌ27፥30፤ ዘኍ18፥12፡21፤ ዘዳ14፥22-29፤ ሕዝ44፥30

[a]32 4 ግራም ያህል ነው።

በ7፥6-63 እና በዕዝ 2፥1-61 ባሉት ዝርዝሮች ውስጥ ይገኛሉ።
10፥28፤ *ሌዋውያኑ፤* በአራት ዘሌዋውያን መጊቢያ ላይ "ርእስ" የሚለውን ይመ። *በር ጠባቂዎቹ፤* የዕዝ 2፥42 ማብ ይመ። *ሚስቶቻቸው፣ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸው፤* የ8፥2 ማብ ይመ።
*10፥31-33፤* በ13፥15-22 ላይ የተፈጸመው ስሕተት እንዲ ታረም ነህምያ ያወጣው ደንብ ሊሆን ይችላል።
10፥31 *በሰንበት ቀን ለመሸጥ፤* ምንም እንኳ ዘፀ 20፥8-11፤ ዘዳ 5፥12-15 በሰንበት ቀን መሸጥ መለወጥን በግልጽ ባይ ከለክሉም፣ አሞ 8፥5፤ ኤር 17፥19-27 ላይ እና ማብ ይመ። *በየሰባት ዓመቱም ምድሪቱን እናሳርፋለን፤ ዕዳንም ሁሉ እንሠርዛለን፤* የዘሌ 25፥4 ማብ ይመ። ሮማውያን በሰንበት ቀን አለመሥራትንና በሰባተኛውም ዓመት ማረፍን እንደ ስንፍና ይቈጥሩት ነበር። ታሲተስ የተባለ ሰው የአይሁድ ሕዝብ "ሌላው አልበቃ ብሎ ሰባተኛው ዓመትም የዕረፍት ዘመን እንዲሆን መወሰናቸው ያለ ሥራ ለመቀመጥ ያላቸውን የታካችነት መንፈስ" ያሳያል ሲል ዘግቦአል።
10፥32 *የሰቅል አንድ ሦስተኛ፤* በዘፀ 30፥13-14 ላይ፣ ዕድሜው ሃያ ዓመትና ከዚያም በላይ የሆነ ወንድ ሁሉ ለመቤዠቱ ምል ክት ይሆነው ዘንድ፣ "ግማሽ ሰቅል" "ለእግዚአብሔር መባ አድ ርጎ" ማቅረብ እንዳለበት ተገልጾአል። በኋላም ኢዮአስ በየዓመቱ የሚደረገውን መዋጮ ለቤተ መቅደሱ ዕድሳት ሥራ አውሎታል (2ዜና 24፥4-14)። በአዲስ ኪዳንም ዘመን ከአገራቸው ውጭ የሚኖሩት አይሁድ በኢየሩሳሌም ለነበረው ቤተ መቅደስ (ማቴ 17) ግማሽ ሰቅል መባ ይልኩ ነበር (ግማሽ ሰቅልና ሁለት ድራክማ ተመጣጣኝ እንደ ሆኑ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን ያረጋግጣል)። ስለዚህ በነህምያ ዘመን ወደ አንድ ሦስተኛ ሰቅል ዝቅ የተደረገበት ምክንያት ከነበራቸው የኑሮ ደረጃ የተነሣ ሳይሆን አይቀርም።
10፥33 *ኅብስት፤* የዘሌ 24፥8 ማብ ይመ።
10፥34 *ዕጣ ተጣጣልን፤* የ11፥1፤ ዮና 1፥7 ማብ ይመ። *ዕን ጨት ... ማምጣት፤* በአምስቱ የሙሴ መጻሕፍት ግገዶ ስለ ማቅረብ የሚናገር ልዩ ክፍል ባይኖርም፣ በቤተ መቅደሱ መሠ ዊያ ላይ የማይጠፋ እሳት ዘወትር መንደድ ስላለበት (ዘሌ 6፥12-13)፣ የዕንጨት አቅርቦቱ መቋረጥ አልነበረበትም። "አብ" በተባለው በአምስተኛው ወር ዐሥራ አራተኛ ቀን፣ "የዕንጨት አቅርቦት በዓል" እንደ ነበረ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን ይጠቅሳል። እንዲሁም ሚሽናሕ የተባለው የአምስቱ የሙሴ መጻሕፍት ትርጒም የተወሰኑ ቤተሰቦች ዘጠኝ ጊዜ እንጨት እንዳቀረቡ በዝርዝር አስቀምጦታል፤ ከዚህም በቀር ከወይን ተክልና ከወይራ ዛፍ በስተቀር፣ ማንኛውንም ዐይነት እንጨት ማቅረብ እንደ ሚቻል ለይቶ ያመለክታል። በቍምራን የተገኘው የቤተ መቅደስ ጥቅልል ብራና፣ አዲሱን የዘይት በዓል ካከበሩ በኋላ፣ የዕንጨት አቅርቦት በዓል ተከብሮ እንደ ነበረ ያስረዳል።
10፥35 *በኵራትም፤* ካህናቱንና ሌዋውያኑን ለመደጎም በኵራትን ወደ መቅደሱ ያመጡ ይሰጡ ነበር (ዘፀ 23፥19፤ ዘኍ 18፥13፤ ዘዳ 26፥1-11፤ ሕዝ 44፥30)።
10፥36 *በኵራት፤* የዘፀ 13፥13 ማብ ይመ።
10፥37 *ዕቃ ቤቶች፤* በቤተ መቅደሱ ግቢ ውስጥ የነበሩ ክፍሎች ለብር፣ ለወርቅና እንዲሁም ለአንዳንድ ንዋየ ቅድሳት ማስቀመጫ ያገለግሉ ነበር (ከቍ 38-39፤ 12፥44፤ 13፥4-5፡9፤ ከዕዝ 8፥28-30 ጋር ያነጻጽሩ)። *አዲሱን የወይን ጠጃችንን፤* የዘዳ 7፥13 ማብ ይመ። ይህ ሐረግ በዕብራይስጡ አዲሱን የወይን ፍሬ ጭማቂ ብቻ ሳይሆን (ኢሳ 65፥8፤ሚክ6፥15)፣ የሚያስከረው ንም የወይን ጠጅ ሊያመለክት ይችላል (ሆሴ 4፥11)። *ዐሥራት፤*

ሱን የወይን ጠጃችንንና የዘይታችንን በኵ
ራት ወደ ካህናቱ፣ ወደ ስምባካችን ቤት
ዕቃ ቤቶች እናመጣለን። እኛ በምንሠራባ
ቸው ከተሞች ሁሉ ያለውን ዐሥራት የሚሰበ
ስቡት ሌዋውያን ስለሆኑ፣ የሰብላችንን ዐሥ
ራት ወደ ሌዋውያኑ እናመጣለን። [38]ዐሥራ
ቱን በሚቀበሉበት ጊዜም ከአሮን ዘር የተወ
ለደው ካህን ከሌዋውያኑ ጋር አብሮ ይገ
ኛል፤ ሌዋውያኑም የዐሥራቱን አንድ ዐሥ
ረኛ ወደ ላይ እስካለው፣ እስከ ስምባካችን
ቤት ዕቃ ቤቶች ማከማቻ ድረስ ያመጡ
ታል። [39]የእስራኤል ሕዝብና ሌዋውያኑ
ጭምር፣ ከእህሉ፣ ከአዲሱ ወይን ጠጅና
ከዘይቱ ያዋጡትን፣ የመቅደሱ ዕቃዎች ወደ
ሚቀመጡበት፣ አገልጋይ ካህናት፣ በር ጠባ
ቂዎቹና መዘምራኑ ወደ ሚያርፉበት ዕቃ
ቤቶች ያምጡ።

"እኛም የስምባካችንን ቤት ቸል አንልም"

## አዲሶቹ የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች

11፥3-19 ተጓ ምብ 1ዜና 9፥1-17

**11** በዚህ ጊዜ የሕዝቡ መሪዎች መኖሪያ
ቸውን በኢየሩሳሌም አደረጉ፤ ከቀ
ረው ሕዝብ ከዐሥር አንዱ እጅ በቅድስቲቱ
ከተማ በኢየሩሳሌም፣ የቀሩት ዘጠኙ እጅ
ደግሞ በየራሳቸው ከተሞች እንዲኖሩ ዕጣ
ተጣጣሉ። [2]ሕዝቡም በኢየሩሳሌም ለመ
ኖር በራሳቸው ፈቃድ የተነሣሡትን ሰዎች
ሁሉ አመሰገኑ።

[3]እንግዲህ በኢየሩሳሌም የተቀመጡት የአ
ውራጃዪቱ መሪዎች እነዚህ ናቸው፤ በዚህ
ጊዜም በይሁዳ ከተሞች የሚኖሩ የተወሰኑ
እስራኤላውያን፣ ካህናት፣ ሌዋውያን፣ የቤተ
መቅደሱ አገልጋዮችና የሰሎሞን አገልጋዮች
ዘሮች እያንዳንዳቸው በተለያዩ ከተሞች
ባሉት በየራሳቸው ንብረት ላይ ተቀመጡ፤
[4]ከይሁዳና ከብንያም ወገን የሆኑት የተቀሩት
ሰዎች ደግሞ በኢየሩሳሌም ተቀመጡ፤
ከይሁዳ ዘሮች፦

ከፋሬስ ዘር የመላልኤል ልጅ፣ የሰፋጥ
ያስ ልጅ፣ የአማርያ ልጅ፣ የዘካርያስ
ልጅ፣ የዖዝያ ልጅ አታያ፤ [5]ከሴሎ ዘር
የዘካርያስ ልጅ፣ የዮያሪብ ልጅ፣ የዓ
ዳያ ልጅ፣ የዖዛያ ልጅ፣ የኮልሖዜ
ልጅ፣ የባሮክ ልጅ መዕሤያ። [6]በኢየሩ
ሳሌም የተቀመጡት የፋሬስ ዘሮች በጠ
ቅላላ 468 ብርቱ ሰዎች ናቸው።

[7]ከብንያም ዘሮች፦

የየሻያ ልጅ፣ የኢቲኤል ልጅ፣ የመዕ
ሤያ ልጅ፣ የቆላያ ልጅ፣ የፈዳያ
ልጅ፣ የዮእድ ልጅ፣ የሜሱላም ልጅ
ሰሉ፤ [8]ተከታዮቹም ጌቤና ሳላይ 928
ወንዶች፤ [9]የእነዚህም አለቃ የዝክሪ
ልጅ ኢዩኤል ሲሆን፣ የሐስኑአ ልጅ
ይሁዳ የከተማዪቱ "ሁለተኛ አውራጃ"
የበላይ ነበር።

[10]ከካህናቱ፦

የዮያሪብ ልጅ ዮዳኤ፤ ያኪን፤ [11]የእግዚ
አብሔር ቤት አለቃ የአኪጦብ ልጅ፣
የመራዮት ልጅ፣ የሳዶቅ ልጅ፣ የሜ
ሱላም ልጅ፣ የኪልቅያስ ልጅ ሠራያ፤
[12]የቤተ መቅደሱን ሥራ ያከናወኑት ወን
ድሞቻቸው፣ 822 ሰዎች፤ የመልክያ
ልጅ፣ የፋስኮር ልጅ፣ የዘካርያስ ልጅ፣
የአማሲ ልጅ፣ የፈላልያ ልጅ፣ የይሮሐም
ልጅ ዓዳያ፤ [13]ወንድሞቹ የሆኑት የየ
ቤተ ሰቡ አለቆች 242 ወንዶች፤ የኢሜር
ልጅ የምሺሌሞት ልጅ፣ የአሕዛይ ልጅ፣
የኤዝርኤል ልጅ አማስያ፤ [14]እንዲሁም
ብርቱ የሆኑት ወንድሞቹ[ከ] 128 ሰዎች፤
የእነርሱም ዋና አለቃ የሐግዶሊም ልጅ
ዘብድኤል ነበር።

[15]ከሌዋውያኑ፦

የቡኒ ልጅ፣ የአሳብያ ልጅ፣ የዓዝሪቃም
ልጅ፣ የአሱብ ልጅ ሻማያ፤ [16]እንዲሁም

10፥38 ዘኍ18፥26
10፥39
ነህ13፥11፡12
11፥1 ነህ7፥4፡73፤
ኢሳ48፥2፤52፥1፤
64፥10፥ዘካ14፥20-21
11፥3 ዕዝ2፥1
11፥4 ዕዝ1፥5፤2፥70
11፥11 2ነገ25፥18፤
ዕዝ2፥2፤7፥2
11፥16 ዕዝ8፥33፤
10፥15

[ከ]14 አብዛኞቹ የሰብዓ ሊቃናት ቅጆች ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ ዕብ
ራይስጡ ግን፣ *ወንድሞቻቸው* ይላል።

የዘፍ 14፥20፤ 28፥22፤ የዘሌ 27፥30፤ የአሞ 4፥4 ማብ ይመ።
*ሌዋውያኑ*፤ ዐሥራት የሚሰበስበው ሌዋውያንን ለመደጉም ነው
(13፥12-13፤ ዘኍ 18፥21-32)።

*10፥39*፤13፥11 ይመ። *እኛም ... ቸል አንልም*፤ ሕዝቡ
የቤተ መቅደሱን ሥራ ቸል በማለታቸው ሐጌ (ሐጌ 1፥4-9)
ወቅሶአቸዋል።

11፥1 *ዕጣ ተጣጣሉ*፤ 10፥34 ይመ። ዕጣ የሚጣጣሉባቸው
ነገሮች ብዙውን ጊዜ ጠጠሮች ወይም ስንጥሮች ነበሩ። አንዳንድ
ጊዜም ወስፈንጥሮችን ይጠቀሙ ነበር (ሕዝ 12፥2) *ከዐሥር
አንዱ እጅ ... በኢየሩሳሌም... እንዲኖሩ*፤ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን
"ነህምያ ግን የከተማይቱ ነዋሪዎች ብዛት አነስተኛ መሆኑን
ተመልክቶ፣ ካህናቱና ሌዋውያኑ ከገጠር ወደ ከተማ እንዲመጡና
በዚያ እንዲኖሩ ግድ አላቸው፤ የሚኖሩበትን ቤት በራሱ ወጪ
አሠርቶ ነበርና" ("አንቲኩቲስ 11.5.8.") ይላል። ሕዝብን ከአንድ
ስፍራ ወደ ሌላ ስፍራ ማንቀሳቀስ የግሪክ ሥልጣኔ (ሄሌናዊነት)
በደረሰባቸው ከተሞች ሁሉ የተለመደ ነበር። ይህም የገጠሩን ሕዝብ
በኀይል አፈናቅሎ በከተሞች እንዲኖር ማድረግን የሚያካትት
ነበር። ሄሮድስ አንቲጳስ በ18 ዓ.ም. አካባቢ በገሊላ ባሕር ዳርቻ
የነበረችው የጥብርያዶስ ከተማ ሕዝብ እንዲሰፍርባት የተደረገው
በዚሁ አሠራር መሠረት ነበር። *በቅድስቲቱ ከተማ*፤ ኢሳ 48፥2
እና ማብ፤ ዳን 9፥24፤ ማቴ 4፥5፤ 27፥53፤ ራእ 11፥2 ይመ፤
ከኢል 3፥17 ጋር ያነጻጽሩ።

*11፥2*፤ በዕጣ ከተመለመሉት በተጨማሪ (ቍ 1)፣ አንዳን
ዶቹ ኀላፊነት ተሰምቶአቸው በፈቃደኝነት ሄደዋል፤ ሆኖም
አብዛኞቹ ከመኖሪያ ከተማቸው መለየት አለመፈለጋቸው ግልጽ ነው።

*11፥3-19*፤ በ1ዜና 9፥2-21 ላይ ከባቢሉን ምርኮ የተመለ
ሱት የመጀመሪያዎቹ የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች የስም ዝርዝር ከሚ
ገኝበት የቈጠራ መዝገብ ጋር ተጓዳኝ ነው። ሁለቱ የስም ዝር
ዝሮች ሲነጻጸሩ ግማሽ ያህሉ ስሞች አንድ ዐይነት ናቸው።

11፥8 *928*፤ ኢየሩሳሌምን ለመጠበቅና በዚያም እንዲኖሩ
የብንያም ሰዎች ያቀረቡት የሰው ብዛት የይሁዳ ሰዎች ካቀረቡት
ጋር ሲነጻጸር በሁለት እጅ ይበልጣል (ቍ 6)።

11፥9 *ሁለተኛ አውራጃ*፤ 2ዜና 34፥22 ይመ (በሶፎ 1፥10
ላይ ይህን ለመግለጽ የገባው የዕብራይስጡ ሐረግ "የከተማው
ሁለተኛ አደባባይ" ተብሎ ተተርጕሞአል)። እንደ ገበያው ስፍራ
ሁሉ (ሶፎ 1፥11)፣ 'ሁለተኛው አውራጃ' የተባለውም ስፍራ፣ ቤተ
መቅደሱ ካለበት ቦታ በስተ ምዕራብ በኩል ወጣ ብሎ በጢ
ሮጳዮን ሸለቆ አካባቢ የነበረ ሳይሆን አይቀርም። ሕዝቅያስ
በ700 ዓ.ቅ.ክ ላይ ሰፊው ቅጥር የተባለውን ከመሥራቱ በፊት፣
ከተማይቱ በስምንተኛው ምዕተ ዓመት ቅ.ል.ክ ላይ በዚህ
አቅጣጫ ተስፋፍታ እንደ ነበር የአካባቢው የሥነ ቅርስ ቍፋሮ
ግኝት ያመለክታል (የ3፥8 ማብ ይመ)።

11፥16 *የውጪ ሥራ*፤ ከቤተ መቅደሱ ውጭ የተከናወነ
ተግባር ቢሆንም (ከ1ዜና 26፥29 ጋር ያነጻጽሩ)፣ ከቤተ መቅደሱ

የእግዚአብሔር ቤት የውጪ ሥራ ኀላፊዎች
የነበሩት፣ ከሌዋውያን አለቆች ሁለቱ ሳባ
ታይና ዮዛባት። 17በምስጋናና በጸሎት ጊዜ
ይመራ የነበረው የዋናው አለቃ የአሳፍ ልጅ፣
የዙብዲ ልጅ፣ የሚካ ልጅ መታንያ፣
ከወንድሞቹ ሁለተኛ የሆነው በቅበቃር፣
የኤዶታም ልጅ፣ የጋላል ልጅ፣ የሳሙስ
ልጅ አብድያ። 18በቅድስቲቱ ከተማ ውስጥ
የነበሩት የሌዋውያኑ ቍጥር 284 ነበረ።
19በር ጠባቂዎች፦

ዓቁብ፣ ጤልሞንና በሮቹን የሚጠብቁ
ወንድሞቻቸው፣ 172 ሰዎች።

20የቀሩት እስራኤላውያንም ከካህናቱና
ከሌዋውያኑ ጋር በይሁዳ ከተሞች ሁሉ በየ
ርስታቸው ተቀመጡ።

21የቤተ መቅደሱ አገልጋዮች በዖፌል
ኰረብታ ላይ ተቀመጡ፤ ሲሐና ጊሽጳ በእ
ነርሱ ላይ ያዙ ነበር።

22በኢየሩሳሌም የሌዋውያኑ ዋና አለቃ የሚካ
ልጅ፣ የመታንያ ልጅ፣ የሐሻብያ ልጅ፣
የባኒ ልጅ ኦዚ ነበረ፤ ኦዚ በእግዚአብሔር
ቤት አገልግሎት ለሚዘመረው መዝሙር
ኀላፊ ከነበሩት ከአሳፍ ዘሮች አንዱ ነበረ።

11፥17 1ዜና9፥15፤ 25፥1፤2ዜና5፥12፤ ነህ12፥8
11፥18 ራእ21፥2
11፥21 ዕዝ2፥43፤ ነህ3፥26
11፥22 1ዜና9፥15
11፥23 ዜና15፥16፤ ነህ7፥44
11፥24 ዘፍ38፥30
11፥25 ዘፍ35፥27፤ ዘኍ21፥30
11፥26 ኢሱ15፥26፡27
11፥27 ዘፍ21፥14፤ ኢሱ15፥28
11፥28 1ሳሙ27፥6
11፥29 ኢሱ10፥3፤ 15፥33፡35
11፥30 ኢሱ10፥3፡ 10፤15፥28፡34፡35፡39
11፥31 ኢሱ 12፥9፤ 21፥17፤1ሳሙ13፥2፤ ኢሳ10፥29
11፥32 ኢሱ21፥18፤ 1ሳሙ21፥1ኢሳ10፥30፤ ኤር1፥1
11፥33 ኢሱ 11፥1፤ 18፥25፤2ሳሙ4፥3
11፥34 1ሳሙ 13፥18
11፥35 1ዜና8፥12

23መዘምራኑ የየዕለቱን ተግባራቸውን በሚ
ቈጣጠረው በንጉሡ ትእዛዝ ሥር ነበሩ።

24የይሁዳ ልጅ የዛራ ዘር የሆነው የሜሴዜ
ቤል ልጅ ፈታያ ሕዝቡን በሚመለከት
ጕዳይ ሁሉ የንጉሡ ተወካይ ነበር።

25ከይሁዳ ሕዝብ ጥቂቱ በመንደሮችና
በእርሻ ቦታዎች፣ በቂርያት አርባቅና በዙሪ
ያዋ ባሉ መኖሪያዎቿ፣ በዲቦንና በመኖሪያ
ዎቿ፣ በይቀብጽኤልና በመንደሮቿ ተቀመጡ፤
26በኢያሱ፣ በሞላዳ፣ በቤትጳሌጥ፣ 27በሐ
ጸርሹዓል፣ በቤርሳቤህና በመኖሪያዎቿ፣
28በጺቅላግ፣ በምኮናና በመኖሪያዎቿ፣ 29በዓ
ይንሪሞን፣ በጸርዓ፣ በየርሙት፣ 30በዛኖዋ፣
በዓዶላምና በመንደሮቻቸው፣ በለኪሶና በእር
ሻዎቿ፣ በዓዜቃና በመንደሮቿ። ስለዚህ ከቤ
ርሳቤህ ጀምሮ እስከ ሄኖም ሸለቆ ባለው
ስፍራ ሁሉ ተቀመጡ።

31ከጌባ የመጡት የብንያም ዘሮች በማክ
ማስ፣ በጋያ፣ በቤቴልና በመኖሪያዎቿ፣
32በዓናቶት፣ በኖብና በሐናንያ፣ 33በሐጸር፣
በራማና በጊቴም፣ 34በሐዲድ፣ በስቦይምና
በንበላት፣ 35በሎድና በኦኖ፣ ደግሞም
"የእጅ ጥበብ ባለሙያዎች ሸለቆ" በተባለው

*ሥራ ጋር የተያያዘ ነው።*

11፥17 *የአሳፍ፤* የዕዝ 2፥41 ማብ፤ እንዲሁም የመዝ 50፤73-83 ርእስ ይመ። *የኤዶታም፤* 1ዜና 16፥42፤25፥1፡3፤2ዜና 5፥12፤ የመዝ 39፤62፤77ርእስ ይመ።

11፥18 *284* የሌዋውያኑ ቍጥር ከካህናቱ ጋር ሲነጻጸር (1192፤ ቍ 12-13 ይመ) በጣም አንሶ መገኘቱ እጅግ የሚያስደንቅ ነው (የዕዝ 2፥4 ማብ ይመ)።

11፥20 *በየርስታቸው፤* በውርስ የሚተላለፉ ለምሳሌ እንደ መሬት፣ ቤትና ተንቀሳቃሽ ንብረት ያሉ ነገሮችን መውረስ የሚቻለው ድል በማድረግ ወይም በውርስ ነው (ዘፍ 31፥14፤ ዘኍ 18፥21፤27፥7፤ 34፥2፤ 36፥3፤ 1ነገ 21፥1-4)።

11፥21 *ዖፌል፤*የ3፥26 ማብ ይመ።

11፥23 *በሚቈጣጠረው በንጉሡ ትእዛዝ፤* ዳዊት የመዘምራኑንና የሌዋውያኑን አገልግሎት ይቈጣጠር ነበር (1ዜና 25)። የፋርሱ ንጉሥ ቀዳማዊ ዳርዮስ፣ "ለንጉሡ እንዲሁም ለወንድ ልጆቹ ደኅንነት እንዲጸልዩ" (ዕዝ 6፥10)፣ ለአይሁድ ሽማግሌዎች ከቤተ መንግሥቱ በየጊዜው ገንዘብ ይሰጣቸው ነበር። ቀዳማዊ አርጤክስስም ለሌዋውያኑ መዘምራን እንደዚሁ ሳያደርግላቸው አልቀረም።

*11፥25-30፤* በይሁዳ ምድር የነበሩትን ከተሞች ዝርዝር ከሚያሳየው፣ ቀደም ሲል ከተዘጋጀው ጋር የሚመሳሰል ጠቃሚ ዝርዝር ነው። እነዚህ ሁሉ ስሞች በኢሱ 15 ውስጥ ይገኛሉ፤ በዝርዝሩ ውስጥ የማይገኙት ዲቦን፣ ይቀብጽኤል (ይሁን እንጂ ቀብጽኤል የሚለው በኢሱ 15፥21 ላይ ይመ)፣ ኢያሱ፣ ምኮና እንዲሁም ዓይንሪሞን (ይሁን እንጂ በኢሱ 15፥32 ላይ ዓይን እና ሪሞን የሚለውን ይመ) ናቸው። ነገር ግን የስም ዝርዝሩ ሁሉን የያዘ አይደለም፤ ምክንያቱም በም3፤ በዕዝ 2፥21-22 ላይ የተጠቀሱት የብዙ ከተሞች ስም ይጐድለዋል። የይሁዳ ሳንቲሞች በዚህ ክፍል ከተጠቀሱት ስፍራዎች ውጭ በሌላ ቦታ አልተገኙም።

11፥25 *በቂርያት አርባቅና፤* የዘፍ 23፥2 ማብ ይመ። ይህች ከተማ በግሪኮች ዘመን ከሌሎች የይሁዳ አውራጃ ከተሞች ጋር በኢዱማውያን እጅ ወድቃለች።

11፥26 *በሞላዳ፤* በቤርሳቤህ አቅራቢያ የምትገኝ ስትሆን፣ በኋላ ግን በኢዱማውያን ተይዛለች። *በቤትጳሌጥ፤* ትርጕሙ፣ "የመጠጊያ ቤት" ማለት ሲሆን፣ በቤርሳቤህ አቅራቢያ ትገኛለች።

11፥27 *በሐጸርሹዓል፤* የስሙ ትርጕም "የቀበሮ ዐጥር" ማለት ነው (1ዜና 4፥28 ይመ)። *በቤርሳቤህና፤* የዘፍ 21፥31 ማብ ይመ፤ የስሙ ትርጕም፣ "የሰባት ውሃ ጕድጓድ" ወይም "የመሐላው ውሃ ጕድጓድ" ማለት ነው። የሥነ ቅርስ ቍፋሮ ግኝት እንደሚያመለክተው ከተማዪቱ በ701 ዓ.ቅ.ክ በሰናክሬም ተደምስሳለች፤ በፋርስ ዘመነ መንግሥት ግን ሕዝቡ እንደ ገና ሰፍሮባት ነበር።

11፥28 *በጺቅላግ፤* ይህችን ከተማ የጌት ንጉሥ አንኩስ ለዳዊት ሰጥቶት ነበር (1ሳሙ 27፥6)፤ ከዚያም በአማሌቃውያን ተያዘች (1ሳሙ 30፥1፤ ኢሱ 15፥31 ይመ)።

11፥29 *በዓይንሪሞን፤* የስሙ ትርጕም፣ "የሮማን ፍሬ ምንጭ" ማለት ነው፤ ከቤርሳቤህ ዐሥራ አራት ኪ.ሜ. ያህል ርቃ በስተ ሰሜን ምሥራቅ ትገኝ የነበረችው ቂርቤት ዑም ኤር ራማሚን ሳትሆን አትቀርም (ኢሱ 15፥32 ይመ)። *በጸርዓ፤* የመሳ 13፥2 ማብ ይመ። *በየርሙት፤* ከኤሉተሮፖሊስ (ከቤት ይብሪን) በስተ ሰሜን ምሥራቅ ዐሥራ ሦስት ኪ.ሜ. ያህል ርቃ የምትገኝ ስትሆን፣ የኢያሱን ወረራ ለማደናቀፍ ከሞከሩት፣ በስተ ደቡብ ከነበሩት አምስት የከነዓን ከተሞች አንዷ ነበረች (ኢሱ 10፥3-5)።

11፥30 *በዛኖዋ፤* በይሁዳና በፍልስጥኤም መካከል በኰረብታማው በሺጳላህ ወረዳ የነበረች መንደር ናት። የዛኖዋ ሰዎች የሸለቆ በር የተባለውን የኢየሩሳሌም ቅጥር መግቢያ መልሰው ሠርተዋል (3፥13)፤ ዛኖው ከቤትሳሚስ በስተ ደቡብ ምሥራቅ አምስት ኪ.ሜ. ያህል ርቃ ከምትገኘው ከቂርቤት ዛኑ ጋር ተጠቅሳለች። በዓዶላምና፤ የዘፍ 38፥1 ማብ ይመ። *በለኪሶና፤* ኢሱ 10፥3 እንዲሁም የኢሳ 36፥2፤ የሚክ 1፥13 ማብ ይመ። *በዓዜቃና፤* የኤር 34፥7 ማብ ይመ። *ሄኖም፤* ከኢየሩሳሌም በስተ ምዕራብና በስተ ደቡብ የሚገኘው ሸለቆ ነው።

*11፥31-35፤* እዚህ ላይ ከተዘረዘሩት የብንያም ከተሞች አብዛኞዎቹ በ7፥26-38፤ ዕዝ 2፥23-35 ላይም ተጠቅሰዋል።

11፥31 *ከጌባ፤* 12፥28፤ እንዲሁም የ1ሳሙ 13፥3 ማብ ይመ። *በማክማስ፤* የ1ሳሙ 13፥2 ማብ ይመ። *በጋያ፤* የጋይ ከተማ ሌላው መጠሪያ ነው (የኢሱ 7፥2 ማብ ይመ)። *በቤቴልና፤* የዘፍ 12፥8፤ የኢሱ 7፥2፤ የዕዝ 2፥28፤ የአሞ 4፥4 ማብ ይመ።

11፥32 *በዓናቶት፤* የኤር 1፥1 ማብ ይመ። *በኖብና፤* የ1ሳሙ 21፥1 ማብ ይመ። *በሐናንያ፤* ቢታንያ ሳትሆን አትቀርም፤ የስሙ ትርጕም፣ "የሐናንያ ቤት" ማለት ነው (የማቴ 21፥17 ማብ ይመ)።

1፥33 *በጊቴም፤* ይህች ከተማ የነበረችበት ቦታ በውል አይታወቅም።

11፥34 *ሐዲድ፤* ከሉድ በስተ ሰሜን ምሥራቅ አምስት ወይም ስድስት ኪ.ሜ ያህል ርቃ ትገኛለች (7፥37፤ ዕዝ 2፥33 ይመ)።

11፥35 *በሉድና፤* የዕዝ 2፥33 ማብ ይመ። *በኦኖ፤* የ6፥2 ማብ ይመ። *የእጅ ጥበብ ባለሙያዎች ሸለቆ!* 1ዜና 4፥14 እና አማራጭ ትርጕሙን ይመ። ይህ ሸለቆ በሉድና በኦኖ መካከል የሚገኘው ትልቁ ሸለቆ ሳይሆን አይቀርም። ስሙ የፍልስጥኤሞችን የብረት

ስፍራ ተቀመጡ።
36በይሁዳ ከነበሩት ሌዋውያን ከፊሎቹ
በብንያም ምድር ተቀመጡ።

## ካህናትና ሌዋውያን

12 ከሰላትያል ልጅ ከዘሩባቤልና ከኢ
ያሱ ጋር የተመለሱት ካህናትና
ሌዋውያን እነዚህ ነበሩ፤
ሠራያ፣ ኤርምያስ፣ ዕዝራ፣
2አማርያ፣ መሉክ፣ ሐጡስ፣
3ሴኬንያ፣ ሬሁም፣ ሜሪሞት፣
4አዶ፣ጌንቶን፣አብያ፣
5ሚያሚን፣ መዓድያ፣ ቢልጋ፣
6ሸማያ፣ ዮያሪብ፣ ዮዳኤ፣
7ሰሉ፣ዓሞቅ፣ ኬልቅያስና ዮዳኤ።
እነዚህ በኢያሱ ዘመን የካህናቱና የወንድሞ
ቻቸው አለቆች ነበሩ።
8ሌዋውያኑ ደግሞ ኢያሱ፣ ቢንዊ፣ ቀድም
ኤል፣ ሰራብያ፣ ይሁዳ እንዲሁም ከወንድ
ሞቹ ጋር የምስጋና መዝሙር ኀላፊ የሆነው
መታንያ ነበሩ። 9ወንድሞቻቸው የሆኑት
በቅቡቅያና ዑኒም በአገልግሎት ጊዜ ከእነርሱ
ትይዩ ይቆሙ ነበር።
10ኢያሱ ዮአቂምን ወለደ፤ ዮአቂም ኤል
ያሴብን ወለደ፤ ኤልያሴብ ዮአዳን ወለደ፤
11ዮአዳ ዮናታንን ወለደ፤ ዮናታንም ያዱ
አን ወለደ።
12በዮአቂም ዘመን የካህናቱ ቤተሰብ
አለቆች እነዚህ ነበሩ፤
ከሠራያ ቤተ ሰብ፣ ምራያ፤
ከኤርምያስ፣ ሐናንያ፤
13ከዕዝራ፣ ሜሱላም፤
ከአማርያ፣ ይሆሐናን፤
14ከሙሊኪ፣ ዮናታን፤
ከሰብንያ፣ ዮሴፍ፤
15ከካሪም፣ ዓድና፤
ከመራዮት፣ ሔልቃይ፤
16ከአዶ፣ ዘካርያስ፤
ከጌንቶን፣ ሜሱላም፤
17ከአብያ፣ ዝክሪ፤
ከሚያሚንና ከሞዓድያ፣ ፈልጣይ፤
18ከቢልጋ፣ ሳሙስ፤
ከሸማያ፣ ዮናታን፤
19ከዮያሪብ፣ መትናይ፤
ከዮዳኤ፣ አዚ፤
20ከሳላይ፣ ቃላይ፤
ከዓሞቅ፣ ዔቤር፤
21ከኬልቅያስ፣ ሐሸብያ፤
ከዮዳኢ፣ ናትናኤል።
22በኤሊያሴብ፣ በዮአዳ፣ በዮሐናንና በያ
ዱአ ዘመን የሌዋውያኑ ቤተ ሰብ አለቆችና
ካህናቱ፣ በፋርሳዊው በዳርዮስ ዘመነ መንግ
ሥት ተመዝግበው ነበር። 23ከሌዋውያን ዘሮች
መካከል እስከ ኤሊያሴብ ልጅ እስከ ዮሐናን
ድረስ ያሉት የየቤተ ሰቡ ኀላፊዎች በታሪክ
መጽሐፍ ተመዝግበው ነበር። 24የሌዋውያኑ
መሪዎች ሐሸብያ፣ ሰራብያ፣ የቀድምኤል
ልጅ ኢያሱ ነበሩ፤ እነርሱም ከወንድሞቻ
ቸው ፊት ለፊት ሆነው የእግዚአብሔር ሰው
ዳዊት በሰጠው መመሪያ መሠረት እየተቀ
ባበሉ ውዳሴና ምስጋና ያቀርቡ ነበር።
25በቅጥሩ በሮች አጠገብ ያሉትን ዕቃ ቤቶች
የሚጠብቁት ዘቦች ደግሞ መታንያ፣ በቅቡ
ቅያ፣ አብድዩ፣ ሜሱላም፣ ጤልሞንና ዓቁብ
ነበሩ። 26እነዚህም በኢዮሴዴቅ ልጅ፣ በኢ
ያሱ ልጅ በዮአቂም፣ በአገረ ገዢ በነህምያ፣

12፥1 1ዜና3፥19፤ ዕዝ2፥2፤3፥2፤ ነህ10፥1-8፡9፤ዘካ4፥6-10
12፥4 ቍ16፤ 1ዜና24፥10፤ዘካ1፥1፤ ሉቃ1፥5
12፥6 1ዜና24፥7
12፥8 ዕዝ 2፥2፤ ነህ11፥17
12፥10 ዕዝ10፥24፤ ነህ 3፥20
12፥16 ቍ4
12፥17 1ዜና24፥10
12፥24 2ዜና8፥14፤ዕዝ2፥40

ባለቤትነት የሚያመለክት ሊሆን ይችላል (1ሳሙ 13፥19-20)።

12፥1 *ከሰላትያል ልጅ ከዘሩባቤልና፤* ዕዝ 3፥2፡8፤5፥2፤ እንዲሁም የሐጌ 1፥1 ማብ ይመ። *ከኢያሱ፤* በ538 ዓ.ቅ.ክ ከባቢሉን ምርኮ የተመለሰ ሰው ነው (ቍ 10:26፤ 7፥7፤ ዕዝ 2፥2 እና ማብ፤ሐጌ 1፥1፤ዘካ 3፥1 እና ማብ ይመ)። *ዕዝራ፤* መጽሐፈ ዕዝራን የጻፈውና ከሰማንያ ዓመት በኋላ ከምርኮ የተመለሱትን አይሁድ የመራው ሰው አይደለም።

12፥7 *የካህናቱና ...አለቆች፤* ካህናትን በሃያ አራት ምድብ ተራ መድቦ ማሠራት የተጀመረው በዳዊት ዘመን ነው (1ዜና 24፥3፡7-19)። በቍ 1-7 ላይ ሃያ ሁለት የካህናት ወገን መሪዎች ተጠቅሰዋል። የሃያ አራቱን ምድብ ካህናት ስም ዝርዝር የያዘው ጽሑፉ በፓለስቲና በየምኵራቡ ሳይሰቀል አልቀረም። እስካሁን ድረስ ይህ ጽሑፍ የተቀረጸባቸው ሁለት የሰሌዳ ስብርባሪዎች ብቻ ተገኝተዋል፤ ከእነዚህም አንዱ በ1920ዎቹ በአስቀሎና፣ ሁለተኛው በ1960ዎቹ በቂሣርያ የተገኙ ሲሆን፣ የተቀረጹበትም ዘመን በሦስተኛውና በአራተኛው ምእተ ዓመት ከክርስቶስ ልደት በኋላ ነበር።

12፥9 *ከእነርሱ ትይዩ፤* ቍ 24፤ ዕዝ 3፥11 እና ማብ ይመ፤ ከ2ዜና 7፥6 ጋር ያነጻጽሩ። አዘማመራቸው አንዱ ቡድን ከሌላው ቡድን ትይዩ በመቆም እየተቀባበሉ ነበር። *በአገልግሎት፤* ይህን ለመግለጽ የገባው የዕብራይስጡ ቃል በፈረቃ ቆሞ ማገልገልን ያመለክታል፤ በቁምራን ከተገኙት ጽሑፎች የአንዱ ርእስ "ምስማሮት" ሲሆን፣ ይህም የቤተ መቅደሱ አገልግሎት በፈረቃ መሆኑን ዝርዝር መግለጫ ይሰጣል።

12፥10 *ኢያሱ፤* የቍ 1 ማብ ይመ። *ዮአቂምን፤* ቍ 12:26 ይመ። *ኤልያሴብን፤* ቍ 22-23 ይመ፤ ቅጥሩን መልሶ በመገንባቱ ሥራ ውስጥ አስተዋፅኦ ያደረገ ሊቀ ካህን ነበረ (3፥1፡20-21፤13፥28)። ኤልያሴብ የተባለ አንድ ካህን ለአሞናዊው ለጦብያ በቤተ መቅደሱ ግቢ ውስጥ ማረፊያ ክፍል በመስጠቱ፣ ቤተ መቅደሱን አርክሶ ነበር (13፥4:7)። ይህ ኤልያሴብና ሊቀ ካህናቱ ኤልያሴብ አንድ ሰው ይሁኑ ወይም አይሁኑ የሚታወቅ ነገር የለም።

12፥11 *ዮናታንን፤* በቍ 22 ላይ ባለው የስም ዝርዝር መሠረት ዮሐናን በዮአዳና በያዱአ መካከል ተጠቅሶ መገኘቱ፣ በቍ 23 ላይ ደግሞ ዮሐናን የኤልያሴብ ልጅ እንደ ሆነ መገለጹ በዚህ ስፍራ "ዮሐናን" መባል የነበረበት በስሕተት "ዮናታን" ተብሎ አል ብለው የሚናገሩ አሉ፤ ከዚህም በላይ በግብፅ አገር ኤሌፋንታይ በተባለው ቦታ "ዮሐናን" የሚል ስም በፓፒረስ ላይ ተጽፎ በመገኘቱ ከሊቀ ካህናቱ ዮሐናን ጋር አንድ ናቸው የሚሉም አሉ፤ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን ከኤሌፋንታይኑ ፓፒረስ ጽሑፍ ጋር የሚስማማ ነገር ተናግሮአል። ይሁን እንጂ እንዲህ ዐይነቱ ግምት አከራካሪ ነው።

*12፥12-21፤* በቍ 2 ላይ ካለው ከሐጡስ በስተቀር፣ ከቍ 1-7 የተዘረዘሩት ሃያ ሁለቱ የካህናት ቤተ ሰቦች ስም በዚህኛው ዝርዝር ውስጥ (አንዳንዶቹ ስሞች ጥቂት ለውጥ ያለ አጠራር ቢታይባቸውም) ተደግሞአል፤ ይህ ዝርዝር በስድስተኛው ምዕተ ዓ.ቅ.ክ ማገባደጃ ወይም በአምስተኛው ምእተ ዓመት ዓ.ቅ.ክ መጀመሪያ ላይ ሊቀ ካህናት በነበረው በዮአቂም ዘመን (ቍ 12) የነበረ ነው።

12፥22 *በፋርሳዊው በዳርዮስ፤* ይህ ሰው ዳግማዊ ዳርዮስ ኖቱስ (423-404 ዓ.ቅ.ክ) ወይም ሣልሳዊ ዳርዮስ ኮደማኑስ (336-331 ዓ.ቅ.ክ) ሊሆን ይችላል።

12፥23 *በታሪክ መጽሐፍ፤* ከ7፥5 ጋር ያነጻጽሩ። ይህ መጽሐፍ የቤተ መቅደሱ ወቅታዊ ድርጊቶችና ሁኔታዎች እንዲሁም የተለያዩ ዝርዝሮችና ሰነዶች የሚዘገቡበት ጽሑፍ ሳይሆን አይቀርም። የፋርስን ነገሥታት የታሪክ አመዘጋገብ ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ (ዕዝ 4፥15፤ አስ 2፥23፤ 6፥1፤10፥2)፤ እንዲሁም በመጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊና ካልዕ፣ "የነገሥታት ታሪክ መጽሐፍ" ተብሎ ብዙ ጊዜ የተጠቀሰውን ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ።

12፥26 *በነህምያ ... በዕዝራ፤* የ8፥9 ማብ ይመ።

በካህኑና በጸሓፊው በዕዝራ ዘመን አገለገሉ።

## የኢየሩሳሌም ቅጥር ምረቃ በዓል

27የኢየሩሳሌም ቅጥር ሲመረቅ ሌዋው
ያኑ በምስጋና መዝሙር፣ በጸናጽል፣ በበገ
ናና በመሰንቆ ድምፅ የምረቃውን በዓል
በደስታ እንዲያከብሩ ከሚኖሩበት ተፈል
ገው ወደ ኢየሩሳሌም መጡ። 28መዘምራ
ኑንም እንደዚሁ በኢየሩሳሌም ዙሪያ ካለው
ከነጦፋውያን መንደሮች በአንድነት ሰበሰ
ቧቸው። 29በኢየሩሳሌም ዙሪያ የራሳቸውን
መንደሮች ሠርተው ስለ ነበር፣ መዘምራኑን
ያመጧቸው ከቤት ጌልገላ፣ ከጌባና ከዓዝ
ሞት አካባቢ ነው። 30ካህናቱና ሌዋውያኑ
በሥርዐቱ መሠረት ራሳቸውን ካነጹ በኋላ፣ ሕዝ
ቡን፣ ቅጥሩና በሮቹን አነጹ።

31እኔም የይሁዳን መሪዎች በቅጥሩ ግንብ
አናት ላይ እንዲወጡ[ሀ] አደረግሁ፤ ደግሞም
ምስጋና እንዲያቀርቡ ሁለት ታላላቅ የመዘ
ምራን ቡድን መደብሁ። አንዱ በቅጥሩ ግንብ
አናት[ለ] በስተ ቀኝ በኩል "ቈሻሻ መጣያ በር"
ወደሚባለው ሄደ። 32እነዚህንም ሆሻያና ከይ
ሁዳ አለቆች እኩሌቶቹ ተከተሏቸው፤ 33የተከ
ተሏቸውም ከዓዛርያስ፣ ከዕዝራ፣ ከሜሱላም፣
34ከይሁዳ፣ ከብንያም፣ ከሸማያ፣ ከኤርምያስና፣
35እንዲሁም መለከት ከያዙ ጥቂት ካህናትና
ከአሳፍ ልጅ፣ ከዘኩር ልጅ፣ ከሚካያ ልጅ
ከመታንያ ልጅ፣ ከሸማያ ልጅ፣ ከዮናታን
ልጅ፣ ከዘካርያስ ጋር ነበር። 36ወንድሞቹ
ሸማያ፣ ኤዝርኤል፣ ሚላላይ፣ ጊላላይ፣ መዓይ፣
ናትናኤል፣ ይሁዳና አናኒም የእግዚአብሔር
ሰው ዳዊት ባዘዘው መሠረት የዜማ መሣሪ
ያዎቹን ይዘው ሄዱ፤ ሰልፉን የሚመራውም
ጸሓፊው ዕዝራ ነበረ። 37"ከምንጭ በር"
ተነሥተው በቀጥታ ወደ "ዳዊት ከተማ"
ደረጃዎች ወጡ፤ ከዚያም በቅጥሩ መውጫ
በኩል አድርገው ከዳዊት ቤት በላይ በስተ
ምሥራቅ ወደ ሚገኘው ወደ "ውሃ በር"
ሄዱ።

38ሁለተኛው የመዘምራን ቡድን በስተግራ
በኩል ሄደ፤ እኔም ከከፊሉ ሕዝብ ጋር
ሆኜ በቅጥሩ ግንብ[ሐ] ላይ፣ የእቶኑን ግንብ
በማለፍ እስከ ሰፊው ቅጥር ተከተልኋቸው፤
39ከዚያም ከኤፍሬም በር በላይ፣ በአሮጌ
በር[መ]፣ በዓሣ በር፣ በሐናንኤል ግንብ፣ በመ
ቶዎቹ ግንብ አልፈ እስከ "በጎች በር"
ድረስ ተከተልኋቸው። እነርሱም "በዘበኞች
በር" አጠገብ ሲደርሱ ቆሙ።

40ቀጥሎም ምስጋና ያቀረቡት ሁለቱ
የመዘምራን ቡድኖች፣ በእግዚአብሔር ቤት
ቦታቸውን ያዙ፤ እኔም ከግማሾቹ ሹማምት
ጋር ቦታዬን ያዝሁ፤ 41እንደዚሁም ካህናቱ
ኤልያቄም፣ መዕሤያ፣ ሚንያሚን፣ ሚካያ፣
ኤልዮዔናይ፣ ዘካርያስና ሐናንያ መለከታ
ቸውን ይዘው፣ 42መዕሤያ፣ ሸማያ፣ አልዓ
ዛር፣ ኦዚ፣ ይሆሐናን፣ መልክያ፣ ኤላምና
ኤጽር ቦታቸውን ያዙ፤ መዘምራኑ በይዝ
ረሕያ መሪነት ዘመሩ። 43እግዚአብሔር ታላቅ
ደስታ ስለ ሰጣቸው፣ በዚያች ዕለት ደስ
ብሏቸው ብዙ መሥዋዕት አቀረቡ፤ ሴቶችና
ልጆችም እንደዚሁ ደስ አላቸው፤ ከዚህም
የተነሣ በኢየሩሳሌም የነበረው የደስታ
ድምፅ እስከ ሩቅ ድረስ ይሰማ ነበር።

12፥27 ዘጸ20፥5፤ 2ሳሙ6፥5፤ 1ዜና15፥16፤28፤25፥6፤ መዝ92፥3
12፥28 1ዜና 2፥54፤9፥16
12፥30 ዘፀ19፥10፤ ኢዮ1፥5
12፥31 ነህ2፥13
12፥34 ዕዝ1፥5
12፥35 ዕዝ3፥10
12፥36 1ዜና15፥16፤ 2ዜና8፥14፤ዕዝ7፥6
12፥37 ነህ2፥14፤3፥26
12፥38 ነህ3፥8፤11
12፥39 2ነገ14፥13፤ 2ዜና33፥14፤ነህ3፥1፡6

[ሀ]31 ወይም *ከቅጥሩ ጎን እንዲሄዱ*
[ለ]31 ወይም *ከቅጥሩ ጎን*
[ሐ]38 ወይም *ከቅጥሩ ጎን*
[መ]39 ወይም *በጀሻና በር*

12፥27 ***ሲመረቅ፤*** የዕዝ 6፥16 ማብ ይመ። ***በጸናጽል፤*** የዕዝ 3፥10 ማብ ይመ። ጸናጽል በሃይማኖት ክብረ በዓላት ጊዜ የሚያገለግል መሣሪያ ነው (1ዜና 16፥42፤ 25፥1፤ 2ዜና 5፥12፤ 29፥25)። በጥ ንት ዘመን የነበሩ ጸናጽሎች በቤትሻሚሽና በቴል አቡ ሐዋም ተገኝተዋል። ***በበገናና፤*** የዘፍ 31፥27ማብ ይመ፤ ብዙውን ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውለው በሃይማኖት ክብረ በዓላት ጊዜ ነው (1ሳሙ 10፥5፤ 2ሳሙ 6፥5፤ መዝ 150፥3)። በዑር የተገኙ የበገና ስብርባሪዎችን፣ ልዩ ልዩ የበገና ሥዕሎችንና የጥንት ጽሑፎች ስለ በገና ቅኝት የሚሰጡትን መግለጫ መሠረት በማድረግ የጥ ንቱን በገና መልሶ መሥራት ተችሏል። ***በመሰንቆ፤*** በዚያን ጊዜ የነበረው መሰንቆ እንደ ክራር ዐይነት ሆኖ የአውታሮቹ ርዝመት እኩል ሲሆን ውፍረቱና የቅኝቱ ውጥረት ይለያይ ነበር (1ዜና 15፥16፤ ዳን 3፥5 ይመ)።

12፥28 ***ከነጦፋውያን፤*** ከቤተ ልሔም አካባቢ ከነጦፋ ከተ ማ የመጡ ሰዎች ናቸው (7፥26)።

12፥29 ***ከቤት ጌልገላ፤*** ኢያሪኮ አጠገብ የነበረችው ጌልገላ ልትሆን ትችላለች (የኢሱ 4፥19 ማብ ይመ)፤ ወይም ኤልያስ ይኖርባት የነበረውና ከቤቴል በስተ ሰሜን ዐሥራ አንድ ኪ.ሜ. ያህል ርቃ የምትገኘው ጌልገላ ትሆናለች።

12፥30 ***ካነጹ፤*** የዘሌ 4፥12 ማብ ይመ። መንፈሳዊ መነቃቃት በነበረበት ዘመን፣ ሌዋውያን በቤተ መቅደሱ ውስጥ የነበረውን ንዋየ ቅድሳት ሁሉ (1ዜና 23፥28) እንዲሁም ቤተ መቅደሱን ራሱን (2ዜና 29፥15) እንዳነጹ ተነግሮአል። የመንጻት ሥርዐት ዓላማ የእግዚአብሔርን ቅድስናና ንጽሕና ለማስተማር ነው (ዘሌ 16፥30)።

12፥31 ***ሁለት/ታላላቅ የመዘምራን ቡድን፤*** የቍ 38 ማብ ይመ። ሁለቱ ታላላቅ የክብረ በዓሉ ተካፋይ ቡድኖች እየተመሙ የተጓዙት፣ በቅጥሩ ምዕራባዊ ክፍል መካከል ከሚገኘው የሸለቆ በር አካባቢ (2፥13፡15፤3፥13) ተነሥተው ሊሆን ይችላል። የመጀ መሪያው ቡድን በዕዝራ መሪነት (ቍ 36) እየተመመ ከግራ ወደ ቀኝ ቅጥሩን ሲዞር፣ ሁለተኛው ደግሞ ከነህምያ ጋር (ቍ 38) ከቀኝ ወደ ግራ ቅጥሩን ዞሮአል። ሁለቱ ቡድኖች በውሃ በርና (ቍ 37) በጠባቂዎች በር (ቍ 39) መካከል ተገናኙ፤ ከዚያም ተያይዘው ወደ ቤተ መቅደሱ አደባባይ ገቡ፤ ከመዝ 48፥12-13 ጋር ያነጻ ጽሩ። ***በስተ ቀኝ በኩል፤*** ወይም "በስተ ደቡብ" ማለት ነው። በሴ ማውያን ልማድ ወደ ምሥራቅ መዞር የተለመደ ነበር፤ ስለዚህ ቀኝ እጅ የደቡብን አቅጣጫ ይወክላል (ኢሱ 17፥7፤ 1ሳሙ 23፥24፤ ኢዮ 23፥9 ይመ)። ***ቈሻሻ መጣያ በር፤*** የ2፥13 ማብ ይመ።

12፥35 ***መለከት፤*** የዕዝ 3፥10 ማብ ይመ። እያንዳንዱ የመዘምራን ቡድን መለከት የሚነፉ ካህናትና በሌሎች የዜማ መሣሪያዎች የሚያገለግሉ ሌዋውያን ነበሩት። ***ከአሳፍ፤*** የ11፥17 ማብ ይመ።

12፥36 ***ጸሓፊው ዕዝራ፤*** የዕዝ 7፥1፡6 ማብ ይመ።

12፥37 ***ከምንጭ በር፤*** የ2፥14 ማብ ይመ። ***ዳዊት ከተማ፤*** 3፥15 ይመ፤ የ2ሳሙ 5፥7 ማብ ይመ። ***ውሃ በር፤*** የ3፥26 ማብ ይመ።

12፥38 ***የመዘምራን ቡድን፤*** ቃል በቃል ሲተረጐም፣ "ምስጋና" ወይም "የአመስጋኞች ቡድን" ማለት ነው (ቍ 40 ይመ)። ***የእቶኑን ግንብ፤*** የ3፥11 ማብ ይመ። ***ሰፊው ቅጥር፤*** የ3፥8 ማብ ይመ።

12፥39 ***ከኤፍሬም በር፤*** የ3፥6፤ 8፥16 ማብ ይመ። ***በአሮጌ በር፤*** የ3፥6 ማብ ይመ። ***በዓሣ በር፤*** የ3፥3 ማብ ይመ። ***በሐናንኤል ግንብ ... በመቶዎቹ ግንብ ... በጎች በር፤*** የ3፥1 ማብ ይመ። ***በዘበኞች በር፤*** ከኤር 32፥2 ጋር ያነጻጽሩ።

12፥43 ***እግዚአብሔር ታላቅ ደስታ ስለ ሰጣቸው፤*** 1ዜና 29፥9፤ ዮና 4፥6 ይመ። ***ሴቶችና፤*** 8፥2፤ ዘፀ 15፥20 እና ማብ ይመ። ***እስከ ሩቅ ...ይሰማ ነበር፤*** የዕዝ 3፥13 ማብ ይመ፤ 1ነገ 1፥40፤ ከ2ነገ 11፥13 ጋር ያነጻጽሩ።

[44]በዚያን ቀን ስጦታው፣ በኵራቱና ዐሥ
ራቱ የሚቀመጥበት ዕቃ ቤት የሚጠብቁ
ሰዎች ተሾሙ:: እነርሱም በየከተሞች ዙሪያ
ከሚገኙት የእርሻ ቦታዎች ሕጉ በሚያዘው
መሠረት የካህናቱንና የሌዋውያኑን ድርሻ
ወደ ዕቃ ቤቱ ማምጣት ነበረባቸው፤ ይሁዳ
በሚያገለግሉ ካህናትና ሌዋውያን ደስ ተሰ
ኝተው ነበርና:: [45]እንደ መዘምራኑና በር ጠባ
ቂዎቹ ሁሉ፣ እነዚህም የአምላካቸውን አገልግ
ሎትና የመንጻቱን ሥርዐት በዳዊትና በልጁ
በሰሎሞን ትእዛዝ መሠረት ፈጸሙ::
[46]ቀድሞ በዳዊትና በአሳፍ ዘመን ለእግዚአ
ብሔር የሚቀርቡትን የውዳሴ መዝሙ
ችና ምስጋና የሚመሩ የመዘምራን አለ
ቆች ነበሩ:: [47]በዘሩባቤልና በነህምያም ዘመን
እስራኤል ሁሉ ለመዘምራኑና ለበር ጠባቂ
ዎቹ የየዕለቱን ድርሻ ይሰጡ ነበር፤ የሌሎ
ቹን ሌዋውያን ድርሻም ለብቻ ያስቀምጡ
ነበር፤ ሌዋውያኑም ለአሮን ዘሮች ድርሻቸ
ውን ያስቀምጡላቸው ነበር::

### ነህምያ በመጨረሻ የወሰደው የተሐድሶ እርምጃ

13 በዚያም ቀን የሙሴን መጽሐፍ ከፍ ባለ
ድምፅ ለሕዝቡ አነበቡ፤ አሞናዊም
ሆነ ሞዓባዊ ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ ፈጽሞ
እንዳይገባ የሚከለክል ተጽፎ ተገኘ፤ [2]ይህ
የሆነው እስራኤልን በምግብና ውሃ መስተን
ግዶ በመቀበል ፈንታ፣ በለዓም እንዲረግም
ላቸው በገንዘብ ስለ ገዙት ነበር:: ይሁን
እንጂ አምላካችን ርግማኑን ወደ በረከት
ለወጠው:: [3]ሕዝቡም ይህን ሕግ በሰሙ ጊዜ፣
የባዕድ ወገን የሆኑትን ሁሉ ከእስራኤል
ለዩ::

[4]ቀድሞ የአምላካችን ዕቃ ቤቶች ኀላፊ ሆኖ
የተሾመው ካህኑ ኤልያሴብ ነበር፤ እርሱም
ከጦብያ ጋር የጠበቀ ወዳጅነት ነበረው፤ [5]ከዚህ
በፊት የእህል ቍርባኑ፣ ዕጣኑ፣ የቤተ መቅ
ደሱ ዕቃዎች፣ የእህሉ ዐሥራትና፣ ለሌዋው
ያን፣ ለመዘምራንና ለበር ጠባቂዎች የታዘ
ዘው አዲሱ ወይንና ዘይት፣ ለካህናቱም
የሚመጣው ስጦታ ይቀመጥበት የነበረውን
ትልቁን የዕቃ ቤት እንዲኖርበት ሰጥቶት
ነበር::

[6]ይህ ሁሉ ሲሆን እኔ በኢየሩሳሌም አል
ነበርሁም፤ ምክንያቱም በባቢሎን ንጉሥ በአ
ርጤክስስ ሠላሳ ሁለተኛ ዓመት ተመልሼ
ወደ ንጉሡ ሄጄ ነበር:: ከጥቂት ጊዜም
በኋላ የንጉሡን ፈቃድ ጠይቄ [7]ወደ ኢየሩ
ሳሌም ተመለስሁ፤ በዚያም ኤልያሴብ በእግ
ዚአብሔር ቤት አደባባይ ለጦብያ አንድ
መኖሪያ ክፍል በመስጠት የፈጸመውን ክፉ
ድርጊት ተረዳሁ:: [8]እኔም በጣም ዐዘንሁ፤
የጦብያንም የቤት ዕቃ ሁሉ ከክፍሉ እያ
ወጣሁ ወደ ውጭ ጣልሁ:: [9]ክፍሎቹንም
እንዲያነጹ ትእዛዝ ሰጠሁ፤ ከዚያም የእግዚ
አብሔርን ቤት ዕቃዎች፣ የእህሉን ቍርባ
ንና ዕጣኑን ጭምር መልሼ አስገባሁ::

[10]እንዲሁም ለሌዋውያን የተመደበው ድርሻ
እንዳልተሰጣቸውና አገልግሎቱን በኀላፊነት
የሚመሩ ሌዋውያንና መዘምራን ሁሉ ወደ
የርስታቸው መመለሳቸውን ተረዳሁ:: [11]ስለ
ዚህ ሹማምቱን ገሥጬ "ቤተ መቅደሱ እስ
ከዚህ ቸል የተባለው ለምንድን ነው?" ብዬ
ጠየቅኋቸው:: ከዚያም እነርሱን በአንድነት
ሰብስቤ ወደ ምድብ ሥራቸው እንዲመለሱ
አደረግሁ::

[12]ይሁዳም ሁሉ የእህሉን፣ የአዲሱን ወይ
ንና የዘይቱን ዐሥራት ወደ ዕቃ ቤቶቹ

12፥44 ዘሌ27፥30፤ ዘዳ18፥8፤ነህ13፥4
12፥45 1ዜና6፥31፤23፥5፤ 2ዜና8፥14
12፥46 2ዜና35፥15፤29፥27፤ መዝ137፥4
12፥47 ዘዳ18፥8
13፥1 ቍ23፥ ዘዳ23፥3
13፥2 ዘኍ22፥3-11፤23፥7:11፤ ዘዳ23፥3:4-5
13፥3 ቍ23፤ነህ9፥2
13፥4 ነህ2፥10፤ 12፥44
13፥5 ዘሌ27፥30፤ ዘኍ18፥21
13፥6 ነህ2፥6
13፥7 ዕዝ10፥24፤ ነህ2፥10
13፥8 ማቴ21፥12-13፤ ማር11፥15-17፤ ሉቃ19፥45-46፤ ዮሐ2፥13-16
13፥9 ዘሌ 2፥1፤ 1ዜና23፥28፤ 2ዜና29፥5
13፥10 ዘዳ12፥19፤ 2ዜና31፥4
13፥11 ነህ10፥37-39፤ ሐጌ1፥1-9ሚል3፥8-9
13፥12 ዘዳ18፥8፤1ነገ7፥51፤ 2ዜና31፥5:6፤ ነህ10፥37-39፤ ሚል3፥10

12፥44 *ይሁዳ ... ደስ ተሰኝተው፤* ሕዝቡ ለካህናቱና ለሌዋውያኑ የሚሆን መባ በበጎ ፈቃድ ሰጠ (ከ2ቆሮ 9፥7 ጋር ያነጻጽሩ):: *በሚያገለግሉ፤* ዘዳ 10፥8 ይመ::

12፥46 *በአሳፍ፤* የ11፥17 ማብ ይመ::

12፥47 *ይሰጡ፤* ይህን ለመግለጽ የገባው የዕብራይስጡ ግሥ ባለማቋረጥ መስጠትን ያመለክታል::

*13፥1-2፤* ዘዳ 23፥3-6 ይመ::

13፥2 *በለዓም፤* የዘኍ 22፥5 ማብ ይመ:: ከዮርዳኖስ ማዶ "ዴር አላ" በተባለ ስፍራ በስድስተኛው ምእተ ዓመት ዓ.ቅ.ክ ላይ የተቀረጸ አንድ የአረማይስጥ ጽሑፍ የበለዓምን ስም ይጠቅሳል::

13፥4 *ኤልያሴብ፤* የ12፥10 ማብ ይመ:: *ከጦብያ፤* የ2፥10 ማብ ይመ::

13፥5 *ትልቁን የዕቃ ቤት ... ሰጥቶት ነበር፤* ነህምያ ወደ ፋርስ ንጉሥ ቤተ መንግሥት ከሄደ በኋላ ከቀንደኛ ጠላቶቹ አንዱ የሆነው ጦብያ፣ ኤልያሴብ ከተባለ ሰው ጋር ገጥሞ፣ ዐሥራትና ሌላውም ዐይነት መባ ተሰብስቦ ወደሚቀመጥበት ክፍል ዘልቆ ገባ (10፥7 እና ማብ ይመ፤ ከዘኍ 18፥21-32፤ ከዘዳ 14፥28-29፤ 26፥12-15 ጋር ያነጻጽሩ):: በሌላ ቦታ የሜሱላም ክፍልና (3፥30) የዮሐናን ክፍል (ዕዝ 10፥6) የሚል ተጽፎ እናገኛለን::

13፥6 *በአርጤክስስ ሠላሳ ሁለተኛ ዓመት፤* የ5፥14 ማብ ይመ:: *በባቢሎን ንጉሥ፤* ቂሮስ ባቢሎንን ድል ካደረገ በኋላ በዚህ የማዕረግ ስም ተጠርቶበታል (ዕዝ 5፥13 ይመ)፤ ከዚያም በኋላ የአኬሜኒድ (የፋርስ) ነገሥታት በዚሁ የማዕረግ ስም ተጠርተውበታል::

13፥7 *ወደ ኢየሩሳሌም ተመለስሁ፤* ኤሌፋንታይን በተባለ ቦታ (ግብፅ አገር) የተገኘው የፓፒረስ ጽሑፍ እንደሚያመለክተው፣ ባጎሒ የይሁዳ አስተዳዳሪ በነበረበት ዘመን ከ407 ዓ.ቅ.ክ በፊት የነህምያ ሁለተኛው ዙር የሥልጣን ዘመን ሳያበቃ አልቀረም:: ነህምያ የመጀመሪያውን የሥልጣን ዘመን በጨረሰ ጊዜ፣ ወንድሙ ሐናኒ በእርሱ ምትክ እንደ ተሾመ የሚናገሩ አሉ (የ1፥2 ማብ ይመ):: *አደባባይ፤* የ8፥16 ማብ ይመ:: ዘሩባቤል ያሠራው ቤተ መቅደስ ሁለት አደባባይ ነበረው (ዘካ 3፥7፤ ከኢሳ 62፥9 ጋር ያነጻጽሩ)::

13፥8 *ዐዘንሁ ... ጣልሁ፤* ነህምያ ቍጣውን በተግባር ገለጠ (ከቍ 24–25፤ 5፥6-7 ጋር ያነጻጽሩ):: ዕዝራ "ደንግጦ የተቀመጠበትን" (ዕዝ 9፥3) ሁኔታ ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ:: ነህምያ የወሰደው እርምጃ፣ ጌታ ኢየሱስ በቤተ መቅደሱ ቅጥር ግቢ ውስጥ በገንዘብ መንዛሪዎችና በሻጮች ላይ የወሰደውን እርምጃ ያስታውሰናል (ማቴ 21፥12-13)::

13፥9 *ክፍሎቹንም፤* በቍ 5-8 ላይ የተጠቀሰው አንድ ክፍል ብቻ ቢሆንም፣ ተጨማሪ ክፍሎችም ነበሩ::

*13፥10፤* ነህምያ ተከሥተው የቈዩትን ችግሮች ማስተካከሉን የሚያመለክት ነው:: በመሠረቱ ሌዋውያን የራሳቸው የሆነ ርስት አልነበራቸውም (ዘኍ 18፥20:23-24፤ ዘዳ 14፥29፤ 18፥1)፤ ይሁን እንጂ አንዳንዶቹ የግል ገቢ ሳይኖራቸው አልቀረም (ዘዳ 18፥8):: በመሆኑም የሌዋውያኑ የገቢ ምንጭ ከታማኝ ሰዎች የሚገኘው ድጋፍ ብቻ ነበር:: ብዙ ሌዋውያን ከምርኮ ያለተመለሱትም በዚሁ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም (ዕዝ 8፥15-20 ይመ):: እግዚአብሔርን በማገልገላቸው ምክንያት ቍሳዊ ጥቅም እንደ ጐደለባቸው በመቍጠር ስላጕረመረሙት ሰዎች በሚል 2፥17፤ 3፥13-15 ላይ ይመ::

13፥11 *ቸል የተባለው፤* የ10፥39 ማብ ይመ::

13፥12 *ዐሥራት፤* 12፥44 ይመ:: ሕዝቡ እግዚአብሔርን በማምለካቸው የተገኘውን በረከት በሚመለከቱበት ጊዜ፣ ዐሥራት

አስገቡ:: 13ለዕቃ ቤቶቹም ካህኑን ሰሌም
ያን፣ ጸሓፊውን ሳዶቅንና ፈዳያ የተባለውን
ሌዋዊ ኀላፊ አድርጌ ሾምሁ፤ መደብሁ፤
እንዲሁም የመታንያን ልጅ፣ የዘኩርን ልጅ
ሐናን ረዳታቸው አደረግሁ፤ ምክንያቱም
እነዚህ ሰዎች ታማኞች ነበሩ:: ሥራቸውም
ለወንድሞቻቸው የተመደበውን ቀለብ ማከ
ፋፈል ነበረ::
14አምላኬ ሆይ፤ ስለዚህ ነገር አስበኝ፤ ለአ
ምላኬ ቤትና ለአገልግሎቱ ስል በታማኝነት
ያከናወንሁትን አታጥፋ::
15በእነዚያ ቀናት በይሁዳ በሰንበት ቀን
የወይን መጭመቂያ የሚረግጡ፣ እህል የሚ
ያስገቡና፣ የወይን ጠጅ፣ የወይን ዘለላ፣ የበ
ለስና ሌሎችን የጭነት ዐይነቶች ሁሉ በአ
ህያ ላይ የሚጭኑ ሰዎች አየሁ፤ ይህን ሁሉ
ወደ ኢየሩሳሌም ያስገቡ የነበረው በሰን
በት ቀን ነበረ:: ስለዚህ በዚያን ቀን ምግብ
እንዳይሸጡ ከለከልኋቸው:: 16በኢየሩሳሌም
የሚኖሩ የጢሮስ ሰዎችም ዓሣና ልዩ ልዩ
ሸቀጣ ሸቀጥ በሰንበት ቀን እያመጡ ለይ
ሁዳ ሕዝብ በኢየሩሳሌም ይሸጡ ነበር::
17እኔም የይሁዳን መኳንንት በመገሠጽ እንዲህ
አልኋቸው፤ "ሰንበትን በማርከስ ይህ የምት
ፈጽሙት ክፉ ድርጊት ምንድን ነው? 18የቀ
ድሞ አባቶቻችሁ ያደረጉት ይህንኑ አልነ
በረምን? አምላካችንስ ይህን ሁሉ ጥፋት በእ
ኛና በዚች ከተማ ላይ ያመጣው በዚሁ
በደላችን አይደለምን? አሁንም እናንተ ሰን
በትን በማርከስ የባሰ መከራ በእስራኤል
ላይ ታመጣላችሁ::"

19በሰንበት ዋዜማ በኢየሩሳሌም በሮች
ላይ የምሽቱ ጥላ ማረፍ ሲጀምር በሮቹ
እንዲዘጉና፣ ሰንበት እስኪያልፍ ድረስ እን
ዳይከፈቱ አዘዝሁ፤ በሰንበት ቀን ጭነት
እንዳይገባም ከራሴ ሰዎች አንዳንዶቹን በየ
በሩ ላይ አቆምሁ:: 20የልዩ ልዩ ሸቀጣ ሸቀጥ
ነጋዴዎችና ቸርቻሪዎች ከኢየሩሳሌም ውጭ
አንድ ወይም ሁለት ጊዜ አድረዋል:: 21እኔ
ግን፣ "ከቅጥሩ ውጭ የምታድሩት ለምንድን
ነው? እንዲህ ያለውን ነገር ዳግመኛ ብታ
ደርጉ እጄን አነሣባችኋለሁ" ስል አስጠነቀቅ
ኋቸው፤ እነርሱም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በሰንበት
ቀን አልመጡም:: 22ከዚያም ሌዋውያኑ ራሳ
ቸውን እንዲያነጹ፣ ሄደውም የቅጥሩን በር
እንዲጠብቁና የሰንበትንም ቀን እንዲቀድሱ
አዘዝኋቸው::
አምላኬ ሆይ፤ ስለዚህም ደግሞ አስበኝ፤
እንደ ታላቅ ፍቅርህም ብዛት ምሕረት
አድርግልኝ::
23በእነዚያም ቀናት የአሽዶድን፣ የአሞ
ንንና የሞዓብን ሴቶች ያገቡ አይሁድ አገ
ኘሁ:: 24ከልጆቻቸውም እኩሌቶቹ የአሽ
ዶድን፣ ወይም ከሌሎቹ ሕዝቦች የአንዱን
ቋንቋ እንጂ የአይሁድን ቋንቋ መናገር አይ
ችሉም ነበር:: 25እኔም ገሠጽኋቸው፤ ርግማ
ንም አወረድሁባቸው:: አንዳንዶቹን መታኋ
ቸው፤ ጠጕራቸውንም ነጨሁ:: በእግዚአብሔር
ስም እንዲህ ስል አማልኋቸው፤ "ሴቶች ልጆ
ቻችሁን ለወንዶች ልጆቻቸው አትስጡ፤ ሴቶች
ልጆቻቸውንም ለወንዶች ልጆቻችሁ አት
ውሰዱ:: 26የእስራኤል ንጉሥ ሰሎሞን ኀጢ

13፥13 ነህ12፥44፤ ሐሥ6፥1-5
13፥14 ዘፍ8፥12፥2ነገ20፥3
13፥15 ዘፀ20፥8-11፤34፥21፤ ዘዳ5፥12-15
13፥16 ነህ10፥31
13፥18 ነህ10፥31፤ ኤር44፥23
13፥19 ዘሌ23፥32
13፥22 ዘፍ8፥1፤ነህ1፥8
13፥23 ቀኍ1፤ ዘፀ34፥16፤ሩት1፥4፤ ዕዝ9፥1-2፤ ነህ10፥30፤ሚክ2፥11
13፥24 አስ1፥22፤3፥12፤8፥9
13፥25 ዘፀ34፥16፤ ዕዝ10፥5
13፥26 ዘፀ34፥16፤ 2ሳሙ12፥25፤1ነገ3፥1 3፤11፥3፤2ዜና1፥12

ለመክፈል ሙሉ ፈቃደኞች ሆነው ተገኝተዋል:: እግዚአብሔርም በዚሁ ዘመን አካባቢ ሚልክያስን አስነሥቶ ነበር፤ ዐሥራትን በታማኝነት ማውጣት ታላቅ በረከት እንደሚያስገኝ ሚልክያስ በመልእክቱ ይነግራቸው ነበር (ሚል 3፥10):: ሕግ በሙሴ አማካይነት ከመሰጠቱ አስቀድሞ እንኳ ዐሥራት ማውጣት በእግዚአብሔር ሰዎች ዘንድ የተለመደ ነበር፤ መልከ ጼዴቅ አብርሃምን ባረከው፤ አብርሃምም ካለው ሁሉ ዐሥራት አውጥቶ ሰጠው (ዘፍ 14፥19-20)፤ ያዕቆብም በቤቴል ሕልም ካየ በኋላ፣ ከሚያገኘው ሁሉ ለእግዚአብሔር ዐሥራት ለመስጠት ተሳለ (ዘፍ 28፥22)::

*13፥13*፤ ከአራቱ የንብረት ክፍል ኀላፊዎች አንዱ ካህን፣ አንዱ ሌዋዊ፣ አንዱ ጸሓፊ ሲሆኑ፣ ሌላው ግን ማዕረግ የሌለው ተራ ሰው ነበር:: *ታማኞች*፤ ነህምያ እምነት የሚጣልባቸውን ሰዎች መርጦ አከፋፋይና ተቈጣጣሪ እንዲሆኑ ያደረገው እያንዳንዱ ሰው የሚገባውን በትክክል ማግኘት እንዲችል በማሰብ ነበር፤ የመጀመሪያዪቱም ቤተ ክርስቲያን ለተመሳሳይ ተግባር ዲያቆናትን መርጣ ሾማ ነበር (ሐሥ 6፥1-5)::

13፥15 *የወይን መጭመቂያ የሚረግጡ፤* የኢሳ 5፥2፤ 16፥10 ማብ ይመ:: *በሰንበት ቀን፤* የሰንበትን ዕረፍት ሽሮ የተከለከለውን ተግባር ማከናወን አይሁዳዊ ያልሆኑ ነጋዴዎች ባሕርይ ነው (10፥31፤ ኢሳ 56፥1-8 ይመ):: በአንጻሩ ብዙዎች ስለ ሰንበት ከነበራቸው አክብሮት የተነሣ የልጆቻቸውን ስም "ሳባታይ" ብለው ይሰይሙ ነበር (8፥7፤ 11፥16፤ ዕዝ 10፥15 ይመ)::

13፥16 *የጢሮስ፤* የኢሳ 23፥1 ማብ ይመ:: *ዓሣና፤* የጢሮስ ሰዎች ከአገራቸው ወደ ውጭ በንግድ መልክ የሚልኩት ዓሣ አብዛኛው የደረቀ፣ በእንፋሎት የበሰለ ወይም በጨው የታሸ ነበር (ሕዝ 26፥4-5፡14):: ዓሣን መመገብ በእስራኤላውያን ዘንድ የተለመደ ሲሆን፣ ብዙውን ዓሣ የሚያገኙትም ከገሊላ ባሕር ነበረ (ዘሌ 11፥9፤ ዘኍ 11፥5፤ ማቴ 15፥34፤ ሉቃ 24፥42፤ ዮሐ 21፥5-13):: የሚሸጡውም የዓሣ በር ተብሎ በሚታወቀው የቅጥሩ ደጃፍ አጠገብ ባለው የገበያ ቦታ ነበረ (የ3፥3 ማብ ይመ)::

13፥17 *መኳንንት በመገሠጽ፤* ምክንያቱም ኀላፊነቱ የእነርሱ ስለ ነበረ ነው:: *በማርከስ* በተቀደሰውና ለእግዚአብሔር ሥራ በተለየው መጠቀም ክብሩን ማቃለል ነው (ሚል 2፥10-11 ይመ)::

13፥19... *በሮች ላይ የምሽቱ ጥላ ማረፍ ሲጀምር፤* ፀሐይ ከመጥለቋ በፊት፣ ሰንበት ከገባ በኋላ ማለት ነው:: የእስራኤላውያን የቀን አቈጣጠር ከጀምበር መጥለቂያ እስከ ጀምበር መጥለቂያ ሲሆን፣ ይህም የባቢሎናውያንን የዘመን አቈጣጠር የተከተለ ነው:: ግብፆች ግን የሚቈጥሩት ከጀምበር መውጫ እስከ ጀምበር መውጫ ነው:: የሰንበት መግቢያ ትክክለኛ ጊዜ የሚታወቀው ካህኑ በሚነፋው የመለከት ድምፅ ነበር:: ሚሽና በተባለው የአይሁድ መጽሐፍ መሠረት፣ "በሰንበት ዋዜማ ስድስት ጊዜ መለከት ይነፋ ነበር፤ ሦስቱ ሕዝቡ ሥራውን እንዲያቆም የሚያሳስብ ሲሆን፣ ሦስቱ ደግሞ የተቀደሰውን ከረከሰው የሚለዩበት ምልክት ነበር::" ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን በሰንበት ዋዜማ ሕዝቡ ሥራውን እንዲያቆም፣ በማግሥቱም የዕለተ ሰንበቱን ማብቂያ ለማብሠርና ሕዝቡ ሥራውን እንዲጀምር ካህናት መለከት ይነፉ እንደ ነበር ጽፎአል:: የሥነ ቅርስ ሊቃውንት፣ ጢጦስ ከተማዋን በወረረ ጊዜ ቤተ መቅደሱ ከነበረበት ላይ ተንዶ በወደቀ አንድ ድንጋይ ላይ "መለከት የሚነፋበት ቦታ" የሚል ጽሑፍ አግኝተዋል::

13፥22 *አስበኝ፤* የ1፥8 ማብ ይመ::

*13፥23*፤ ከሃያ አምስት ዓመት በፊት ዕዝራም ተመሳሳይ እርምጃ ወስዶአል (የዕዝ 9፥1 ማብ ይመ):: *የአሽዶድን፤* 4፥7፤ ኢሳ 20፥1 እና ማብ ይመ:: *የአሞንንና የሞዓብን፤* የዘፍ 19፥36-38 ማብ ይመ::

*13፥24*፤ እስራኤላውያን ሌላውን ሕዝብ የሚለዩት በቋንቋው ነበር (ዘዳ 3፥9፤መሳ 12፥6፤ መዝ 114፥1፤ኢሳ 33፥19፤ሕዝ3፥5-6 ይመ)::

13፥25 *ጠጕራቸውንም ነጨሁ፤* ዕዝ 9፥3፤ ኢሳ 50፥6 እና ማብ ይመ:: *አትውሰዱ፤* ነህምያ የወሰደው እርምጃ ለወደፊት ከባዕዳን ጋር እንዳይጋቡ የሚከለክል ሲሆን፣ የዕዝራ እርምጃ ግን ጋብቻውን የሚያፈርስ ነው::

13፥26 *ሰሎሞን፤* በብልጽግናውና በፖለቲካው ስኬታማነት እጅግ የታወቀ የእስራኤል ንጉሥ ነበረ (1ነገ 3፥13፤ 2ዜና

አት የሠራው እንዲህ ከመሰለው ጋብቻ
የተነሣ አይደለምን? በብዙ በመንግሥታት
መካከል እንደ እርሱ ያለ ንጉሥ አልነበረም፤
በአምላኩም የተወደደ ነበረ፤ እግዚአብሔርም
በእስራኤል ሁሉ ላይ ንጉሥ አደረገው።
ነገር ግን ባዕዳን ሴቶች ወደ ኀጢአት መሩት።
27እናንተም ደግሞ ባዕዳን ሴቶችን በማግባት
ይህን የመሰለ ታላቅ በደል እንደምትፈ
ጽሙና በአምላካችንም ታማኞች እንዳልሆና
ችሁ መስማት ይገባናልን?
28ከሊቀ ካህኑ ከኤልያሴብ ልጅ ከዮአዳ
ልጆች አንዱ የሖሮናዊው የሰንባላጥ አማች
ነበረ፤ እኔም ከአጠገቤ አባረርሁት።
29አምላኬ ሆይ፤ የክህነትን ማዕረግ፣ የክህ
ነትንና የሌዋውያንን ቃል ኪዳን ስላረከሱ
አስባቸው።
30ስለዚህ ካህናቱንና ሌዋውያኑን ከማናቸ
ውም ባዕድ ነገር ሁሉ አነጻኋቸው፤ የእያን
ዳንዱንም ተግባር በመለየት በየሥራ ቦታ
ቸው መደብኋቸው። 31በተወሰነው ጊዜ ስለ
ሚቀጣውም የማገዶ ዕንጨትና ስለ በኵራቱ
መመሪያ ሰጠሁ። አምላኬ ሆይ፤ በቸርነት
አስበኝ።

13፥27 ዕዝ9፥14
13፥28 ዕዝ10፥24፤ ነህ2፥10
13፥29 ዘኍ3፥12፤ነህ1፥8
13፥30 ነህ9፥2
13፥31 ዘዳ8፥1፤ነህ1፥8፤10፥3
4:35-36

1፥12)። ሰሎሞን ንግሥናውን የጀመረው እግዚአብሔር ጥበብና ማስተዋል እንዲሰጠው በትሕትና በመለመን ነበር (1ነገ 3፥5-9)። *ኀጢአት የሠራው፤* ንጉሥ ሰሎሞን አጀማመሩ መልካም ቢሆንም የኋላ ኋላ ግን ከእስራኤል ነገድ ውጭ ያገባቸው ሚስቶቹ ባዕዳን አማልክትን እንዲያመልክ አደረጉት፤ እርሱም ዐልፎ ተርፎ ካሞሽ ለተባለው የሞዓባውያን አምላክ በኰረብታ ላይ የማምለኪያ ስፍራ እስከ መሥራት ደረሰ (1ነገ 11፥7)።

13፥28 *የሰንባላጥ አማች፤* በዘሌ 21፥14 መሠረት ሊቀ ካህን ከእስራኤል ነገድ ውጭ ማግባት አይፈቀድለትም። የዮአዳ ልጅ ከማኅበረ ሰቡ የተወገደው በዚህ ዐይነቱ ልዩ ዕገዳ መሠረት ሊሆን ይችላል፤ ወይም በአጠቃላይ ከባዕዳን ወገኖች ጋር መጋባት ስላልተፈቀደ ብቻ ይሆናል። በዚህ ጥቅስ ላይ የተነገረው ጋብቻ ከሰንባላጥ ጠላትነት የተነሣ (2፥10 ይመ)፣ በነህምያ ላይ ለብዙ ጊዜ ከባድ ሐዘን አስከትሏል።

13፥30 *ተግባር፤* "የሥራ ድርሻ" ማለት ነው፤ ይኸውም አንድን የተለየ ሥራ ለአንድ የካህናት ወይም የሌዋውያን ቡድን መስጠትን ያመለክታል፤ ሥራውም በፈረቃ የሚሠራ ይመስላል (የ12፥9 ማብ ይመ)።

13፥31 *የማገዶ ዕንጨት፤* የ10፥34 ማብ ይመ። *በኵራቱ፤* የ10፥35 ማብ ይመ። *በቸርነት አስበኝ፤* በመጽሐፉ መጨረሻ ላይ የተወሳው ይህ የነህምያ ቃል፣ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ጐልቶ የሚታየውን መሪ ሐሳብ (ቍ 14:22፤ የ1፥8ማብ ይመ) የሚያስተጋባ ነው። ነህምያ በአገልግሎቱ ሁሉ የነበረው ምኞት ልዑል የሆነውን አምላኩን ደስ ማሰኘትና ማገልገል ነበረ።